# ምድብ ሰባት
# ከገሊላ ያደረገው ስንብት
# (ሦስተኛ የአገልግሎት ዓመት)

**§ 72ሀ:ለ**
**በተሐድሶና መንፈሳዊ መነቃቃት መካከል**
**(ማቴ 14፥13-14፤ ማር 6፥30-34፤ ሉቃ 9፥10-13፤ ዮሐ 6፥1-3)**

ከኢየሱስ ሕይወት የመጨረሻ ሳምንት ቀደም ሲል ከተፈጸሙት በአራቱም ወንጌሎች የተጠቀሰው ይህ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ የኢየሱስ ታዋቂነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነበር፡፡ እውነተኛ ማንነቱን መግለጽ ከሚጀምርበት ከዚህ ጊዜ በኋላ ተወዳጅነቱም እያሽቈለቈለ ይሄዳል፡፡

ሰዎችን ከመገበበት ከዚህ ሁኔታ በተምሳሊትነት ወይም በትእምርትነት የተወሰዱ በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ ሥጋውን ስለ መብላትና ደሙን ስለ መጠጣት በተናገረው ንግግር ስለ ጌታ ራት እንደተጠቀሰ አድርገው ብዙዎች ያስባሉ (ማቴ 26፥20-29፤ ዮሐ 6፥35-59 ጋር ያነ)፡፡ ሌሎች ደግሞ ዐሥራ ሁለቱን ቅርጫቶች የዐሥራ ሁለቱ ነገዶች/ሐዋርያት ተምሳሊት እንደሆኑ ወይም የምግብ ዕደላ አገልግሎት የመሲሐዊ ግብዣ ምሳሌ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፡፡ ከከተማ ራቅ ባለ ቦታ ኢየሱስ ለሕዝቡ ያቀረበውንም ምግብ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለሕዝቡ ከሰጠው መና ጋር እያነጻጸሩ ይናገራሉ (ዮሐ 6፥30-33 ጋር ያነ)፡፡[1] ዓሣ የጥንት ክርስቲያኖች ጉልህ ስዕላዊ መገለጫ ሆኖ ኖሯል፡፡[2]

---

[1] B.E. Thiering, "Breaking of Bread' and 'Harvest' in John's Gospel," *NovT* 12 (1970): አምስት ሺውን መመገብን አስመልክቶ ከ1-12 ያለው ቍጥር በመላ-ምታዊ ቍጥር አሰጣጥ እንደ ዋና ምሳሌ የሚቀርብ ነው፡፡

[2] R. Hiers' "The Bread and Fish Eucharist in the Gospels and Early Christian Art," *PRS* (1970): ያለውን እጥር ያለ ግሩም ማብራሪያ ከገጽ 20-47 ይመ፡፡



የትኛውንም ነገር ወይም ሁኔታ እንደ ትእምርት ወይም ተምሳሊት ብንወስደው ማዕከላዊውን ስፍራ የሚይዘው ኢየሱስ ነው፡፡ ማርቆስ ርኅራኄውን ጕላ አድርጎ ያቀርባል (ማር 6፥34)፡፡ ዮሐንስ በተፈጥሮ ላይ ያለውን ሥልጣንና (ዮሐ 2፥1-11) መንፈሳዊ ጉድለታችንን የሚያሟላ መሆኑን አቅርቧል (ዮሐ 6፥26-59)፡፡ ማቴዎስ ስካር የሰፈነበትን ኃጢአታዊ የሄሮድስ ግብዣን ኢየሱስ ለገጠሬው ሕዝብ ካቀረበው ገራገር የምግብ ዕደላ ጋር በማነጻጸር ውበቱን ያሳያል፡፡ በእርግጥ በቦታው የነበሩና ይህንን ይከታተሉ የነበሩ ሰዎች ይህንን ኢየሱስ መሲሕ ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃ አድርገው ወስደውታል (ዮሐ 6፥15 ከ1ነገ 17፥9-16፤ 2ነገ 4፥42-44 ጋር ያነ)፡፡

**ማር 6፥30-31**

30ሐዋርያትም በኢየሱስ ዙሪያ ተሰብስበው
የሠሩትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት፡፡ 31ብዙ ሰዎች
ይመጡና ይሄዱ ስለ ነበር ምግብ እንኳ ለመብላት ጊዜ
ስላልነበራቸው፣ «እስቲ ብቻችሁን ከእኔ ጋር ወደ አንድ
ገለልተኛ ስፍራ እንሂድና ጥቂት ዕረፉ» አላቸው፡፡

ሐዋርያቱ በየግል ከተሰማሩበት ከሐዋርያዊ ጕዞ መመለሳቸው ነበር፡፡ በአስደናቂ ሁኔታ አገልግሎታቸው የተሳካ ነበር፡፡ በኢየሱስ ዙሪያ ተሰብስበው ስለ ስኬታማ አገልግሎታቸው ማለትም ስለ ተከናወኑ ፈውሶች፣ ስለ ተሰበሰበው ብዙ ሕዝብ፣ ንስሐ ስለገቡ ብዙ ሰዎች፣ አጋንንት ስለ ማስወጣታቸው ወዘተ እየነገሩት ሳለ የነበራቸውን ደስታ መገመት እንችላለን፡፡ የእነዚህን ሰዎች ማንነት ግምት ውስጥ በማስገባት ስናስብ አንዳቸው ከሌላው በመቀጠል ታሪኮቻቸውን ይናገሩ እንደ ነበር ማሰብ ይቻላል፡፡ ኢየሱስ እየተገረመ በትዕግሥት አደመጣቸው፡፡

ሆኖም በዚሁ ጊዜ (ቀደም ሲል የነበረውን ምንባብ መሠረት በማድረግ) ስለ አሳዛኙ የዮሐንስ ሞት ሲነግሩት ወደ እርሱ ከመጡ

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጋር ኢየሱስ ተገናኝቶ ነበር፡፡ የዮሐንስ ሞት በግል ኢየሱስን በእርግጥ በጣም አሳዝኖታል፡፡ ዮሐንስ ሥጋ ዘመዱ፣ ለአገልግሎቱ መንገድ የጠረገለትና ወዳጁም ነበር፡፡ ከሴት ከተወለዱት ሁሉ እጅግ የላቀውና የብሉይ ኪዳንም የመጨረሻ ነቢይ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ኢየሱስን በሁለት ተጻራሪ ስሜቶች መካከል ሚዛኑን እንዲጠብቅ አድርጐታል፤ በአንድ በኩል በሐዋርያቱ ደስ ተሰኝቶአል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዮሐንስ በሄሮድስ በመገደሉ ክፉኛ አዝኖአል፡፡

በእርግጥም ሁኔታው ከአካባቢው ዘወር ማለት ተገቢ የሆነበት ጊዜ ነበር፡፡ ኢየሱስም ሆነ ዐሥራ ሁለቱ የቅርብ ጊዜ ሁኔታዎችን ወደ ኋላ ዘወር ብለው የሚያስቡበትና ይህ ሁኔታ ወዴት እያመራ እንደ ሆነ የሚገመግሙበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ የሚመገብበት ጊዜ እስከሚያጣ ድረስ ሰዎች እየመጡ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ የኢየሱስን ዝና ከመስማት፣ አንዳንዶቹ ዐሥራ ሁለቱ በቅርቡ ካደረጉት የተልዕኮ ጉዞ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በዮሐንስ መገደል ከመቈጣታቸው የተነሣ መጥተው ነበር፡፡ ይህ ጊዜ የኢየሱስ ዝና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነበር፡፡ ሕዝቡ የሚሆነውን በመጠበቅ ስሜታቸው በጣም ተነሣሥቶ ነበር፡፡

ለተሐድሶና ለመንፈሳዊ መነቃቃት ብቻ ሳይሆን ከሄሮድስ ግዛት ለመሸሽና እስራትና ተቃውሞ እንዳይነሣ ለማድረግ ጭምር ወደ ገለልተኛ ስፍራ መሄድ ነበረባቸው፡፡ ስለዚህም በጀልባ ተሳፍረው የገሊላ ባሕርን በማቋረጥ የሄሮድስ ፊልጶስ ግዛት ወደ ነበረችው ወደ ትንሿ ቤተ ሳይዳ (ቃል በቃል፣ «የዓሣ ቤት» ሄዱ፡፡ ይህችኛዋ ቤተ ሳይዳ የፊልጶስ፣ የእንድርያስና የጴጥሮስ ትውልድ ቦታ የነበረችው ቤተ ሳይዳ ልትሆን አትችልም (ዮሐ 1÷44)፡፡[3] በዚያ ዘመን በተመሳሳይ ስም የሚጠሩ በርካታ ከተሞች ወይም መንደሮች መኖራቸው የተለመደ

[3] ለአማራጭ ገለጻና የቤተ ሳይዳውን ውዝግብ በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት S.H. Smith, "Beth¨aida via Gennesaret: The Enigma of the Sea Crossing in Mark 6:45-53," *Biblica* 77/3 (1996): 349-374 ይመ፡፡



ነበር፡፡ ታምራቱ ከተከናወነ በኋላ ወደ ቤተ ሳይዳ ሄዱ (ማ 6÷45)፡፡ ከዚህም በላይ የፊልጶስ፣ የእንድርያስና የጴጥሮስ ትውልድ ቦታ ለኢየሱስና አብረውት ለነበሩት መደበቂያ የሚሆን «ገለልተኛ ስፍራ» አልነበረም፡፡

**ማር 6÷32-34፤**
**ሉቃ 9÷10-11፤**
**ዮሐ 6÷1-3 ጋር**

32ስለዚህ ብቻቸውን [ወደ ባሕር ዳርቻ[ዮሐ]] ወደ
አንድ ገለልተኛ ስፍራ [ቤተ ሳይዳ ወደምትባል ከተማ[ሉቃ]]
በጀልባ ሄዱ፡፡ 33እነርሱም ሲሄዱ ብዙ ሰዎች አይተው
ዐወቋቸው፤ ከከተሞችም ሁሉ በእግር እየሮጡ ቀድመዋቸው
ደረሱ [በሽተኞችን በመፈወስ ያደረጋቸውን ታምራዊ
ምልክቶች ስላዩ ተከተሉት[ዮሐ]]፡፡ 34ኢየሱስ ከጀልባዋ
በሚወርድበት ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ አየ፤ [እርሱም
ተቀብሉአቸው[ሉቃ]] እረኛ እንደሌላቸው በጐች ስለነበሩም አዘነላቸው፤ [ወደ ተራራ
ወጥቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ[ዮሐ]] ብዙ ነገርም ያስተምራቸው ጀመር [ስለ
እግዚአብሔር መንግሥት ይነግራቸው ነበር፤ ፈውስ የሚያስፈልጋቸውንም ፈወሳቸው[ሉቃ]]፡፡

ሐዋርያቱና ኢየሱስ በጀልባ ሲሳፈሩ ሕዝቡ ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄዱ መቅዘፊያቸውን እየተመለከቱ ነበር፡፡ በባሕሩ ዙሪያ በመሄድ ጥቂቶቹም ኢየሱስን ቀድመው ወደ ዳርቻው ደረሱ፡፡[4] እኛ እንደምናደርገው ሳይሆን ኢየሱስ የራሱን ረሀብና ድካም ከማስታገሥ ይልቅ የሰዎችን ችግር ማስወገድ ይገደው ነበር፡፡ የሕዝቡ የእውቀት ማጣትና የፈውስ ፍላጐት ያስጨንቀው ነበር፡፡ ረሃባቸውና የምግብ ፍላጐታቸው ያሳስበው ነበር፡፡ እርሱን ለመከተል ያላቸው ጉጉትና መሲሑን የማወቅ ጥማታቸው ልቡን ነክቶት ነበር፡፡ ከሁለት ሺህ

[4] ኢየሱስን በመቅደም ከባሕሩ ዳርቻ ስለ ደረሱትና እሱ ላይም ለመድረስ በመሞከር ሁለት ኪሎ ሜትር ርዝመት ከኋላው ይጓዙ የነበሩ ሰዎችን ስልፍ ስናስብ መጀመሪያ የደረሰው የትኛው እንደ ሆነ በማርቆስ 6÷33 እና በዮሐ 6÷5 መካከል ያለ ለሚመስለው አለመጣጣም መልስ ልናገኝለት እንችላለን፡፡

ዓመታት በኋላ እንኳ ከዚህ የበለጠ ለአገልግሎት አርዓያ ሊሆነን የሚችል አልተገኘም። እኛ በእርግጥ እረኛ የሌላቸውን በጐች የምንረዳ ነን (ማቴ 9፥36፤ ዘኍ 27፥1፤ ሕዝ 34፥5:23:25 ጋር ያነ)።

ዮርዳኖስ ወደ ከገሊላ ባሕር ጋር ከሚቀላቀልበት ሁለት ኪ.ሜ. ከፍ ብሎ በስተሰሜን በኩል ወንዙን ለመሻገር የሚያመች ቦታ አለ። አንድ ኪ.ሜ. ከፍ ብሎ ቤተ ሳይዳ ጁሊያስ አጠገብ ሣር የሞላበት ሰፊ ሜዳ አለ። ከዚያ ሜዳ በስተ ሰሜን በኩል ያለው ተራራ ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር የወጣበት ሳይሆን እንደማይቀር ይታሰባል። ሁኔታው ትኩረት የሚስብ ነበር፤ 5000 ወንዶች (አንድሬስ - andres) ሴቶችና ሕፃናት ጭምር በዚያ ቦታ ነበሩ። ቍጥራቸው ወደ 15000 ያህል ሊጠጋ እንደሚችል ይታሰባል። «እረኛ የሌላቸው በጐች» በሚለው ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ በተመለከተ §70ሀ ይመለከቷል።

**§ 72ሐ**
**5000 ሰዎችን መመገቡ (ማቴ 14፥15-21፤ ማር 6፥35-44፤ ሉቃ 9፥12-17፤ ዮሐ 6፥4-13)**

[ዮሐ6]4የአሁድ የፋሲካ በዓልም ተቃርቦ ነበር።
5ኢየሱስም ቀና ብሎ ሲመለከት ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ
ሲመጣ አየ፤ ፊልጶስንም፣ «እነዚህ ሁሉ እንዲበሉ
እንጀራ ከየት እንግዛ?» አለው። 6ይህን የጠየቀው
ሊፈትነው እንጂ ራሱ ሊያደርግ ያሰበውን ያውቅ ነበር።
7ፊልጶስም፣ «እያንዳንዱ ሰው ትንሽ ትንሽ
እንዲቃመስ ለማድረግ፣ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ
እንኳ አይበቃም ሲል መለሰ።

ይህ የፋሲካ በዓል በኢየሱስ ሁለተኛና ሦስተኛ አገልግሎት ዓመት ሽግግር የተከናወነበት ነበር። ፋሲካ ከወቅት መንገሪያነት ያለፈ ፋይዳ ያለው ነበር። ያን ያህል ብዛት ያለው በተለይም በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ የሚያደርጉ ሰዎች ለምን በዚያ እንደተገኙ መግለጫ የሚሰጥ ነበር። ኢየሱስን ለማንገሥ የነበራቸውን የጋለ ስሜትም



የሚያስረዳ ነበር። የአይሁድ ሃይማኖታዊ ብሔርተኛነት ከምንጊዜውም ይልቅ በፋሲካ በዓል ሰሞን ይበረታል። ደስ የተሰኘው ይሄ ቡድን በባሕሩ ዙሪያ እየተጓዘ ባለፈባቸው መንደሮችና ሰፈሮች የነበሩ ሰዎችን በእርግጥ ሳያስከትል አይቀርም። ስልፉ ኢየሱስ ከሚያርፍበት ቦታ ሲደርስ ሁኔታው የተለየ ግዙፍ መልክ ይኖረዋል። ኢየሱስ ቀና ብሎ ሲመለከት ሕዝቡ እርሱን እንደከበቡት አየ (ዮሐ 4፥25 ጋር ያነ)።

ትኩረቱን ለምን በፊልጶስ ላይ አደረገ? አናውቅም። ምናልባትም ኢየሱስ ሊያስተምረው የፈለገው አንዳች ነገር ስለ ነበር ሊሆን ይችላል (ዮሐ 14፥8-9)፣ ምናልባት አጠገቡ የነበረው እርሱ ስለ ነበር ይሆናል። ፊልጶስ የሰጠው ቁርጥ ያለ መልስ ቀደም ብሎ ወጪውን ሳያሰላ እንዳልቀረ ያመለክታል። ኢየሱስ ማስተማሩንና መፈወሱን በቀጠለበት ጊዜ ፊልጶስ መልስ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ጥያቄውን ራሱን ለማውጣትና ለማወረድ ሰፊ ጊዜ ነበረው። የኢየሱስ ትኩረት ፊልጶስ በሚሰጠው መልስ ላይ ሳይሆን በሚያሳየው ዝንባሌ ላይ እንደ ነበር ግልጽ ነው።

**ማር 6፥35**
**ሉቃ 9፥12 ጋር**

35በዚህ ጊዜ ቀኑ እየመሸ በመሄዱ ደቀ
መዛሙርቱ [በሥራ ሁለቱ[ሶቃ]] ወደ እርሱ ቀርበው እንዲህ
አሉት፤ «ይህ ቦታ ምድረ በዳ ነው፤ ቀኑም መሽቶአል፤
36በአካባቢው ሰው ወደለበት መንደር ሄደው የሚበላ ነገር
ገዝተው እንዲመገቡ አሰናብታቸው። 37እርሱ ግን መልሶ፣ «የሚበሉትን እናንተው
ስጧቸው» አላቸው። እነርሱም፣ «ሄደን በሁለት መቶ ዲናር እንጀራ ገዝተን
የሚበሉትን እንስጣቸውን?» አሉት።
38እርሱም፣ «ስንት እንጀራ አላችሁ? አስቲ ሄዳችሁ እዩ አላቸው።
አይተውም፣ «አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ አሉት።

ቀኑ እየመሸ ነበር የሚለው ምናልባት ከሰዓት በኋላ ከዘጠኝ እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት ያለውን ወቅት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል::[5] የነበሩት ከከተማ ውጪ ራቅ ካለ ስፍራ (ብዙ ኪሎ ሜትሮች የሚርቁ ሊሆኑ ይችላሉ) ስለ ነበር ሕዝቡ በአቅራቢያው ወዳሉት ሰፈሮች ደርሰው፣ «አልጋና እራት» ለማግኘት በቂ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል:: በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሐዋርያት እንደ ኢየሱስ ለሰዎች እንክብካቤ ማድረግን ተምረዋል:: ምናልባትም እነርሱ ራሳቸውንም ሳይርባቸው አልቀረም:: ለመመገብ ጊዜ እንዳልነበራቸው እናስታውሳለን::

ለሕዝቡ የሚበሉትን እንዲሰጡ ኢየሱስ ለዐሥራ ሁለቱ ሲናገር የአስቆሮቱ ይሁዳ ሳይናደድ እንዳልቀረ እናስባለን:: ያን ያህል ገንዘብ አይኖራቸውም እንጂ ቢኖራቸው ኖሮ ገንዘባቸውን ሁሉ ማሟጠጣቸው ነበር:: ይህ ደግሞ ማንኛውንም ገንዘብ ያዥ በተለይም የመቆንጠር ልማድ ያለውን እንደሚያናድድ ግልጽ ነው::

በእጃቸው ላይ ያለው ምን እንደ ሆነ ሕዝቡን በሚገባ እንዲሰቡ ኢየሱስ ላካቸው:: ወደ እርሱ የተመለሱት ባዶ እጃቸውን ነበር ማለት ይቻላል:: ለአንድ ትንሽ ልጅ ምሳ ሊሆኑ የሚችሉ አምስት እንጀራዎችንና ሁለት ዓሣዎችን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገዋል::[6] እንጀራዎቹ የእኛን ያህል ትልልቅ አልነበሩም:: ትንንሽ፣ ጠፍጣፋና ክብ ነበሩ (ምናልባት ዙሪያውን ከአራት ጋት የማይበልጡ):: የገብስ እንጀራዎች ነበሩ፣ ገብስ ደግሞ የድሆች ምግብ ቢሆንም የምግብ ይዘቱ

---

5 ኤደርሼይም እንደሚለው አይሁድ የመጀመሪያ ምሽት የሚሉት የጀምበርን ማዘቅዘቅ (ከዘጠኝ እስከ ዐሥራ ሁለት ሰዓት) ሲሆን፣ ሁለተኛው ምሽት ደግሞ ፀሐይ ስትጠልቅ የመጀመሪያው ኮከብ ከሚታይበት፣ ሦስተኛው ኮከብ እስከሚታይበት (ከዐሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት) ያለውን ጊዜ በማለት መድበውታል:: ሌሊቱ የሚቀጥለው ቀን መዳረሻ እንደሆነ ይታሰባል::

6 ሦስቱ ተወራራሽ ወንጌሎች ዓሣን በተለመደው ቃል [*ichthys*] በማለት ጠርተውታል:: ዮሐንስ ግን፣ ተቀናብሮ የተዘጋጀ ዓሣን ማለትም እንደ ቋንጣ የተዘጋጀ ወይም የተቀመመ ሆኖ ከዳቦ ጋር የሚበላውን ዓሣ በማመልከት [*opsarion*] በሚለው ያልተለመደ ቃል ነው የተጠቀመው::



ደካማ አልነበረም:: ዓሣዎቹ የተቀመሙና ለዳቦው እንደ ማባያ የሚሆኑ ነበሩ እንጂ ዋና ምግብ አልነበሩም:: ምናልባትም በቀርቀሮ እንደ ታሸገ ሰርዲን ዓይነት ነበሩ ማለት ይቻላል:: አንድን ልጅ ለማጥገብ የሚበቃ ቢሆንም ከዚያ ሕዝብ ብዛት አንጻር ግን ግምት ውስጥ የሚገባ አልነበረም::

**ዮሐ 6፥8-11**
**ማቴ 14፥18-19፤**
**ማር 6፥41፤**
**ሉቃ 9፥16 ጋር**

8ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ የስምዖን ጴጥሮስ
ወንድም እንድርያስም፣ እንዲህ አለ፣ 9«አምስት ትንንሽ
የገብስ እንጀራና ሁለት ትንንሽ ዓሣ የያዘ አንድ ልጅ
እዚህ አለ፤ ይህ ግን [ሄደን ካልገዛን በስተቀር[ሉቃ]] ለዚህ
ሁሉ ሕዝብ አይበቃም አለ:: 10ኢየሱስም፣ [ወደ እኔ
አምጡት[ማቴ]] «ሰዎቹ እንዲቀመጡ አድርጉ» አለ:: በዚያ ቦታ ብዙ ሣር ነበረ፤ አምስት
ሺህ ያህል ወንዶችም [መቶ መቶና አምሳ አምሳ ሆነው[ማር]] ተቀመጡ:: 11ኢየሱስ
አምስቱን እንጀራ አንሥቶ አመሰገነ፤ ለተቀመጡትም የሚፈልጉትን ያህል ዐደለ፤
ዓሣውንም እንዲሁ::

እንድርያስ ሦስት ጊዜ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ማምጣቱን ዮሐንስ አመልክቷል፤ (1) ጴጥሮስን (1፥40-41)፣ (2) ይህን ልጅ (6፥8-9)፣ (3) የግሪክ ሰዎችን (12፥22):: ይህ የእርሱ የተለየ ስጦታ ሊሆን ይችላል:: ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ደቀ መዛሙርት አንዱ የነበረው ሰው ከወንድሙ ከጴጥሮስ በስተጀርባ (በራሱ ፈቃድ ይመስላል) በመሆኑ ትሕትናው ያስገርመናል:: ኢየሱስ በደብረ ዘይት ባስተማረበት በማርቆስ 13፥3 ከምንመለከተው በስተቀር ይህ ሰው እንደሚገባ ባይሆንም ኢየሱስን በጣም ከሚቀርቡት አንዱ ነበር:: እንድርያስ ጥቂት ምግብ የያዘውን ልጅ ይዞ ቢመጣም፣ አሁንም ቢሆን ወደ ገበያ ሄዶ ስለ መግዛት እያሰበ ነበር::

ፋሲካን ተከትሎ የሚበቅለው የፀደይ ሣር ለሕዝቡ የእንኳን ደኅና መጣችሁ ዓይነት ምንጣፍ ሆኖ ነበር:: ለመቍጠርና ለማደል በሚመች ሁኔታ ሕዝቡ በአምሳ በአምሳ በመቶ በመቶ ሆነው በቡድን ተቀመጡ:: ማርቆስ ስለ ሕዝቡ ሲናገር አንድ የተለየ ቃል ተጠቅሞአል (6÷40) [*Prasiai*] ማለት ቃል በቃል «የአትክልት መደብ» ማለት ነው::[7] ያ ሁሉ ሰው እዚያ ለምለም ሜዳ ላይ ጋደም ብሎ ኢየሱስ ደግሞ ቆሞ ሲታይ በእርግጥም በእግዚአብሔር የአበቦች አትክልት ቦታ ይመስል ነበር::

ኢየሱስ ምግቡ ከመቅረቡ በፊት አንድ አይሁዳዊ የቤተሰብ መሪ እንደሚያደርገው መሠረት ወደ ሰማይ ቀና ብሎ አመሰገነ:: ምናልባትም «ምግብን ከመሬት የምታወጣ የፍጥረተ ዓለሙ ንጉሥ፣ ጌታ አምላካችን ሆይ ስምህ ቡሩክ ይሁን» (*m.Ber* 6:1) የሚለውን ዓይነተኛ የምስጋና ጸሎት አቅርቦ ይሆናል::

ከአራቱ ወንጌል ጸሐፊዎች አንዱ እንኳ ይህ ተአምር እንዴት እንደ ተፈጸመ ፍንጭ አለመስጠታቸው የሚያስደንቅ ነው:: ኢየሱስ ነገሮች እንዲበረክቱ የማድረግ ሥልጣን (ኤልያስ ምናልባት እንደነበረው ሁሉ - 2ነገ 4÷42-44) እንደ ነበረው ይታሰብ ነበር:: በቃና ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ እንደ ለወጠ ሁሉ አሁንም የገብስ እንጀራዎቹንና ዓሣዎቹን «እም ሀበ አልቦ» እንዲበረክቱ አድርጎ ይሆናል:: በሌሎች ጊዜያት ኢየሱስ በተፈጥሮ ላይ ያለውን ሥልጣን አሳይቶ ነበር፤ በተአምር ዓሣዎችን አጥምዷል (ሉቃ 5÷5-10) ባሕሩን ፀጥ አሰኝቷል (ሉቃ 8÷24):: አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር ችሎታው (ዮሐ 1÷1-4፤ቈላ 1÷16-17 ጋር ያነ) እዚህ ላይ የዓይነት ልዩነት አሳይቶ ነበር::

[7] *Anepesan* ቃል በቃል፣ «መጋደም» ማለት ነው:: ቃሉ በእርግጥ አይሁዳውያን ሲመገቡ ጋደም የማለት ልምዳቸውን በሚገባ የሚገልጽ ነው::

**ዮሐ 6÷12-13**

[12]ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱን፣ «ከተረፈው ቍርስራሽ ምንም እንዳይባክን ሰብስቡ» አላቸው:: [13]እነርሱም ከተበላው አምስት የገብስ እንጀራ የተረፈውን ቍርስራሽ ሰብስበው ዐሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ::

**ማቴ 14÷21**

[21]የበሉትም ከሴቶችና ከሕፃናት ሌላ አምስት ሺህ ወንዶች ያህል ነበሩ::

ዐሥራ ሁለት መሶብ የኢየሱስን መልካም ባለ አደራነት የሚያመለክት አይመስልም:: ይልቁንም የዐሥራ ሁለቱን ቅርጫቶች ተምሳሌትነት የሚያመለክት ይሆናል:: እነዚህ በሸንበቆ ተጠላልፈው የተሠሩ ቅርጫቶች [*kophinos*]፣ «አይሁዳውያን በሕግ ንፁሐን እንደሆኑ የተደነገጉ ምግቦችን የሚይዙባቸው ቅርጫቶች ናቸው» (Blomberg. p. 233):: ዐሥራ ሁለት የእግዚአብሔር በረከትን ይወክላል::

**§ 73**
**ያልተሳካው ኢየሱስን የማንገሥ ሙከራ**
**(ማቴ 14÷22-23፤ ማር 6÷45-46፤ ዮሐ 6÷14-15)**

[ዮሐ6:][14]ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት ካዩ በኋላ፣ «ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው» አሉ::

[ማቴ14:][22]ወዲያውኑ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ተሳፍረው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት አዘዛቸውና እርሱ ሕዝቡን ለማሰናበት ወደ ኋላ ቀረት አለ::

[ዮሐ6:][15]ኢየሱስም ሰዎቹ መጥተው በግድ ሊያነግሡት እንዳሰቡ ዐውቆ እንደ ገና ብቻውን [ለመጸለይ[ማቴ፣ማር]] ወደ ተራራ ገለል አለ::

ሕዝቡ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ተገንዝበዋል (ነቢዩ፣ ዘዳ 18፥15-18፤ ዮሐ 1፥21 ጋር ያነ):: በመጨረሻ እንደ መሲሕ እንዲያደርግ የፈለጉትን ማድረግ ጀመረ::[8] በወቅቱ በነበረው መሲሑን የመጠባበቅ መንፈስ የተገፋፋው በቅርቡ በተገደለው የመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ቁጣው የጋለው ይህ ትዕግሥት የሌለው ሕዝባዊ ጉባኤ ቢፈልገውም ባይፈልገውም ኢየሱሱን ለማንገሥ ዝግጁ ነበር:: ምናልባትም የተራረፈውን ዐሥራ ሁለት መሶብ ቁርስራሽ አንግበውና በእርሱ የተፈወሱትን ሰዎች አስከትለው የነፃነት አዋጃቸውን እያሰሙ እስከ ኢየሩሳሌም አጅበውት ሊሄዱ ቆርጠዋል::

ኢየሱስ ግን ሦስት ወሳኝ ነገሮችን በማድረግ ሙከራቸውን አጨናገፈ፤ (1) ሐዋርያቱን ሰደዳቸው:: (2) ሕዝቡን አሰናበታቸው:: (3) ብቻውን ወደ ተራራ ሄዶ ተሰወረ:: በመጨረሻም ኢየሱስ ይፈልገው የነበረውን ዕረፍት አገኘ:: ዕረፍቱ የአካል ዕረፍት ሳይሆን ከአባቱ ጋር በግል ለመገናኘት ገለል ማለቱ ነበር:: ኢየሱስ ከእንቅልፍ ይልቅ በጣም አስፈላጊ አድርጎ የወሰደው ጸሎትን እንደ ነበር ግልጽ ነው:: ምንም እንኳ ማቴዎስና ማርቆስ ኢየሱስ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙት ይጸልይ እንደ ነበር የሚያቀርቡልን ቢሆንም (ማቴ 14፥22-23፤ 26፥36-39፤ ማር 1፥35) ሉቃስ ግን ኢየሱስ ዘወትር ይጸልይ እንደ ነበር ያመለክታል (ሉቃ 5፥16፤ 6፥12-13፤ 9፥18፤ 9፥28-29፤ 11፥1)::

---

[8] በመጀመሪያው መቶ ዓመት አንድን የዋህ የገጠር ሰው ወደ ንጉሥነት ደረጃ ያወጡ የተለያዩ ሕዝባዊ ዓመፆች በአይሁድ መካከል ይካሄዱ ነበር:: R.A. Horsley, "Popular Messianic Movement around the Time of Jesus," *CBQ* 46 (1984): 471-495 ያነ:: ሆኖም እነዚህ ሁሉ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ሕዝባዊ ዓመፆች ነበሩ:: ዓመፆቹ ገበሬዎችን ከሮምና ከሄሮድስ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በግልጽ የታለሙ ነበሩ:: ምንም እንኳ ኢየሱስን በኃይል ለማንገሥ የተደረገው ሙከራ ከእነዚህ ሕዝባዊ ዓመፆች የመነጨ ሊሆን ቢችልም ኢየሱስ ከ[illegible]ግለት ዓላማ ጋር ግን በፍጹም ሊነጻጸሩ የሚችሉ አልነበሩም::



## § 74
## በባሕር ላይ *መራመዱ*
(ማቴ 14፥24-33፤ ማር 6፥47-52፤ ዮሐ 6፥16-21)

ይህ ትረካ አንድ ሳይሆን አራት ተአምራቶችን ይዟል (1) በውሃ ላይ መራመዱ፣ (2) ጴጥሮስ በውሃ ላይ እንዲራመድ ማድረጉ፣ (3) ማዕበሉን ፀጥ ማሰኘቱ፣ (4) በቅጽበት ወደ የብስ መምጣቱ:: የኢየሱስን ሉዓላዊነት ጉላ አድርጎ በማቅረብ፣ 5000 ሕዝብ ለመመገቡ ታሪክ ድጋፍ ይሰጣል:: ከዚያም በላይ ሰዎች ኢየሱስን በትክክለኛው መንገድ አለመረዳታቸውን አስመልክቶ በዚህ ክፍል የተነሣውን ዐቢይ ሐሳብ ይቀጥላል:: በእውነትም ሕዝቡ ኢየሱስን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ነበር:: ቀደም ሲል ለመጥምቁ ዮሐንስ እንኳ የኢየሱስ ማንነት አጠያያቂ ሆኖበት ነበር:: አሁን ደግሞ 5000 ሰዎችን ከመገበ በኋላ የራሱ ደቀ መዛሙርት እንኳ በትክክል አላወቁትም (ማር 6፥52)::

ማር 6፥47-49
ማቴ 14፥24፤
ዮሐ 6፥19፤17 ጋር

47 በመሸም ጊዜ ጀልባዋ [ባሕሩን ዘልቃ እየተጓዘች ሳለች[ማቴ]] ባሕሩ መካከል ነበረች:: እርሱም ብቻውን በምድር ላይ ነበር:: 48 ነፋስ በርትቶባቸው ስለነበር፣ ደቀ መዛሙርቱ ከመቅዘፊያው ጋር ሲታገሉ አያቸው፤ [አምስት ወይም ስድስት ኪሎሜትር እንደ ቀዘፉ ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ወደ ጀልባዋ ሲመጣ አዩተው[ዮሐ]] በአራተኛውም ክፍለ ሌሊት ገደማ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ [ጊዜው መሸቶ ነበር፤ ኢየሱስም ወደ እነርሱ ገና አልመጣም ነበር[ዮሐ]] በአጠገባቸውም ዐልፎ ሊሄድ ነበር:: ነገር ግን 49 በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ፤

> 26ፈሩ፤ እነርሱም «ምትሀት ነው!» በማለት በፍርሃት ጮኹ። 27ኢየሱስም ወዲያውኑ፣ «አይዞአችሁ እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው። — ማቴ 14፥26-27

መቼም እነዚያ 5000 ሰዎች ምናልባት እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ድረስ እዚያ ሳይሆኑ አይቀሩም። እንዲህ ያለው ጉዳይ እንዲያበቃ የሚፈልግ አይኖርም። በስሜት የገነፈለውን ሕዝብ ለማረጋጋትና በቅድሚያ ዐሥራ ሁለቱን በኋላም 5000ውን ለማሰናበት ኢየሱስ ጥቂት ጊዜ አስፈልጎት ነበር። ከምሽቱ አንሥቶ ከሐዋርያቱ ጋር እንደገና እስከተገናኘበት እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት[9] ሲጸልይ ነበር።

በተራራው ላይ ከነበረው የመመልከቻ ስፍራ ኢየሱስ በፋሲካ ወቅት በምትወጣው ሙሉ ጨረቃ ብርሃን ከባሕሩ ማዶ ማየት ይችል ነበር። የባሕሩን ዳርቻ ለቀው መንቀሳቀሳቸውን ማየት ይችል ነበር። በሰሜናዊው ባሕር ዳርቻ ወደ ቤተ ሳይዳ ከማምራት ይልቅ በደቡባዊ ምዕራብ ባሕር ዳርቻ በኩል ወደ ጌንሳሬጥ እየተቃረቡ ነበር። አምስት ወይም ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል በመጓዛቸው ወደ ባሕሩ መካከል ተዳርሰው ነበር። ፊት ለፊት ይነፍስ ከነበረው ኀይለኛ ነፋስ የተነሣ አብዛኛውን የሌሊቱን ክፍል ያሳለፉት በትግል ነበር።

ለሐዋርያቱ ይህ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነበር። ኢየሱስን ለማንገሥ ሕዝቡ የነበረው ስሜት ተካፋዮች ነበሩ። ኢየሱስ ንጉሥ ቢሆን እነርሱም በሚገባ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ ከፖለቲካዊ መሲሕ ሲጠብቁ የነበረውም ይህንኑ መሳይ ነገር ነበር። ኢየሱስ ከዚያ ዘወር እንዲሉ ማድረጉ አሳዝኖአቸዋል። ይባስ ብሎ የተላኩት ወደ ማዕበል ውስጥ እንዲገቡ ነበር። ወደ ባሕሩ መሐል ደርሰው፣ በዚያ ማዕበል

[9] ሌሊቱ እያንዳንዳቸው ሦስት ሰዓት ገደማ ርዝመት ባላቸው አራት ክፍሎች የተከፈለ ነበር። አራተኛው ክፍል ከ9-12 ሰዓት ያለው ነው።



መካከል መሆናቸው 5000 ሰዎችን ከመገበ በኋላ እንኳ[10] የኢየሱስ ጌትነት አጠያያቂ እንዲሆንባቸው ሳያደርጋቸው አልቀረም። ኢየሱስ በባሕር ላይ መራመዱ የሚያስገኘውን ተጨማሪ ትምህርት ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ክፍል ዮሐንስ ለታሪኩ የዓይን ምስክር ድባብ መስጠት በሚችሉ ግሦች ተጠቅሞአል።

> ሁኔታውን በተለይም በጀልባው ያሉትን ሰዎችና ባሕሩን በተመለከተ፣ «እየገሠገሡ ነበር» ወይም «ባሕሩ እየተናወጠ ነበር» ወይም፣ «እየተነሣ ነበር» በሚል የነገር መቋጫን በማያመለክት ግሥ ተጠቅሞአል። ይሁን እንጂ በዚህ መቋጫን በማያመለክቱ ግሦች መሐል ወደ ባሕሩ ዳር ከመድረሳቸው በፊት የሆነውን ለማመልከት (ኢየሱስ) «ወደ እነርሱ ገና አልመጣም ነበር» ብሏል። (Hendriksen p. 224)

ስለሆነም ሁለት ትዕይንቶችን እናያለን ማለት ነው። በአንድ በኩል በዚያ ፀጥ ባለ ሌሊት ኢየሱስ እየጸለየ ነበር። በሌላ በኩል ሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሐዋርያቱ በማዕበል መሐል መቅዘፊያውን ይዘው እየታገሉ ነበር። ሐዋርያቱ ከጌታ ዕይታም ሆነ ሐሳብ ውጪ አልነበሩም።

ኢየሱስ በቀጥታ ባሕሩን መሐል ለመሐል እያቋረጠ መጣ! ደቀ መዛሙርቱን ለመርዳት እየመጣ ነበር። ታዲያ ማርቆስ፣ «ዐልፎ ሊሄድ ነበር» ያለው ለምንድነው? እያፌዘባቸው ነበርን? በአቋራጭ ወደ ባሕሩ በመሄድ ደቀ መዛሙርቱን መቅደም ፈልጎ ነው? እንደ መፍትሔ

[10] በዚህ ዘመን ብዙ አንድምታዊ የቤተ ክርስቲያን ንፅፅሮችን ማግኘት ይቻላል። አንዳንዴ ራሳችንን እንደ ከበቡን የምናገኛቸው ማዕበሎች የኢየሱስን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥሩ ፈተናዎች አይደሉም። ኤደርሼም እንደሚለው (I:691) «ሁኔታውን ማለትም ሌሊቱን፣ የጨረቃውን ብርሃን፣ ትንሹን ጀልባ፣ ዐውሎ ነፋሱን፣ ከጸሎት በኋላ ወደ ባሕሩ ዳር ለመምጣት በከንቱ ይደክሙ የነበሩትንና ጀልባው ላይ የነበሩትን ሰዎች ከማዶ የማየቱን ብቸኛው አዳኝ ታሪክ ስንመለከት ነገሩ ሁሉ ተምሳሊታዊ ይመስላል»።

የምናቀርበው ወደ ባሕሩ ዳር እየደረሱ ስለነበር ጥቂት ቆይቶ እዚያ ስለሚያገኛቸው ነበር:: ማክኢነርኒ በጣም የተወሳሰበ መፍትሔ አቅርቧል::[11][12] በብሉይ ኪዳን፣ «ዐልፎ» የሚለው ቃል የያህዌን መገለጽ ለማመልከት ተጠቅሷል:: ምናልባትም ማርቆስ ማሳየት የፈለገው የኢየሱስ በባሕር ላይ መራመድ ከእግዚአብሔር መገለጽ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ነው:: ሦስተኛው መፍትሔ በጀልባው ትይዩ እስከሚሆን ድረስ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን አላወቁትም ነበር የሚል ነው:: ካዩት በኋላ እያለፈ የነበረው ጣረ-ሞት ሳይሆን እንደማይቀር አሰበዋል:: ስለሆነም፣ «ዐልፎ ሊሄድ ነበር» የሚለው ደቀ መዛሙርቱ የመሰላቸው እንጂ የኢየሱስ ሐሳብ አልነበረም::

ሐዋርያቱ መፍራታቸው የሚገርም አይደለም:: ትኩረታቸው ሁሉ ከዚያ ማዕበል ከሚያናውጠው ባሕር በመውጣት ላይ ያለ ሰው መሰል ፍጡር ወይም ምትሐታዊ የጣረ-ሞት ገጽታ ላይ ነበር:: ጣረ-ሞት (ከአካል የተለየ መንፈስ) እንደሆነ ማሰባቸው የተለመደና የሚጠበቅ ነው:: ዛሬስ ቢሆን ከዚህ የተለየ የሚያስብ ማነው? የልባቸው ሀዘንና የአካላቸው መዛል ለነበራቸው አቋም ድጋፍ መስጠት አይችልም::

ኢየሱስ ወዲያውኑ ራሱን በመግለጽ ሊያረጋጋቸው ሞከረ:: «እኔ ነኝ» የሚለው በዘፀአት 3፥14 መሠረት እግዚአብሔር ራሱን፣ እኔ ነኝ በማለት ከገለጸበት ጋር ይመሳሰላል:: ምንም እንኳ የተድበሰበሰ

[11] የዓይን ምስክር ያልነበረው ሉቃስ ወንጌሉ ውስጥ ይህን ታሪክ አለማስፈሩን ስናስተውል እንደነቃለን::

[12] W.F. McInerny, "An Unresolved Question in the Gospel Called, Mark: 'Who Is This Whom Even the Wind and Sea Obey?' (4:41), *PRS* 23 (Spring 1996): 255-268. ለዚህና ለሌቹም ጠቃሚ ገለጻ ለማግኘት D.F. Hill, "The Walking on the Water: A Geographical or Linguistic Answer?" *ExpT* 99 (1998): 267-269 ይመለከቷል::



ቢመስልም ኢየሱስ መለኮታዊነቱን በሚመለከት እስካሁን ካደረገው ይልቅ በማያሻማ ሁኔታ የገለጸው በዚህ ጊዜ ነበር (Blomberg p. 235)[13]::

5000 ሰዎችን የመመገቡን ታሪክ ያህል ይህኛውም ታሪክ ማመን እንደሚያስቸግር እንቀበላለን:: ብዙዎች እነዚህን ሁለት ተአምራቶች በተፈጥሯዊ መንገድ ለመግለጽ ሞክረዋል::[14] ይህ ግን አያዋጣም:: ምንባቦቹ ማለት የፈለጉትን በትክክል አስቀምጠዋል:: ነገረ መለኮታዊ ዓላማዎችን ለማስጨበጥ የታለሙ ሥነ ጽሑፋዊ ፈጠራዎች ናቸው ወይም ሆን ብለው የተቀናበሩ ውሸቶች አለዚያም እግዚአብሔር የተፈጥሮን ሕግ መጣሱን የሚያመለክቱ ናቸው:: ክስተቶቹን መቀበል ወይም አለመቀበል አለብን:: የተለየ ገለጻ በማድረግ ለማስተባበል መሞከር ለአእምሮ ታማኝ አለመሆንን ነው የሚያሳየው::

**ማቴ 14፥28-33**

28 ጴጥሮስም፣ «ጌታ ሆይ፣ አንተ ከሆንህስ፣
በውሃው ላይ እየተራመድሁ ወደ አንተ እንድመጣ
እዘዘኝ» አለው:: 29 እርሱም፣ «ና» አለው::

[13] ይሁን እንጂ K.L. McKay, "'I Am' in John's Gospel," *ExpT* 107/10 [1996]: 302-303, ላይ ተገቢ ማስጠንቀቂያ እንደሚያቀርበው በግሪክና በዕራይስጥ «እኔ ነኝ» ከሚሉት ጋር ተመሳሳይ እንደ ሆነ መረዳት ያልተጻፈውን የማንበብ ያህል ይሆናል::

[14] 5000ዎችን መመገቡ በተለምዶ እንደ ልግስና ተአምር ተደርጎ ነው የሚገለጸው:: ያ ትንሽ ልጅ ምሳውን ለኢየሱስ ሲሰጥ ሲያዩ ሕዝቡ ሁሉ የደበቁትን ማውጣት ጀመሩ:: D.F. Robinson 5000ዎቹን መመገቡ አንድምታዊ እንጂ (አሳማኝ ባይሆንም) እውነተኛ ታሪክ አይደለም ይላል ("The Parable of the Loaves," *ATR* [1957]: 107-115. ኢየሱስ በባሕር ላይ መራመዱ ብዙውን ጊዜ እሱ በባሕሩ ዳርቻ እየተራመደ ሳለ ሐዋርያቱ ግን ባሕሩ መሐል ያለ መሰሏቸው እነርሱ ካሰቡት ይልቅ ወደ ዳርቻው እንደተቃረቡ አስበው ነበር የሚል ገለጻ ይሰጠዋል:: J.D.M. Derrett በጣም የተወሳሰበ ተፈጥሮአዊ ገለጻ አቅርቧል:: እንደ እርሱ ከሆነ ኢየሱስ የተራመደው ሰሜናዊ የዮርዳኖስ ወንዝ አሚጥጦ ባሕሩ ውስጥ የጨመረው ደለል ባመጣቸው ጠጠሮች ላይ ነበር ("Why Jesus Walked on the Sea." *NovT* 23/4 [1981]: 330-348). ይሁን እንጂ የጴጥሮስን በባሕር ላይ መራመድ፣ የዓሣ አጥማጆቹ አለማወቅ እንዴት ቶሎ ወደ ባህሩ ዳር መድረሳቸው፣ ባሕሩ ወዲያውኑ ጸጥ ማለቱን፣ ምንባቡ እንደሚለው ነፋሱ እየነፈሰ የነበረው ከደቡብ እንጂ ከሰሜን አለመሆኑን የመሳሰሉትን ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ሳይገልጽ ስለሚያልፋቸው ገለጻው በፍጹም አጥጋቢ አይደለም::

ጴጥሮስም ከጀልባው ወርዶ በውሃው እየተራመደ ወደ ኢየሱስ አመራ:: 30ነገር ግን የነፋሱን ኀይል ባየ ጊዜ ፈራ፤ መስጠምም ሲጀምር፣ «ጌታ ሆይ አድነኝ!» ብሎ ጮኸ::

31ኢየሱስም ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ ያዘውና፣ «አንተ እምነት የጐደለህ ስለምን ተጠራጠርህ?» አለው::

32ጴጥሮስና ኢየሱስ ጀልባው ላይ እንደ ወጡ ነፋሱ ጸጥ አለ:: 33ከዚያም በጀልባው ውስጥ የነበሩት፣ «በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብለው ሰገዱለት::

ማር 6÷51-52

51እነርሱም እጅግ ተደነቁ፤ 52የእንጀራውን ታምር አላስተዋሉም ነበርና ልባቸው ደንድኖ ነበር::

ዮሐ 6÷21

21እነርሱም እንዲሳፈር ፈለጉ፤ ጀልባዋም ወዲያውኑ ወደሚሄዱበት ዳርቻ ደረሰች::

ጴጥሮስ በባሕሩ ላይ ስለ መራመዱ ተጽፎ የምናገኘው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው:: ትረካው ስለ ጴጥሮስ እምነትና ውድቀት ያመለክታል::[15] ችኩል አንዳንዴም ደፋርና ሳያስብ ለመናገር ፈጣን ነው:: ሆኖም እንደዚያም ቢሆን ከኢየሱስ ቀጥሎ በውሃ ላይ የተራመደ እርሱ ነበር::

«አንተ ከሆንህስ» (ቍ 28) የሚለው፣ «አንተ እስከ ሆንህ ድረስ» ቢባል የተሻለ ትርጕም ይሆናል:: ኢየሱስ እንዲመጣ ጋበዘው እርሱም እንዳለው አደረገ:: የሚያሳዝነው ግን በፍጥነት ተዘናግቶ መስጠም ጀመረ::

[15] ብሉምበርግ እንዳስተዋለው ይህ በማቴ 14-18 የጴጥሮስን ሁኔታ ጐላ አድርጐ (ብዙውን ጊዜ ውድቀቱን) ከሚያቀርቡትና የማቴዎስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት ከሆኑት አምስት ቁልፍ ምንባቦች የመጀመሪው ሲሆን የምናገኘው በዚሁ ወንጌል 14÷28-31፤ 15÷15-16፤ 16÷17-19፤ 17÷24-27፤ 18÷21 ነው::



በማቴዎስ 14÷33 እና በማርቆስ 6÷51-52 መካከል ያለው ተቃርኖ ምንኛ ጉልህ ነው! በመጀመሪያ ደረጃ ብዙውን ጊዜ እውነተኛ አምልኮ የኢየሱስን ማንነት ከመረዳት የሚመጣ ፍርሃት ውጤት መሆኑን እናያለን:: በሁለተኛ ደረጃ ረዘም ላለ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር አብረው የነበሩት እንኳ የእርሱን ማንነት በሚገባ አልተረዱም ነበር:: በሦስተኛ ደረጃ፣ በኢየሱስ ድርጊቶች (ለምሳሌ በተአምራቶቹ) ተደነቅን ማለት የግድ ስለ ታምራቶቹ ትክክለኛ ግንዛቤ አለን ማለት እንዳልሆነ እንገነዘባን::

በድንገት ወደ ባህሩ ዳርቻ መጡ:: ይህም ማለት ኢየሱስ በጀልባዋ ሲሳፈር ወደ ዳርቻ እየቀረቡ ነበር ማለት ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ በውሃ ላይ የመራመዱን ምሥጢር ማወቅ እንደማንችል ሁሉ ይህም ከመረዳት ችሎታችን በላይ የሆነ መለኮታዊ፣ «ጉዞ» ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ እኛ ከምንረዳው ጋር ስላልተጣጣመ ብቻ ታሪኩን ችላ ማለት ምን ያህል ትልቅ ሞኝነት ነው:: ምናልባትም፣ «ልባቸው ደንድኖ ነበር» ከተባለላቸው ያላመኑ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ምድብ ውስጥ (አስደንጋጭ ቢሆንም እንደ ኢየሱስ ጠላቶች ሁሉ) ራሳችንን እናገኘው ይሆናል::

§ 75
በጌንሴሬጥ መፈወሱ
(ማቴ 14÷34-36
ማር 6÷53-56)

[ማር 6:]53በተሻገሩም ጊዜ፣ ጌንሴሬጥ ደርሰው ወረዱ፤ ጀልባዋንም እዚያው አቆሙ:: 54ወዲያው እንደ ወረዱም፣ ሕዝቡ ኢየሱስን ዐወቁት፤ 55ወደ አካባቢውም ሁሉ በመሮጥ ሕመምተኞችን በዐልጋ ላይ እየተሸከሙ እርሱ ወደሚገኝበት ስፍራ ሁሉ ያመጡ ነበር:: 56በየደረሰበት መንደር ወይም ከተማ ወይም ገጠር ሁሉ ሕመምተኞችን በየአደባባዩ እያስቀመጡ የልብሱ ጫፍ እንኳ ለመንካት ይለምኑት ነበር፤ የነኩትም ሁሉ ይድኑ ነበር::

ጌንሴሬጥ ከባሕሩ በስተ ምዕራብ ያለ ለም ሜዳ ነው:: ጆሴፈስ፣ «አንድ ሰው ይህን ቦታ እርስ በርስ የሚጻረሩ ዕፅዋት ተስማምተው የሚኖሩበት የፍጥረት ሁሉ ናፍቆት ሊለው ይችላል» ብሏል (*War* 3.518):: በማዕበሉ ጀልባዋ አቅጣጫዋን ቀይራለች:: በመጀመሪያ ወደ ቅፍርናሆም (ዮሐ 6÷17) እንዲያውም በትክክል ለመናገር ከቤተ ሳይዳ ውጪ ወዳለ ቦታ (ማር 6÷45) እያመሩ ነበር:: የባሕር ጉዞ ያስጠላቸው ደቀ መዛሙርት በእግራቸው ከጌንሴሬጥ ወደ ቅፍርናሆም ለመመለስ ወስነው ነበር:: ከቁርስ በኋላ ጀልባዋን ወደ ማረፊያ ቦታዋ እንዲመልሱ የተመደቡ ሁለት ደቀ መዛሙርት ሳይኖሩ አይቀሩም::

ኢየሱስ ታዋቂ ሆኗል፤ ሕዝቡ በዚያ በኩል እንደሚያልፍ ሲሰሙ ዐልጋዎችንና ቃሬዛዎችን በየመንገዱ ዳር ደርድረው የእርሱን በዚያ ማለፍ እየጠበቁ ነበር:: ይህ ሁኔታ የኢየሱስ የፈውስ አገልግሎት በናሙናዊና እጥር ባለ መልኩ የቀረበበት ነው (ማቴ 8÷1-17፤ 9÷18-34፤ ማር 1÷32-34፤ 3÷7-12):: ማቴዎስ ስለ ፈውስ ለመናገር የተጠቀመበት ጠንከር ያለ ቃል (ዲያሶዞ - *diasozo*) ሰዎቹ እንደ ተፈወሱና ጤናቸው በተሟላ ሁኔታ እንደ ተመለሰላቸው ያመለክታል::

ኢየሱስ «የፈውስ አገልግሎት» ለማድረግ ቆም ብሎ፣ ጊዜ አልወሰደም:: ከዚያ ይልቅ ሰዎች በሚያልፍበት ጊዜ እንዲነኩት ነበር የፈቀደው:: በተለመደው የፓለስቲናውያን አለባበስ መሠረት ለጸሎት የሚሆን ዘርፍ ያለበት መጐናጸፊያ ለብሶ ነበር (ዘኍ 15÷37-39፤ ዘዳ 22÷12 ጋር ያነ):: ኃይል ከግለ ሰቡ ወደ ልብሱ በተለይም ለጸሎት የሚሆን ዘርፍ ወዳለበት እንደሚያልፍ በዘመኑ ይታሰብ ነበር:: ደም ይፈሳት ከነበረችው ሴት ታሪክ የተመለከትነው ይህንኑ ልማዳዊ እምነት ነበር (§67፣ ማቴ 9÷20-21፤ ማር 5÷24-34):: የልብሱን ዘርፍ ከነኩ እንደሚፈወሱ ያምኑ ነበር:: ኢየሱስ ቅፍርናሆም በደረሰ ጊዜ በፈውስ



አገልግሎቱ ማግስት እዚያ የቀሩ ሰዎች ረጅም ሰልፍ ሠርተው እየጠበቁት ነበር:: በቅፍርናሆም የነበረው ምኩራብ እንደዚያ ቀን በሰዎች ተጨናንቆ አያውቅም::

**§ 76**
**ስለ የሕይወት እንጀራ የቀረበ ስብከት**
**(ዮሐ 6÷22-59)**

ይህ ለየት ያለ ስብከት ነበር:: ሕዝቡ በርካታ ጥያቄዎች እያቀረበ ነበር፤ ኢየሱስ ከእነዚህ ጥያቄዎች ለአንዳንዶቹ ቀጥተኛ መልስ አልሰጠም:: ከአስመሳይ ግልጽነት ወደ ለየለት ጥላቻ ተሸጋገረዋል:: በዚህ ስብከት ፍጻሜ ኢየሱስ ብዙ ሰባኪዎች በተቻለ መጠን ሊያስወግዷቸው የሚሞክሯቸውን ሁለት የሚሆኑ ነገሮችን አከናውኗል:: የማያምኑ አድማጮቹን ግራ አጋባ፤ በጣም ከሚቀርቡት ወዳጆቹ በስተቀር ሌሎቹ ከእርሱ እንዲለዩ አደረገ:: በአዎንታዊ መልኩ ስንመለከተው፣ (ሀ) ከምድር ወደ ሰማይ ተሸጋገረ (ለ) ለእርሱ የተሰጠ ሕይወት እንዲኖራቸው ግልጽ ያለ ጥሪ አቀረበ (ሐ) ባለፉት ሁለት የአገልግሎት ዓመቶች ካደረገው ይልቅ ስለ ማንነቱ በግልጽ ለመናገር ተቃረበ::

የዚህ ስብከቱ መሪ ሐሳብ፣ «በኢየሱስ የሚገኝ እውነተኛ ሕይወት» የሚል ነበር:: እዚህ ላይ ስለ «ሕይወት» ብዙ ሲናገር እንመለከታለን (ቍ 27:33:35:40:47:48:50:51:53:54:57:58:63):: ኢየሱስ ራሱን እውነተኛና ብቸኛ የዘላለም ሕይወት ምንጭ አድርጐ አቀረበ:: በመዝሙር መካከል እንደሚገባ አዝማች፣ «እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ» የሚለውን ደጋግመን እንሰማለን (ቍ 39:40:44:54):: በዚህ ምንባብ ኢየሱስ ስድስት ጊዜ ከሰማይ መምጣቱን ይናገራል (ቍ 33:38:41:50:51:58 በተጨማሪም ቍ 62 ይመ):: ከዚህ መግለጫ መሪ ሐሳቦቹ አንዱ የኢየሱስ ከሰማይ የመጣ መሆኑን የሚመለከት እንደሆነ ግልጽ ነው (41-42 ጋር ያነ):: መቼም አይሁድ ይህንን አይስቱትም (ከቍ 41-42 ጋር ያነ)

ዮሐ 6፥22-24

[22]በማግሥቱ በባሕሩ ማዶ የቀሩት ሰዎች በዚያ
አንዲት ጀልባ ብቻ እንደ ነበረች ተረዱ፣ ኢየሱስ
እንዳልተሳፈረና ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን እንደ ሄዱም
ዐወቁ። [23]ከዚያም በኋላ፣ ሌሎች ጀልባዎች ከጥብርያዶስ፣ ሕዝቡ ጌታ የባረከውን
እንጀራ ወደ በላበት ስፍራ መጡ። [24]ሰዎቹም ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ
አለመኖራቸውን እንዳወቁ ኢየሱስን ፍለጋ በጀልባዎቹ ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ።

ኢየሱስ ባፈው ሌሊት 5000ዎቹን ካሰናበተ በኋላ ከዚያ አካባቢ ርቀው አልሄዱም። አንዳንዶቹ ምናልባት በአቅራቢያው ባሉ መንደሮች መኝታ አግኝተው ይሆናል። ሌሎቹ ደግሞ ሰብሰብ ብለው በዚያ ምግብ በበሉት ቦታ አቅራቢያ ሳያድሩ አይቀሩም። ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ በትናንትናው ቀን በባህሩ ማዶ አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ክብ ሠርቶ የነበረው ሰልፉ ከጀመረበት ጥብርያዶስን ከመሰለ ሩቅ ቦታ ነበር የሚኖሩት፣[16] በዚያ ሌሊት ወደ እየቤታቸው መድረስ የሚችሉበት መንገድ አልነበረም፤ ስለዚህም እዚያ አድረው ማግሥቱ ይዞት ሊመጣ የሚችለውን ድግስ ለማየት ወስነዋል።

በማግሥቱ ጥዋት እንደ ገና ተሰባስበው ተመለሱ። ጥቂት ወዲያ ወዲህ ብለው ከፈለጉት በኋላ ኢየሱስ እዚያ እንዳልነበረ ዐወቁ። ግን የት ሄዶ ሊሆን ይችላል? በጀልባ ባሕሩን ተሻግሮ እንዳልሄደ ዐውቀዋል፤ ባለፈው ሌሊት የነበረችውን ብቸኛ ጀልባ ደቀ መዛሙርቱ ወስደዋታል ኢየሱስ ደግሞ በዚያች ጀልባ አልተሳፈረም። ከ5000 የሚበልጡ ሰዎች ዙሪያውን ሳሉ ማንም ሳያየው እንዴት ከዚያ ቦታ ሊሰወር ይችላል? ግራ በመጋባታቸው ልንወቅሳቸው አንችልም። ምን እንደ ተፈጠረ ማን በትክክል መገመት ይችላል?

ጀልባዎቹ ከጥብርያዶስ የመጡት ለምንድነው? ምናልባት አንዳንድ ጀብድ ፈላጊ ወጣቶች የደከሙ ወላጆቻቸውን ወደ ቤት ለማምጣት በዚያ ሌሊት ከቤተ ሳይዳ ወደ ጥብርያዶስ በመቅዘፋቸው ሊሆን ይችላል። በማግሥቱ ጠዋት መጓጓዣ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ሰዎች መኖራቸውን ለጎረቤቶቻቸው ሁሉ አውርተው ይሆናል። አንዳንድ ገቢ ማግኛ መንገድ የሚፈልጉ ሰዎችም በዚህ አገልግሎት ለመሳተፍ ፍቃደኞች ሆነው ይሆናል።

ወደ ቤት ለመመለስ ያን ያህል ፍላጎት አልነበራቸውም። እንደ ገና ኢየሱስን ማየት ነበር የፈለጉት። ስለዚህም በባሕሩ መሓል ለመሐል ጥብርያዶስን አቋርጠው ከማለፍ ይልቅ በመጀመሪያ የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከል እንደ ነበረች ወደምትታወቀው ቅፍርናሆም አቀኑ። ኢየሱስን እዚያ ባላገኙት ጊዜ ምዕራባዊ የባሕሩን ዳቻ ተከትለው በየማረፊያ ስፍራው የሚያገኙትን ሰው ሁሉ ኢየሱስን ዐይተው እንደ ሆነ መጠየቅ ጀመሩ።

ዮሐ 6፥25-27

[25]ከባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ፣ «ረቢ መቼ
ወደዚህ መጣህ?» አሉት።
[26]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ የምትፈልጉኝ
እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ፣ ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም።
[27]ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፤ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት
ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማኅተሙን በእርሱ ላይ
አትሞአልና።

---

[16] ኢየሱስ ከጥብርያዶስ ወደ ቤተ ሳይዳ ጁሉያስ ለመሻገሩ በርካታ አመልካቾች አሉን፣ (1) በማግሥቱ ጀልባዎች ከጥብርያዶስ መጥተዋል (ዮሐ 6፥23)። እነዚህ ጀልባዎች ቀደም ባለው ቀን ኢየሱስን ተከትለው መጥተው የነበሩ ዘመዶቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ለመውሰድ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። (2) ኢየሱስ፣ «ራቅ ወዳለው» ዳርቻ ተሻግሮአል (ዮሐ 6፥1)። ጥብርያዶስ ከቤተ ሳይዳ ጁሊያስ ማዶ ነበር የሚገኘው። (3) በቅንብብ (ቅንፍ) ባለ ማሳሰቢያ ዮሐንስ «የገሊላ» ባሕር በመባል የሚታወቀውን፣ «የጥብርያዶስ ባሕር» ብሎታል። (4) በተጨማሪም የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያመቻችለት በመሆኑ ጥብርያዶስ ለኢየሱስ ተገቢ ቦታ ነበር፣ (ሀ) ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲጓዝ ስለ ዋለ አንጻራዊ ጸጥታ ማግኘት የሚችልበት በመሆኑ፣ (ለ) ከገሊላ ጉዞ በኋላ ለመገናኘት መካከለኛ ቦታ በመሆኑ፣ (ሐ) ደቀ መዛሙርቱ ከተመለሱ በኋላ ያን ያህል ብዛት ያለው ሕዝብ ሊኖር የሚችለው እዚያ በመሆኑ (ማር 6፥31)።

ይህ ትረካ አንድ ወጥ ስብከት ይመስላል:: ይሁን እንጂ በጥብርያዶስ አጠገብ ተጀምሮ (ቊ 25) በቅፍርናሆም በነበረው ምኵራብ (ቊ 59)[17] የተጠናቀቀው የቀን ውሎ ውይይት አጭር ማጠቃለያ ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ 5000ዎቹን የመገበው ሐሙስ፣ ውይይቱ የተጀመረው ዐርብ ሲሆን ያበቃው በመደበኛው የምኵራብ አገልግሎት ጊዜ ነበር ብለን መገመት እንችላለን:: ይሁን እንጂ ሰኞና ሐሙስም በምኵራብ ውስጥ አገልግሎት ይሰጥ ነበር:: የፋሲካ በዓል እየተቃረበ ስለ ነበር በምኵራቡ የተለየ አገልግሎት የሚሰጥበት ጊዜ ሊሆን ይችላል::

«መቼ ወደዚህ መጣህ?» በማለት ኢየሱስን ጠየቁት:: መልሱ «ከቀኑ ዐሥር እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት» ነበር የሚል ነው:: ይህን የምንረዳው ከማቴዎስና ከማርቆስ እንጂ ከኢየሱስ አይደለም:: ከልብ ሳልሆነ ጥያቄያቸው መልስ አልሰጠም:: ይልቁንም ልባቸው ውስጥ የነበረውን ዓላማ አቅጣጫ ያስቀይር ነበር:: ኢየሱስ «ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ» ሲል በተለምዶ ከእንስሳት አመጋገብ ጋር የተያያዘ ቃል ነበር የተጠቀመው (ኢኮርታስቴ - *echortasthete*):: ሕዝቡ የሚያስቡት በጣም ሥጋዊ በሆነ ደረጃ - ማለትም እርካታና ዋስትና በማግኘት ፍላጐት ነበር:: ስለ መሲሑ በመናገራቸው መንፈሳዊ እንደ ሆኑ ማሰባቸው ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነበር::

ከዚህ ትረካ የምናገኘው ግልጽ ትምህርት፣ «ከሥጋዊ ጉዳይ ባሻገር አስቡ»የሚለውን ነው:: እነርሱ ግን አልተረዱም:: ሌላው ቀርቶ የኢየሱስን ቃል የተረጐሙበት መንገድ (በምሳሌያዊ መልኩ ሳይሆን ቃል በቃል መውሰዳቸው) ራሱ አሳስቶአቸዋል::

[17] በቅፍርናሆም በነበረው ምኵራብ ፍርስራሽ በወይን ቅጠሎችና እዚህና እዚያ በተበታተኑ ወይኖች ያገጠ የመና መያዣ የመሰለ ማሰሮ በመገኘቱ ሁኔታው የሚገርም ሁኔታ ነው (Edersheim, II:29)::



ኢየሱስ፣ «ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ» ሲል ስለ ሥራቸው መናገሩ ብቻ ሳይሆን እንጀራና ዓሣ የመገባቸው እሱን በመፈለግ ያደርጉት ስለ ነበረው ጥረትም ጭምር መናገሩ ነበር:: ሐቁ እነዚህ ሰዎች ምንም አለመሥራታቸው ነው:: ኢየሱስን ፍለጋ በየገጠሩ ወዲያ ወዲህ እየባዘኑ ነበር:: እርሱን ለማግኘት በትናንትናው ቀን ዐሥር ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘዋል፤ ቀኑን ሙሉ ውለው ሌሊቱን አንድ ላይ ስብስብ ብለው አድረዋል:: በማግሥቱ ጠዋት ከቤተ ሳይዳ ጁሊያስ እስከ ቅፍርናሆም፣ ከዚያም እስከ ጥብርያዶስ ሊያገኙት ፈልገው ተከታትለውታል:: አሁን ደግሞ እንደ ገና እስከ ቅፍርናሆም ተከትለውት ሄደዋል:: ቢያንስ ሁለት «የሥራ» ቀኖች አባክነዋል:: ሆኖም ኢየሱስን መፈለግ «ሥራ» ነው:: እኛም እንድንሠራ የተጠራነው ይህንኑ ነው:: የእነዚህ ሰዎች ችግር ኢየሱስን በተሳሳተ ምክንያት መፈለጋቸው ነው:: ኢየሱስ የመጣው የዘላለም ሕይወት ሊሰጣቸው ሆኖ ሳለ፣ እነርሱ በገብስ እንጀራና በዓሣ ለመወሰን ራሳቸውን አዘጋጅተዋል::

እነዚያ ፈጥነው መረዳት የማይችሉ (ከአብዛኞቹ ሰዎች የተለዩ ባይሆኑም) ገሊላውያን ከኢየሱስ የበለጠ መጠበቅ ነበረባቸው:: እግዚአብሔር ለኢየሱስ፣ «የማረጋገጫ ማኅተሙን» አትሞለታል:: በዚያ ዘመን ማኅተም በቀለበት መልክ በሰም ወይም በሸክላ ላይ የተቀረጸና ቅርጹን እንዲያትም ይደረግ ነበር:: ማኅተም በተለይ ንጉሦችና ገዢዎች ያላቸውን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ይጠቀሙበት የነበረ የሚታይ ምልክት ነበር:: እግዚአብሔር ለኢየሱስ የሰጠው በግልጽ የሚይ ምልክት ምን ነበር?

1. ተአምራትን፣
2. የመጥምቁ ዮሐንስን ምስክርነት፣
3. ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ በርግብ አምሳል ወርዶ በነበረው መንፈስ ቅዱስ፣
4. መሲሐዊ ትንቢቶች (በምሳሌና በቃል የተነገሩትን)፣
5. በኢየሱስ ግልጽ ባሕርይና ትምህርቶች፣

28እነርሱም፣ «ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ዮሐ 6፥28-29
ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?» አሉት።
29ኢየሱስም፣ «እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው»
ሲል መለሰላቸው።

ቁጥር 28፣ «ታዲያ ምን አናድርግ?» የሚል ቀጥተኛ ጥያቄ ይመስላል:: ሆኖም ትረካው ወደ ፊት ከሚገለጸው እንደምንረዳው ሕዝቡ ልባቸውን ከኢየሱስ መልሰዋል:: እነርሱ የፈለጉት ዓይነት ንጉሥ ለመሆን ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ኢየሱስ ምንም ማድረግ በማይችልበት ሁኔታ ልባቸው አዝኗል:: ከዚህ በኋላ እስከ መስቀሉ ድረስ በጣም የሚያሳዝን ሁኔታን ነው የምናየው:: ኢየሱስ ስለ ራሱ ማንነት ይበልጥ ግልጽ ባደረገ መጠን የሰዎቹም ቍጥር እያነሰ ይሄድ ጀመር::

ምንም እንኳ ጥያቄያቸው ጥርጥርን መሠረት ያደረገ ቢሆንም፣ እጅግ መልካም ጥያቄ ነበር:: እንዲያውም፣ የሰው ልጆች ሁሉ ጥያቄ ነው ለማለት እደፍራለሁ:: «የእናንተ ሥራ በእኔ ማመን ነው» በማለት ኢየሱስ የሰጠውም መልስ እንዲሁ መሠረታዊ ነው:: ይህ ሁለት ጥያቄዎችን ያስከትላል:: በመጀመሪያ እምነት ሥራ የሚሆነው እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነትን፣ «መታመን» ብለን ብንረዳው የተሻለ ይሆናል:: አእምሮአችን ከተቀበለው ሕይወታችንም ያንኑ ያሳያል:: ስለሆነም፣ «እምነታችን» በምንኖረው ኑሮ መገለጹ የማይቀር ይሆናል (ያዕ 2፥14-26)::

ሁለተኛው ጥያቄያችን፣ «ሥርተን የምናገኘው እስከ ሆነ ድረስ የዳንነው በጸጋ ነው ማለት እንዴት ይችላል?» መልሱ፣ እንቀበለዋለን እንጂ ሥርተን የምናገኘው አይደለም የሚል ነው:: ድነትን በምንም መልኩ በሥራ አናገኝም:: የቱንም ያህል ጥሩ ሰዎች ብንሆን፣ የቱንም ያህል ትክክለኛ ሕይወት ብንኖር ለራሳችን ኀጢአት ቤዛ ለመሆን ወይም ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚያስገባ ክፍያ ልንከፍል አንችልም:: እንዲህ



ሲባል የክርስቶስን ስጦታ ለመቀበል ምንም አናደርግም ማለት አይደለም:: በመላው አዲስ ኪዳን ከድነት ጋር የተያያዙና ልንፈጽማቸው የሚያስፈልጉን አንዳንድ ነገሮች ተጠቅሰዋል - ንስሐ (ሐሥ 17፥30-31፤ ሉቃ 13፥3:5)፣ ሌሎችን ይቅር ማለት(ማቴ 6፥14-15)፣ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን መመስከር (ማቴ 10፥32-33፤ ሮሜ 10፥9-10)፣ ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላት (ማቴ 12፥36-37) ወዘተ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ «እምነት» በሚል አንድ ቃል መገለጽ ይችላሉ:: ይህም ማለት በእውነት በኢየሱስ የምታመን ከሆነ እነዚህ ሁሉ እንደዚሁ የሚመጡና አስፈላጊ የሆኑ የዚያ እምነት መገለጫ ይሆናሉ ማለት ነው::

መጀመሪያ ላይ ምን ያህል ነገሮችን እንደሚሸፍን እስክንገነዘብ ድረስ በጣም ቀላል ይመስላል:: እውነኛ እምነት ማንኛውንም የሕይወት ገጽታችንን ያስተካክላል:: ያለንን ሁሉ፣ ጊዜያችንን፣ ችሎታዎቻችንን፣ ሀብታችንን ሁሉ ይጠይቃል:: የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ከእኛ የሚጠበቀው፣ «በኢየሱስ መታመን» መሆኑን መጀመሪያ ስንሰማ፣ «ይህ ብቻ ነው?» እንላለን:: ጥቂት ረጋ ብለን ካሰብን በኋላ ደግሞ፣ «ይሄማ ሁሉንም ነው!» እንላለን::

ዮሐ 6፥30-33
30ስለዚህ እንዲህ ብለው ጠየቁት፤ «አይተን
እንድናምንህ ምን ታምራዊ ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ
ትሠራለህ? 31አበው ዘንድ ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው ተብሎ
እንደ ተጻፈ፣ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ::ǁ»
32ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ «እውነት እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ
የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ
ነው፤ 33የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ የሚወርድ፣ ለዓለምም ሕይወትን
የሚሰጥ ነውና።

*ǁ31 ዘፀአት 16፥4፤ ነህምያ 9፥15፤ መዝ 78፥24-25 (በተጨማሪ ዘጸአት 16፥15፤ መዝ 105፥40 ይመ)*

ይህ ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ቢሆንም፣ አዲስ አይደለም:: ከዚህ በፊት አይሁድ ታምራዊ ምልክት እንዲያሳያቸው ሁለት ጊዜ ኢየሱስን ጠይቀው ነበር (ማቴ 12÷38-45፤ ዮሐ 2÷18-23 ጋር ያነ):: በሁለቱም ጊዜያት ከታላቅ ተአምር በኋላ ነበር የጠየቁት:: በሁለቱም ጊዜያት ኢየሱስ ወዲያውኑ ጥያቄያቸውን ባይቀበልም በኋላ ታምራት ማድረጉን ቀጥሏል::

በግዑዝ ነገሮች ማለት በወይኑ፣ በእንጀራው፣ በነፋስና በማዕበል የነበረውን ሥልጣን ሳይጨምር ኢየሱስ ሕሙማን መፈውስን፣ ሙታን ማስነሣትን፣ ለምጻሞችን ማንጻትን፣ አጋንንት ማውጣትን የመሳሰሉ አስገራሚ ታምራትን አድርጐ ነበር:: 5000 ሰዎችን ከመገበ በኋላ በማግሥቱ እንዴት ሌላ ምልክት እንዲያደርግ እንዴት ሊጠይቁት ቻሉ? ቁጥር 31 እዚህና ቀደም ሲል ሁለት ጊዜ አይሁድ ምልክት ሲጠይቁ ለሰጡት ምክንያት ቁልፍ የሆነ ነገር ያቀርባል:: ሙሴ መና እንደ ሰጣቸው ሁሉ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ፈልገዋል::[18] አነጋገራቸው፣ «አንተ ራስህ የሰጠኸን ምድራዊ ምግብ ስለነበር እኛም የተከተልንህ ለምድራዊ ምግብ ነው:: ለሰማያዊ ምግብ እንድንከተልህ ከፈለግህ ግን (ቁ 27) ከሰማይ ምልክት እንድታሳየን እንፈልጋለን» የማለት ያህል ነበር:: ሦስቱንም ጊዜ ኢየሱስ እንደሚያሳያቸው ቃል የገባው ምልክት ትንሣኤን ነበር::

ያቀረቡት ሰበብ ትክክል ይመስላል፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከእነርሱ የሚጠብቀውን ችላ ብሎ ከማለፍ የተሻለ አልነበረም:: የሚፈልጉትን ስለ ሰጣቸው በትናንትናው ቀን ኢየሱስን ንጉሥ ማድረግ

[18] (እነርሱ እንደሚያስቡት) የመላእክት ምግብ የነበረው ያ መና ከላይኛው ብርሃን፣ «ከሰማይ ጠል» የጠለለ (Yoma 75b) - ማንኛውንም ዓይነት ጣዕም የያዘ፣ በሚበላው ሰው ሁኔታና ፍላጐት መሠረት በየትኛውም ዕድሜ ላሉ ሁሉ የሚስማማ [Shem. R. 25], ለሕዝብ ጉሮሮ ግን የሚመር ተአምራዊ ምግብ - መሲሕ በድጋሚ ከሰማይ እንዲያወርድ ይጠብቁ ነበር:: የመጀመሪያው ታዳጊ ሙሴ እንዳደረገ ሁሉ ሁለተኛው መሲሕም እንዲሁ ያደርጋል [Midr.on Eccles. 1:9]" Edresheim, II:29-30).



ፈልገው ነበር:: ዛሬ ግን ኢየሱስ እንዲታዘዙለት ሲጠይቅ ተቃወሙት:: «ስጠን፣ ስጠን፣ ምድራዊውንም ባይሆን ሰማያዊውን ምግብ ስጠን!» በማለት ኢየሱስን እየወተወቱት ነበር:: ኢየሱስ ግን «የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው እንጂ እኔ አይደለሁም፤ ሙሴም አልነበረም:: ለአባቶቻችሁ መና ሰጣቸው፤ ለእናንተ ግን እኔን ሰጣችሁ:: ሰማያዊ እንጀራ እንድሰጣችሁ ትጠይቃላችሁ፤ ያ እንጀራ ግን እኔ ነኝ» በማለት መለሰላቸው:: ኢየሱስን በመቃወማቸው እርሱ እንዲሰጣቸው እየጠየቁ የነበሩትንም ያንኑ ነገር ገፍተውታል::

**ዮሐ 6÷34-36**

34እነርሱም፣ «ጌታ እንግዲያውስ ይህን እንጀራ
ሁልጊዜ ስጠን» አሉት::
35ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ
የሚመጣ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም:: 36ነገር ግን እንደ
ነገርኋችሁ፣ አይታችሁኝም እንኳ አታምኑም::

ይህን ስናነብ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ ስለ ነበረችው ሴት ማሰባችን የማይቀር ነው (ዮሐ 4÷4-14):: ዮሐንስ ሆን ብሎ ይህን ንጽጽር አቅርቧል:: በአንድ በኩል አንድ ተአምር እንኳ ሳትጠይቅ የሕይወት ውሃ በሆነው በኢየሱስ ያመነች ሳምራዊት ሴት አለች:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ ብዙ ተአምራት ካዩ በኋላ እንኳ ያላመኑ፣ የሕይወት እንጀራ የሆነው ኢየሱስን የናቁ አይሁድ አሉ::

ኢየሱስ «የሕይወት እንጀራ» መሆኑን መናገሩ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ «እኔ ነኝ» በማለት ካደረጋቸው ተከታታይ ንግግሮች የመጀመሪያው ነው (8÷12፤ 10÷7:11፤ 11÷25፤ 14÷6፤ 15÷1):: «እያንዳንዱ ቃል ኢየሱስ ከሰዎች መንፈሳዊ ፍላጐት ጋር ያለውን ዝምድና ይወክላሉ ... ሰዎች እርሱ ለሚሰጣቸው ሳይሆን፣ እርሱ

ለእነርሱ ለሚሆንላቸው ነገር ሲሉ እንዲቀበሉት ይፈልጋል (ቴኒ፣ ገጽ 76)::

37እብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤
ወደ እኔ የሚመጣውንም ከቶ ወደ ውጭ
አላወጣውም፤ 38ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ
ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም
ነውና፤ 39የላከኝም ፈቃድ፣ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ
ሳይጠፋብኝ በመጨረሻው እንዳስነሣ ነው:: 40የአባቴ
ፈቃድ ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም
ሕይወት እንዲኖረው ነው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ::

ዮሐ 6÷37-40

ምንባቡ፣ «ዘላለማዊ ዋስትናን» አስመልክቶ አስቸጋሪና ጥንቃቄ የሚያሻው ክርክር ያስነሣል:: ይሁን እንጂ ስለዚያ ለመነጋገር ይህ ስፍራው አይደለም:: በዚህ የምናገኘው ኢየሱስ ምሥጢራዊ በሆነ መንገድ ያቀረበው የጋለ ክርክር እንጂ ነገረ መለኮታዊ ትንታኔ አይደለም:: እንዲህ ሲባል ግን አድማጮቹ ምን ማለቱ እንደ ሆነ እንዲያሰላስሉ ለማድረግ ጠንከር ባለ ሁኔታ መልእክቱን ማቅረቡ እንጂ እርሱን መረዳት አይቻልም ማለት አይደለም:: ስለሆነም ይህን ምንባብ በተመለከተ ጠቃሚ ግንዛቤ እንዲኖረን መልእክቶቹን ማየት ሊኖርብን ነው:: ከዚህም በላይ ኢየሱስ በዮሐንስ 10÷25 ዘላለማዊ ዋስትናን በተመለከተ በግልጽ ይናገራል፤ ሰፋ ባለ ሁኔታ የምንነጋገረው እዚያ ስንደርስ ይሆናል::

በአንዳንድ መልኩ ዘላለማዊ ዋስትናን አስመልክቶ የሚነሣ ውይይት አከራካሪ ነጥብ ነው:: አንድ ሰው ክህደት ውስጥ ቢገባ በዘላለማዊ ዋስትና የማያምኑ ሰዎች፣ «ከኢየሱስ ተለየ» ሊሉ ይችላሉ:: በዘላለማዊ ዋስትና የሚያምኑ ደግሞ፣ «መጀመሪያውኑ አልዳነም ነበር» ወይም፣ «በንስሐ መመለስ ያለበት ኍብላይ ነው» ሊሉ ይችላሉ:: ሁለት ነገሮችን እናስተውል:: በመጀመሪያ ሁለቱም ነገረ መለኮታዊ አቋሞች የሚሰጡት ምላሽ ተመሳሳይ ነው - ሰውየውን ወደ ንስሐ መጥራት:: ስለዚህም በዋነኛነት ደረጃ ይህ ፍልስፍናዊ ልዩነት እንጂ፣ ተጻራራዊ አይደለም:: ሁለተኛ፣ ሁለቱም አቋሞች ሌላው ሰው በክርስቶስ ስላለው ቦታ የራሳቸውን ፍርድ ያሳልፋሉ:: በመሠረቱ «እኔ ራሴ ደኅና መሆኔ አይሰማኝም» የሚሉ በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ይልቁንም፣ ብዙዎቹ «እኔ ደኅና ነኝ፤ የአንተን ግን አላውቅም!» ነው የሚሉት:: ይህ አደገኛ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም መጠንቀቅ አለብን፣ በጐና ትሑትም መሆን አለብን::

ዘላለማዊ ዋስትናን የሚቀበሉ ወገኖች ከሥርዓት ውጪ በመኖር ሲወቀሱ ኖረዋል:: አንዳንዶች አንዴ ኢየሱስን ጌታ አድርገው በመቀበላቸው ለአኗኗራቸው ደንታ የላቸውም የሚል አስተሳሰብ ይዘዋል:: ድነዋል፣ ግን እንደ ፈለጉ ይኖራሉ:: ይህ ፍጹም ውሸት ነው (ገላ 5÷13፣17):: በሌላ በኩል ያሉት ደግሞ ዋስትና ማጣትን እንደሚሰብኩ ይከሰሳሉ:: በእውነትም አንዳንዶች በማያስፈልግ ሁኔታ ዘወትር በክርስቶስ ያላቸውን ስፍራ ይጠራጠራሉ (ከ1ዮሐ 5÷13 ጋር ያነ):: ሁለቱንም ጽንፍ ማስወገድ ይኖርብናል::

አሁን ወደያዝነው ክፍል ከመግባታችን በፊት ስለ ዘላለማዊ ዋስትና ወይም መጥፋት የሚናገሩ ጥቅሶችን ስለምናስተናግድበት መንገድ አንድ ነገር ማለት ይኖርብናል:: መነሻ ነጥባችን መድረሻ መደምደሚያችንን ይወስናል:: ስለ ዘላለማዊ ዋስትና ከሚያመለክቱ ጥቅሶች ከተነሣን[19] ስለ መጥፋት የሚናገሩ ክፍሎችን የተለየ ገለጻ የመስጠት ድምዳሜ ላይ ልንደርስ እንችላለን፤ ከዚያኛውም ወገን

[19] ለምሳሌ፣ መዝ 89÷30-35፤ ዮሐ 4÷14፤ 5÷24፤ 6÷37-40፤ 10÷27-30፤ ሮሜ 8÷29-39፤ 11÷29፤ 14÷4፤ 1ቆሮ 1÷8፤ 2ቆሮ 1÷21-22፤ 5÷4-5፤ ኤፌ 1÷13-14፤ 4÷30፤ ፊል 1÷6፤ 1ተሰ 5÷23-24፤ 2ጢሞ 1÷12፤ 2÷19፤ 4÷18፤ ዕብ 6÷17፤ 7÷25፤ 1ጴጥ 1÷3-5፤ 1ዮሐ 2÷18-19፤ 3÷6፤ 5÷12-13፤ ይሁዳ 24::

እንዲሁ።[20] ቀደም ሲል የያዝነው አቋም መቀበል ከምንፈልገው በላይ መደምደሚያችንን ይወስነዋል። እዚህ ለአንዳንድ እርስ በርስ የሚቃረኑ ለሚመስሉ ነገሮች ስፍራ መስጠት ይኖርብናል፤ ምክንያቱም እያየን ያለነው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰውን ነጻ ፈቃድ ጥምረት ነው፤ ሁለቱም እውነት ናቸው፤ በኀጢአት የወደቀው የሰው አእምሮ ግን ሙሉ በሙሉ ይህን ማጣጣም ይሳነዋል። ስለዚህም ቀና አመለካከት ሊኖረንና እያንዳንዱ ጥቅስ ማለት የፈለገውን እንዲል መፍቀድ ይኖርብናል።

አሁን የጀመርነውን ክፍል እንመልከት። ቍጥር 37ን አስመልክቶ ቴኒ እንዲህ ይላል፡-

> «ሁሉም» (ፓን - pan) የሚለው ተባዕታይና ብዙ ቍጥር ሳይሆን የወልና ነጠላ ቍጥር ሲሆን እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ቁጥጥር ሥር ያደረጋቸው ነገሮችን ሁሉ ይመለከታል (ከዮሐ 5÷19-27 ጋር ያነ)። የእርሱ የሆኑትን ሕዝቦች ሁሉ ይጨምራል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ተሰውሮ ያለው እርስ በርስ የሚቃረን የሚመስል ጉዳይ ብዙዎችን ግራ አጋብቷል። አንድ ሰው እግዚአብሔር አብ ለክርስቶስ እንደ ሰጠው እርግጠኛ መሆን የሚችለው እንዴት ነው? የሚመጣው አፍሮ ለመመለስ ነው? የሰዎችን መዳን እግዚአብሔርን እንደማያስደንቀው ኢየሱስ ግልጽ አድርጐታል። በቃሉና በመንፈሱ ሰዎችን ወደ ራሱ ይጠራል። መምጣት የሚችሉት በእርሱ ጥሪ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ጥሪው በተወሰነ ጊዜ ወይም ስፍራ የተገደበ አይደለም፤ ወይም ለአንድ የተወሰነ ሕዝብ፣ ዘር ወይም የአኗኗር ዓይነት ላላቸው ብቻ አይደለም። ማንም በከንቱ እንዳይመጣ መፍራት የለበትም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ማንንም ለመቀበል እንደማይል አጠንክሮ ተናግሯል (ገጽ 76)።

ቁጥር 39 እና 40 የሚጨርሱት፣ «እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ» በሚል የድል አነጋገር ነው። «ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ» በሚለውና «ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው» በሚለው መካከል ያለውን ተጓዳኝነትም ተመልክተናል። ሁለቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ናቸው። ቍጥር 39 ስለ ውጤቱ ሲናገር ቍጥር 40 ግን ስለ መንገዱ ይናገራል። በኢየሱስ ዋስትና የሚኖረን ወደ እርሱ ስንመለከትና ስናምን ነው።[21] (ሁለቱም ግሦች ቀጣይ ድርጊትን የሚያመለክቱ የአሁን ጊዜ ናቸው)። በሌላ አነጋገር ቀጣይ በሆነ መልኩ መመልከትና በኢየሱስ ማመን አለብን ማለት ነው።

ቍጥር 39 ላይ ያለው፣ «አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ» የሚለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያመለክት እንጂ የተስፋ ቃል አለመሆኑን ማስተዋል ያሻል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሌም ይፈጸማልን? በፍጹም። በኤደን ገነት ወይም በኖኅ፣ በሙሴ ወይም በዳዊት ዘመን እንደዚያ አልነበረም። ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲመጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው

---

[20] ለምሳሌ፣ ኢያሱ 24÷19-20፤ ነህ 1÷7-9፤ መዝ 95÷7-10፤ ማቴ 10÷22፤ 13÷1-9፣18-23፤ 18÷21-35፤ 24÷13፤ ሉቃ 12÷42-46፤ ዮሐ 15÷1-6፤ ሮሜ 11÷20-22፤ 1ቆሮ 9÷24-27፤ 10÷1-13፤ 15÷1-2፤ ገላ 5÷1-4፤ 6÷7-9፤ ቈላ 1÷19-23፤ 1ጢሞ 1÷18-19፤ 4÷1፤ 2ጢሞ 2÷11-13፤ 4÷10፤ ዕብ 3÷1-19፤ 4÷1-13፤ 6÷4-8፤ 10÷26-31፣36-39፤ 12÷15-17፤ 2ጴጥ 2÷20-22፤ ይሁዳ 6፤ ራእ 2÷5፣7፣10፣11፣ 17፣26፤ 3÷5፣12፣21፤ 21÷7።

[21] ብዛት ባላቸው ተጓዳኝ ምንባቦች ከድነት ጋር የተያያዙ ሌሎች ትእዛዞች አሉ። «መመልከት» እና በኢየሱስ፣ «ማመን» አጠቃይ ገለጻዎች ሲሆኑ በእነዚህ ውስጥ ንስሐን (ሐሥ 2÷38፤ 3÷19፤ 17÷30-31፤ ሉቃ 13÷5፤ ራእ 2÷16፣22)፣ መናዘዝ ወይም መመስከርን (ማቴ 10÷32-33፤ ዮሐ 12÷42፤ ሮሜ 10÷9-10፤ 1ዮሐ 2÷23፤ 4÷2፣3፣15)፣ መጠመቅን (ማር 16÷15-16፤ ሐሥ 2÷38፤ ሮሜ 6÷3-5፤ ገላ 3÷27፤ 1ጴጥ 3÷21)፣ ሌሎችን ይቅር ማለትን (ማቴ 6÷14-15፤ 18÷35፤ ኤፌ 4÷32፤ ያዕ 2÷13)፣ የክርስቶስን ስም መጥራትን (ሐሥ 2÷21፤ 22÷16፤ ሮሜ 10÷13)፣ መታዘዝን (ዮሐ 3÷36፤ ዕብ 5÷9፤ 11÷8፤ 1ዮሐ 5÷1-3)፣ መልካም ሥራ/ፍሬ ማፍራትን (ማቴ 7÷21-23፤ ዮሐ 15÷2፤ ያዕ 2÷20-26)፣ ፍቅርን (ገላ 5÷6፤ 1ዮሐ 3÷10-24፤ 4÷7-21)፣ ሌሎችን መርዳትን (ማቴ 25÷31-46፤ 1ዮሐ 3÷17)፣ እስከ ሞት ታማኝ መሆንን (ዮሐ 15÷6፤ ዕብ 3÷6፣12፤ 10÷23-31፣36-39፤ ራእ 2÷10፣26)፣ ወዘተ የመሳሰሉት ሁሉ ይካተታሉ።

(2ጴጥ 3÷9)፣ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያመለክተው እንደዚያ አይሆንም (ማቴ 22÷14፤ ሉቃ 8÷13፤ 13÷23-24፤ ራእ 3÷4):: በተጨማሪም ኢየሱስ፣ «አንድም አልጠፋብኝም» ማለቱ ፍጹማዊ አነጋገር እንዳልነበር እንረዳለን (ከዮሐ 18÷9 ጋር ያነ):: የአስቆሮቱ ይሁዳን «አጥቷል» (ዮሐንስ 17÷12):: ይህ እግዚአብሔር ተስፋ የሚያደርገው እንጂ ስለ ዘላለማዊ ዋስትና የተነገረ አይደለም:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጽሞአልን? አዎን ... ከሉዓላዊነቱ አኳያ ተፈጽሟል:: ይሁን እንጂ በሉዓላዊነቱ ውስጥ ለሰው ነጻ ፈቃድ ስፍራ ሰጥቷል:: ብዙ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔር የማይወደው ውሳኔ ያደርጋሉ::

ዮሐ 6÷41-47

41 አይሁድም፣ «ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ
ነኝ» በማለቱ ያጕረመርሙበት ጀመር:: 42 ደግሞም፣
«ይህ አባቱና እናቱን የምናውቃቸው፣ የዮሴፍ ልጅ
ኢየሱስ አይደለምን? ታዲያ አሁን እንዴት ከሰማይ
ወረድሁ ይላል አሉ::
43 ኢየሱስም መለሰ እንዲህ አላቸው፤ «እርስ
በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ 44 የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር
ማንም ወደ እኔ መምጣት አይችልም፤ እኔም
በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ:: 45 በነቢያትም፣
«ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ» ተብሎ
ተጽፎአል፤ አብን የሚሰማና ከእርሱም የሚማር ሁሉ
ወደ እኔ ይመጣል:: 46 ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነው
በቀር አብን ያየ ማንም የለም፤ አብን ያየው እርሱ
ብቻ ነው:: 47 እውነት እላችኋለሁ፤ የሚያምን ሁሉ
የዘላለም ሕይወት አለው::



ማጉረምረም አለመታመንን የሚያሳይ በመሆኑ እግዚአብሔርን ያሳዝናል:: ሆኖም በሕዝቡ ዘንድ በጣም የተለመደ አጉል ነገር ነበር (ዘፀ 16÷7፤ ዘኍ 14÷27፤ 14÷36፤ 16÷11፤ ዮሐ 6÷41፤ 1ቆሮ 10÷10፤ ያዕ 5÷9):: «ያጉረመረምሁት በሰባኪው/ መምህሩ/ሽማግሌው እንጂ በእግዚአብሔር ላይ አይደለም» በማለት ተገቢ ልናስመስለው እንሞክራለን:: ሆኖም ከነዚህ ምንባቦች እንደምንመለከተው የእግዚአብሔር ሕዝብ እርሱ በመረጣቸው ሰዎች እንጂ በቀጥታ በእግዚአብሔር ላይ አላጉረመረሙም ነበር:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንደ ተፈጸመ አድርጐ ነበር የወሰደው:: እግዚአብሔርና የመሠረተውን ሥልጣን ከተቃወምን ራሱ እግዚአብሔርን መቃወማችን ነው::

በኢየሱስ ላይ ያቀረቡት ማጉረምረም (ቍ 28 ላይ እንዳለው ሁሉ) ቅንነትና ምክንያታዊነት ያለው ቢመስልም መንፈሳዊ አልነበረም:: «ከሰማይ የወረድሁ» የሚለውን በተመለከተ አነጋገሩን ቃል በቃል የመውሰድ ስሕተት ፈጽመዋል:: ቤተ ሰቦቹን እስካወቁ ድረስ፣ በአካል ከሰማይ አለመምጣቱን ያውቃሉ:: የማኅበረ ሰባቸው አካል እንጂ የሰማይ ዜጋ አለመሆኑን ያውቃሉ:: «ሥጋዊ ሲሆን ስለ መቻሉ ሐሳቡ እንኳ አልነበራቸውም::

ኢየሱስ፣ አስመሳይ ለሆነ ጥያቄያቸው መልስ ሳይሰጥ ዋናውን ጉዳይ - ፈቃደኝነትንና ወደ ኢየሱስ የመምጣት ችሎታን አነሣ:: እግዚአብሔር ካልሳበን በቀር ወደ ኢየሱስ መምጣት አንችልም (ቍ 44):: እግዚአብሔር የሚስበን እንዴት ነው? በትምህርቱ በኩል ነው (ቍ 45):: ትምህርቶቹ እንዴት ነው የሚገኙት? ምንባባችን አራት መንገዶችን ያቀርባል:-

(1) *የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት* - ኢየሱስ ከኢሳይያስ 54÷13 መጥቀሱ በቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ጥበብ መኖሩን

ያመለክታል:: በጽሑፍ የሰፈረውን የእግዚአብሔር ቃል ከተማርን ወደ ኢየሱስ ይመራናል (ሉቃ 24÷25-27):: ማሳሰቢያ - እንዲህ ሲባል እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ የሚያዘነብል ልብ ማለት እንጂ ምሑራዊ ዕውቀት ማለት አይደለም (ከዮሐ 5÷39-40፣45-47 ጋር ያነ)::

(2) *በሰዎች ልብ ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ሕግ* - ኢሳይያስ 54÷13 ላይ ያለው ከኤርምያስ 31÷31-34 ጋር በጣም ይስማማል:: በጽሑፍ የሰፈረውን ቃል ከማጥናት ባሻገር መንፈስ ቅዱስ ልባችንን ያነቃቃል (ከ1ቆሮ 2÷10-16 ጋር ያነ፤ በተጨማሪም ዮሐ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷13-14ን ይመ):: በተለይ ደግሞ በሁለት መንገዶች:- (ሀ) የድነታችን ምክንያት በሆነው ኢየሱስ መኖር (1ዮሐ 2÷27፤ 1ቆሮ 2÷12)፣ (ለ) በወደቀው ዓለም እንዴት የእግዚአብሔርን ፍቅር መግለጽ እንደሚቻል በማስተማር (1ተሰ 4÷9)::

(3) *ኢየሱስን መስማት* - ቍጥር 46 የእግዚአብሔርን ባሕርያ እቅድ የሚያውቅ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ያሳስበናል:: ስለዚህ «ከእግዚአብሔር መማር» የምትፈልጉ ከሆነ ኢየሱስን መስማት ይኖርባችኋል (ከዮሐ 14÷26 ጋር ያነ)::

(4) *ወደ ማመን የሚያዘነብል ልብ* - ወደ እምነት የሚያዘነብል ልብ ከሌለን በቀር ወደ ኢየሱስ መምጣት አንችልም:: ያ ማለት ግን ግልብ ሙሆን አለብን ማለት ኣይደለም:: ይልቁንም ዝግጁ አእምሮና ልብ ሊኖረን ይገባል ማለት ነው:: ቍጥር 47 (ከቍ 40 ጋር ያነ) በእውነት ከእግዚአብሔር ለመማር እምነትን እንደ ቅድመ ሁኔታ ይጠይቃል::



ምንም እንኳ ምንባባችን አስቀድሞ ስለ መወሰን የሚናገር ቢመስልም፣ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር በኩል የሚያልቅ አይደለም:: ማቴዎስ 22÷14፣ «የተጠሩት ብዙዎች፣ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸው» በማለቱ አንድ ፍንጭ ያቀርባል:: በምሳሌው መሠረት የተመረጡት እነማን ናቸው (ማቴ 22÷1-14)? ለጥሪው ምላሽ የሰጡት አይደለምን? ካልተጠራ፣ ካልተጋበዘ ወይም በእግዚአብሔር ካልተሳበ በቀር በእርግጥ ማንም ወደ ኢየሱስ መምጣት አይችልም (ከሐሥ 16÷14፤ ኢሳ 6÷9-10 ጋር ያነ):: ይህ ግን ምላሽ ከመስጠት ሰውን ነጻ አያደርግም:: አሁንም ቢሆን ማመን፣ ማጥናት መስማት፣ ምላሽ መስጠትና መታዘዝ ይኖርብናል:: መሠረተ ሐሳቡ፣ ያለ እግዚአብሔር ጥሪ ወደ ኢየሱስ የመምጣት ተስፋ የለንም የሚል ነው:: ይህን ኅብረት የሚጀምረው እርሱ እንጂ እኛ አይደለንም:: በተመሳሳይ ሁኔታ ያለ ፈቃዱና ምርጫው ማንም አይድንም:: ድነት፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በሰው ነጻ ምርጫ መካከል የሚደረግ መቀራረብ ነው::

**ዮሐ 6÷48-59**

48የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ:: 49አባቶቻችሁ
በምድረ በዳ መና በሉ፤ ይሁን እንጂ ሞቱ:: 50ነገር ግን
ሰው እንዳይሞት ይበላው ዘንድ ከሰማይ የሚወርድ
እንጀራ ይህ ነው:: 51ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ማንም ሰው ከዚህ
እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ ይህም እንጀራ፣ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን
የምሰጠው ሥጋዬ ነው::

52አይሁድም፣ «እንበላ ዘንድ ይህ ሰው ሥጋውን እንዴት ሊሰጠን ይችላል?»
እያሉ እርስ በርሳቸው እጥብቀው ይከራከሩ ጀመር::

53ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋውን
ካልበላችሁና ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም:: 54ሥጋዬን የሚበላ፣
ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፤
55ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፤ 56ሥጋዬን የሚበላ፣

ደሜንም የሚጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ። [57]ሕያው አብ እንደ ላከኝ፣ እኔም ከእርሱ የተነሣ በሕይወት እንደምኖር የሚበላኝም እንዲሁ ከእኔ የተነሣ በሕይወት ይኖራል። [58]ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በሉ፤ ሞቱም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ግን ለዘላለም ይኖራል።» [59]ይህን የተናገረው በቅፍርናሆም በምኵራብ እያስተማረ ሳለ ነበር።

የኢየሱስ ቃላት አስደንጋጭ፣ ከዚያም በላይ የሚስቀጡ ነበሩ። ኢየሱስ ደምን ስለ መጠጣትና ሥጋን ስለ መብላት (ትሮጎ - *trogo*) ሲናገር ሁናቴያቸው ሲያጉረመርሙ የመስማት ያህል ነበር። ሕዝቡ ተቀይመዋል፤ እርስ በርስ መከራከርም ጀምረዋል። ምናልባትም፣ ኢየሱስ በመጠኑ ላላ በማለት፣ «የነገርኳችሁን ቃል በቃል አትውሰዱት!» ይላል ብላችሁ ልታስቡ ትችላላችሁ። እርሱ ግን እንደዚያ አላደረገም። እንዲያውም ምሳሌውን የበለጠ አጽንዖት ሰጥቶታል።

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር መሆኑ ግልጽ ነው። ኢየሱስ የሰውን ሥጋ መብላትና ደም መጠጣትን የመሰለ ክፉ ልማድ እያበረታታ አልነበረም (ከዘፍ 9÷4፤ ዘሌ 17÷10-14፤ 1ሳሙ 14÷32-35 ጋር ያነ)። ከልብ እርሱን ስለ መቀበል እየተናገረ ነበር። በእስ ውስጥ ስለ መሆንና የጸባዩ፣ የዓላማውና የባሕርይው ተሳታፊ ስለ መሆን እየተናገረ ነበር። አንደ ሰው፣ «ኢየሱስን የሚበላው» እንዴት ነው? ወደ ኢየሱስ መምጣትና በእርሱ ማመን እንደሆነ ቍጥር 35 ላይ መልሱን ሰጥቷል።[22]

በኢየሱስ ከማመን ባሻገር ይህ ምንባብ ኢየሱስ በእኛ ምትክ እንደሚሞት ይናገራል (ከማር 10÷45፤ ሮሜ 3÷21-26፤ 2ቆሮ 5÷14-

[22] በቍጥር 51 እና 53 *esthio* «መብላት» የሚለው aorist subjunctive አንድ ሰው በመጀመሪያ ክርስቶስን ሲቀበል የሚሆን አንድ አስቀድሞ የተደረገን ቁርጥ ውሳኔ ያመለክታል። ቍጥር 54 እና 56 ላይ ያለው *trogo* «ማላመጥ» የሚለው የአሁን ጊዜ፣ በአማኙ «የሕይወት ልምምድ» የሚሆን ቀጣይ ድርጊትን ያመለክታል።



15፤ ቈላ 2÷13-14፤ 1ጴጥ 1÷18-19፤ 1ዮሐ 2÷2 ጋር ያነ)።[23] ነገር ግን ዮሐንስ ስለ ቅዱስ ቍርባንም እየተናገረ ይሆን? ዮሐንስ 6 የሚናገረው ስለ ቅዱስ ቍርባን ነው ማለቱ ከጊዜው የቀደመ ቢሆንም ወደዚያ እያመለከተ መሆኑ ግን ግልጽ ነው።[24] በኋላኛው ዘመኑ ዮሐንስ በሚጽፍበት ጊዜ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ በብዛት ዘርዝሯል። በሌላ አነጋገር ምንም እንኳ ስለ ራሱ ስለ ኢየሱስ እንጂ ስለ ቅዱስ ቍርባን የሚያመለክት አለመሆኑን ብናውቅም ዮሐንስ 6÷53ን በምናነብበት ጊዜ ሁሉ ስለ ቍርባኑ ማሰባችን የማይቀር ነው።[25] ስለሆነም ዮሐንስ 6 የሚያመለክተው ወደ ፊት ስለሚሆነው የኢየሱስ መስቀል ላይ ውሎ ነው። የጌታ ራት መታሰቢያ የሆነው ምሳሌ ቀድሞ የተፈጸመ የኢየሱስን መስቀል ላይ ውሎ ያመለክታል። ተመሳሳይ የሚሆኑት ሁለቱም አንድ ዓይነት ነገርን የሚያመለክቱ በመሆናቸው ነው።

በእነዚህ ሁለት ነገሮች አማካይነት ድነትና ቅድስናን በመሳሰሉ መለኮታዊ ሥራዎች እንሳተፋለን። ሆኖም የእኛ ተሳትፎ የቍርባኑን ሥርዓት መፈጸም ብቻ አይደለም። ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረት በዕለት ተለት ሕይወታችን እውን የሚሆነው እንዴት እንደምንመላለስ፣

[23] በዚህ ጥቅስ *soma* (ሶማ) ከሚለው ይልቅ *sarx* (ሳርክ) የሚለውን ቃል መጠቀሙ ስለ መሰቀሉ የሚናገር ይመስላል። R.Bailey, "John 6," *Rev. & Expos* 85 (1988):95-98.

[24] ክርክሩን አስከመልክቶ በጥሩ ሁኔታ በአጭሩ የቀረበ ሐሳብ ለማግኘት፣ J.D.G. Dunn, "John 6 - A Eucharistic Discourse?" *NTS* 17 (1971): 328-338 እና J.K. Howard, Passover and Eucharist in the Fourth Gospel," *SJT* 20 (1967):329-337 ይመ።

[25] ለፋሲካው ራት አምስት ምዕራፎች የሰጠው ዮሐንስ፣ ስለ ጌታ ራት ምንም የሚለው የለም። ይህ ጠንከር ባለ ሁኔታ የሚያመለክተው በዚህ ምዕራፍ ስለ ክርስቶስ ሥጋ ለሚናገረው ምትክ መሆኑን ነው። ጥምቀትን (ዮሐ 3÷5)፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን (ዮሐ 7÷38-39፤ 20÷22) በተመለከተም ዮሐንስ እንዲሁ አድርጓል። እንዲያውም አንዳንዶች ዮሐንስ 19÷34 እና ዮሐንስ 5÷5-8 ስለ ቅዱስ ቍርባን የሚያመለክት ፍንጭ ማሳየታቸውን ይናገራሉ።

እንደምንናገር፣ እንደምንኖርና እንደምንወድ፣ እንደምንሠራና እንደምናርፍ የሚጨምር ሲሆን ነው።

**§ 76ለ**
**ሕዝቡ ኢየሱስን ትቶ ሄደ**
**(ዮሐ 6፥60-61)**

[60]ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ይህን ሲሰሙ፣ «ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ ሊቀበለው ይችላል?» አሉ።

[61] ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር ማጉረምረማቸውን ኢየሱስ በገዛ ራሱ ተረድቶ፣ እንዲህ አላቸው፤ «ይህ ሰንቀፋት ይሆንባችኋልን? [62]ታዲያ፣ የሰው ልጅ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ ምን ልትሉ ነው? [63]መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል፤ ሥጋ ግን ምንም አይጠቅምም። እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስም ሕይወትም ነው፤ [64]ይሁን እንጂ ከእናንተ የማያምኑ አንዳንዶች አሉ።» ይህም፣ ኢየሱስ እነማን እንዳላመኑና ማን አሳልፎ እንደሚሰጠው ቀድሞውኑ ያውቅ ስለ ነበር ነው። [65]ቀጥሎም፣ «'ከአብ ካልተሰጠው በቀር፣ ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም' ያልኋችሁ ስለዚህ ነው» አለ።

በዚህ ምዕራፍ ሦስት የተለያዩ ወገኖች ያሉ ይመስላል። የልዩነተ መስመር በጣም ፈዛዛ ነው። ይሁን እንጂ የክርስቶስ የቅርብ ሰዎች የሆኑ ዐሥራ ሁለቱንም ይመለከታል። ይህ ወገን ማንነቱ የለየ ነው። ቀጥሎ ደግሞ፣ ከሞላ ጐደል፣ ትምህርቱን የሚቀበሉና ደቀ መዛሙርት ተብለው የተጠሩ (ቊ 60) ብዙ የኢየሱስ ተከታዮች አሉ። በተጨማሪም፣ በአንደበታቸው ኢየሱስን የሚቃወሙ፣ ዮሐንስ «አይሁድ» የሚላቸው ወገኖችም አሉ (ቊ 41፣52)።

አይሁድ ከኢየሱስ ጋር እንደማይስማሙ ቀደም ሲል ተናግረዋል። አሁን ደግሞ የደቀ መዛሙርቱ ተራ ነው። የሚናገሩት ትክክል ነበር። ከባድ አነጋገር ነበር። ይሁን እንጂ ወደ ፊት የሚያዩት የኢየሱስ የምትክነት ሞትን፣ በአካል መነሣትን፣ ወደ ሰማይ ማረግን (ቊ 52)፣ የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና ሌሎችንም ያህል ከባድ



አልነበረም። በዚህ፣ «ከተሰናከሉ»[26] የኢየሱስ አገልግሎት ጥልቀትና ስፋ ለመረዳት ያላቸው ተስፋ በጣም በጥቂቱ ነው። በሌላ አነጋገር ኢየሱስ፣ «ከሰማይ መጥቻለሁ» ማለቱ የሚያስከፋቸው ከሆነ፣ ወደ ሰማይ ሲወጣ ሲመለከቱ ምን ሊሆኑ ነው? ወደ ሰማይ ማረጉ በዮሐንስ ወንጌል አልተገለጸም፣ ሆኖም በተደጋጋሚ ተነሥቶ ነበር (3፥13፤ 8፥21፤ 14፥3፤ 16፥10፤ 17፥11፤ 20፥17)።

ኢየሱስ የተናገረውን ከማጠፍ ወይም ከማለስለስ ይልቅ፣ እንደማያመቻምች በመለኮታዊው እቅድ የተወሰነ በመሆኑ ጠንከር ባለ አነጋገሩ ገፋበት። አሁን ደግሞ መልእክቱን በሙሉ በማሳጠር በሦስት ጥቅሶች አቅርቧል። በመጀመሪያ፣ ከሥጋ ይልቅ (ምግብና መጠጥ) ቃሉ ውስጥ ወዳለው መንፈስ (ሰማያዊ ምግብ) ሲጠራቸው እንመለከታለን። ሁለተኛው፣ አለማመናቸውን በመቃወም ወደ እምነት ጠራቸው። ቊጥር 64 የቊጥር 70 ተጓዳኝ ነው። ወደ ፊት የአስቈሮቱ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው እንዳወቀ ሁሉ፣ ከደቀ መዛሙርቱም እነማን ትተውት እንደሚሄዱም አውቋል። ሦስተኛው፣ እርሱን ይቀበሉ ዘንድ የእግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራር እንደሚኖር ኢየሱስ አሳስቧቸዋል።

**ዮሐ 6፥66-71**

[66]ከዚህም በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ አልተከተሉትም። [67]ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን፣ «እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ?» አላቸው።

[68]ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ «ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ [69]አንተ አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆንህ አምነናል፤ ዐውቀናልም።»

[26] ይህ «ማሰናከል» (*skandalizo*) የሚለው ቃል በቃል ትርጒም ነው።

70 ኢየሱስም መልሶ፣ «ዐሥራ ሁለታችሁንም የመረጥኋችሁ እኔ አይደለሁምን? ነገር ግን ከእናንተ አንዱ ዲያብሎስ ነው» አላቸው:: 71 የአስቆሮቱ የስምዖን ልጅ ይሁዳ፣ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ቢሆንም፣ ኋላ አሳልፎ ስለሚሰጠው ስለ እርሱ መናገሩ ነበር::

የቍጥር 66ቱ የግሪክ ቃል ከአማርኛው ትርጒም ይበልጥ በጣም ግልጽ ነው:: በመጀመሪያ፣ «ከዚህም በኋላ» [*ek toutou*] የሚለው የሚያመለክተው ይህን ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ይህን ሁኔታ ጭምር ነው:: ከዚህ ስብከት የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ትተውታል:: ሁለተኛ፣ «ወደ ኋላ ተመለሱ» የሚለው የአዲሱ መደበኛ ትርጒም፣ «ወደ ኋላቸው ወደ ተዉት ነገር» [*eis ta opiso*] የሚለውን ሐረግ ሳይተረጒም ትቶታል:: በሌላ አነጋገር ወደ ቤታቸው፣ ወደ ሥራቸው፣ ወደ ቀድሞ ልማዳቸው፣ ወደ ቀድሞ አስተሳሰባቸው፣ ወዘተ ተመልሰዋል:: የተውት እርሱን መከተል ብቻ ሳይሆን እርሱ የወከለውንና ያስተማረውን ጭምር ነበር:: ለመንግሥቱ የሚገቡ አልሆኑም (ሉቃ 9÷62)::

ምናልባትም ይህ፣ ከስብከቶቹ ሁሉ፣ «ያልተዋጣለት» ይሆናል:: ኢየሱስ በሺዎች ጀምሮ እጥፍ በሆኑት ፈጽሟል:: ይሁን እንጂ፣ በኢየሱስ አገልግሎት፣ አዲስ ነገር የተጀመረበት ሁኔታ ነበር:: ቍጥር 67 ላይ ኢየሱስ ጥያቄውን ያቀረበው አሉታዊ መልስ እንደሚጠብቅ ሆኖ ነበር:: እንዲሄዱ ጥሪ ማቅረቡ ሳይሆን፣ ለምን ከእርሱ ጋር መቅረትን እንደመረጡ የሚያሳስብ ነበር::

እንደ ተለመደው ሌሎችን ወክሎ መልሶ የሰጠ ጴጥሮስ ነበር:: «እኛ በማለት አጠንክሮ መናገሩ በዐሥራ ሁለቱና ከኢየሱስ በተለዩት መካከል ንጽጽርን ያሳያል» (Tenney, p. 80):: ምንኛ የሚገርም መልስ ነው! ምናልባት ጴጥሮስ የዚህን ስብከት ሙሉ ፋይዳ አልተረዳ ይሆናል፤ ዋናውን ነጥብ ግን አግኝቷል፤ ያም ሕይወት የሚገኘው በኢየሱስ ቃል ውስጥ መሆኑ ነው::



ጴጥሮስ አስደናቂ ምስክርነቱን ቀጥሏል (ቍ 69):: «አምነናል፤ ዐውቀናልም» የሚሉ ሁለት ግሦች የአሁን ጊዜን በሚያመለክት ሁኔታ ቢተረጐሙም፣ ሁለቱም ኀላፊ ጊዜን ነው የሚያመለክቱት:: «እኛ አምነናል፣ ወደ ማወቅም ደርሰናል» በሚል መልኩ ልንረዳው ይገባል:: ለጴጥሮስና ለሌሎች ይህ ያበቃለት ጉዳይ ነው:: ኢየሱስን ለመከተል ወስነዋል:: የሚያንሰራራ እምነታቸው ከእንግዲህ ወሰድ መለስ ለሚል የብዙኃን አስተሳሰብ ስፍራ አይሰጥም::

ጴጥሮስ ኢየሱስን፣ የእግዚአብሔር «ቅዱስ» እስከ ማለት ድረስ ርቆ ሄዷል፤ ይህ ሐረግ ኢሳይያስ የሚያዘወትረው ነው (ሃያ ስባት ጊዜ ተጠቅሞበታል):: አዲስ ኪዳን ውስጥ ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሷል፤ ሦስቱ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሲሆን (ሐሥ 2÷27፤ 3÷14፤ 13÷35) አንዱ የተናገረው ጋኔን ነበር (ማር 1÷24፤ ሉቃ 4÷34):: ይህ በሦስቱ ወንጌሎች ከሚገኙ ሌሎች የጴጥሮስ ምስክርነቶች ጋር የሚስተካከል ኢየሱስን በተመለከተ ከተሰነዘሩ ከፍ ያሉ ምስክርነቶች አንዱ ነው (ማቴ 16÷16፤ ማር 8÷29፤ ሉቃ 9÷20)::

ሁሉም ጥሩዎች አይሆኑም፤ በዐሥራ ሁለቱ መካከል እንኳ ሁሉም ጥሩዎች አልነበሩም:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር አስቀድሞ የማወቅ ችሎታ ስላለው ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቅ ነበር:: አንዳንዶች ከይሁዳ የመጣ ብቸኛ ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን መገለል ይሰማው እንደ ነበር ገምተዋል (ቄሪዮት በኔጌብ ካለችው ኬብሮን በስተ ደቡብ ነበረች)::[27] ይሁን እንጂ ገንዘብ ያዥ የነበረው ይሁዳ በሌሎች የሚገለል ነበር ብሎ ማሰብ ይከብዳል::

---

[27] "Judas Iscariot," *HibJ* 9 (1911): 529-544 ላይ W.B.Smith እንደሚለው «አስቆሮቱ» የሚለው ከቂርያት ከተማ የተገኘ ሥርወ ቃል ነው ማለት አጠራጣሪ መሆኑን አመልክቷል:: «አስቆሮቱ» የሚለው ቃል ትርጒም፣ «ከሃዲ» ማለት ነው ቢባል ይበልጥ የተሻለ ይሆናል::

ሌላ እርስ በርስ የሚቃረን የሚመስለው ደግሞ በታላቁ ሐዋርያ በጴጥሮስና በከሃዲው ይሁዳ[28] መካከል የቀረበው ንጽጽር ነው:: ሁለቱም ከሰይጣን ጋር ተያይዘው ተጠርተው ነበር (ማቴ 16÷23 እና ዮሐ 6÷70፤ በ2ጢሞ 3÷3 እና ቲቶ 2÷3 «ከሳሽ» ተብሎ ተጠርቷል)፤ ሁለቱም ተሰሚነት ያላቸው መሪዎች ነበሩ (ዮሐ 6÷68 እና ሌሎች፣ እንዲሁም ዮሐ 12÷4-6)፤ ሁለቱም ክርስቶስን ክደዋል (ዮሐ 6÷71 እና ማቴ 26÷31-35):: የጴጥሮስን ተነሳሺነትና ቅንዓት ግምት ውስጥ አለማስገባት አግባብ አይሆንም፤ የይሁዳን ታማኝነት እንዳልነበር መቊጠርም ተገቢ አይሆንም:: ይሁን እንጂ በእነዚህ ሁለቱ መካከል የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እጅ ጉልህ ልዩነት ማድረጉን እንዴት መካድ ይቻላል:: ኩሩው ሰባኪ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ከመምጣቱ በፊት የመረጠው እግዚአብሔር መሆኑን ማስታወስ ይኖርበታል (ቊ 70)::

### §77 የመንጻት ሥርዓትን በተመለከተ የተነሣ አለመግባባት (ማቴ 15÷1-20፤ ማር 7÷1-23፤ ዮሐ 7÷1)

[ዮሐ7][1]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ፣ በዚያ የነበሩት አይሁድ ሊገድሉት ስለ ፈለጉ፣ በይሁዳ አውራጃ መዘዋወር ትቶ በገሊላ ተዘዋወረ::

የ5000ዎቹ መመገብና ስለ የሕይወት እንጀራ የቀረበው ስብከት ከፍተኛ ቊጣ አስነስቷል:: እንዲያውም ኢየሱስ በመገባቸው ሰዎች በኩል ያ ቊጣ ኢየሩሳሌም ደርሶ ነበር:: ለፋሲካ በዓል ኢየሩሳሌም ሲደርሱ፣ የኢየሱስ የገሊላ አገልግሎት ዋናው መወያያ ርእስ ሆኖ ነበር:: ፈሪሳውያን ወሬውን ሲሰሙ፣ ይህ እያቆጠቆጠ ያለ ከኢየሱስ ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴ ምን ማለት እንደ ሆነ ሁኔታውን የሚያጣሩ መልእክተኞች ላኩ:: በኢየሱስ ስብከት ውስጥ እንደ ተሰነዘረ የሰሙት የእምነት ማጉደል ቃል ስላናደዳቸው ሊገድሉት ተዘጋጅተዋል (ከማር 3÷6 ጋር ያነ):: የመጡት ብዙዎቹ ደቀ መዛሙርት ከተለዩት በኋላና ለጥቃት በተጋለጠበት ጊዜ ነበር:: ስለዚህ ድንበር አቋርጦ ወደ ፊንቃና ፊልጶስ ቂሣርያ የሚሸሽበት ጊዜ ከመምጣቱ በፊት ኢየሱስ ድጋሚ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ገሊላ ሄደ (ዮሐ 7፥1)::

ማር 7÷1-4

[1]ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም የመጡ አንዳንድ ጸሐፍት በዙሪያው ተሰበሰቡ፤ [2]ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ ባልነጻ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ፤ [3]ፈሪሳውያንና አይሁድ ሁሉ የአባቶችን ወግ ስለሚጠብቁ ሲሉ፣ በሥርዐቱ መሠረት እጃቸውን በጥንቃቄ ሳይታጠቡ አይበሉም ነበርና:: [4]ከገበያ ሲመለሱም ታጥበው ራሳቸውን ካላነጹ በስተቀር አይበሉም ነበር:: እንዲሁም ዋንጫን፣ ማሰሮን፣ ሳሕንና ዐልጋን እንደ ማጠብ ያሉትን ሌሎችን ወጐች ይጠብቁ ነበር::

በዚህ ጉዞ ከኢየሩሳሌም ከፈሪሳውያን የተላኩ ሰዎች ከኢየሱስ ጋር ተገናኙ:: ከትውፊቱ የወጣ ነገር በማድረጉም ድጋሚ ተቃወሙት (ከ47-48፤ ማቴ 9÷9-17፤ ማር 2÷13-22፤ ሉቃ 5÷27-39 ጋር ያነ):: «ባልነጻ» [ኮይኖስ - *koinos*] እጅ በመብላታቸው ደቀ መዛሙርቱን ነቀፉ (ከማር 7÷15፣18፣20፣23 ጋር ያነ):: በደፈናው ቃሉ፣ «ተራ» ማለት ሲሆን፣ እዚህ ላይ ግን፣ «ያልነጻ» በመባሉ በትክክል ተተርጉሟል (ከሐሥ 10÷14፣28፤ 11÷8፤ ራእ 21÷27 ጋር ያነ):: ጉዳዩ ጤና ነክ ሳይሆን ከሥርዐት ጋር የተያያዘ እንደ ነበር ግልጽ ነው:: እጆቻቸው በዚህ ሥርዐታዊ ሕግ አልነጹም ነበር::[29]

[28] ምንጊዜም ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ከመስጠት ጋር ይያያዛል (ከማቴ 10÷4፤ ማር 3÷19፤ ሉቃ 6÷16፤ ዮሐ 12÷4፤ 18÷2 ጋር ያነ)::

[29] *Baptizo* - (ባፕታይዞ) ቃል በቃል ማስጠም ማለት ነው:: «ከአሕዛብ ጋር የሚደረግ ንክኪ፣ ሌላው ቀርቶ ልብሱን መንካት እንኳ ቢሆን ሊያረክስ ይችላል፤ እውነተኛ አይሁድ ከገበያ በሚመለስበት ጊዜ ሁሉ ውሃ ውስጥ መከተት ነበረበት» (Edersheim, II:15)::

የአይሁድ ባሕል ሕፅበትን አስመልክቶ ምናልባት ዘሌዋውያን 15፥11 ላይ የተመሠረቱ አያሌ ደንቦችና መመሪያዎች ነበሩት:: እንዲያውም ሚሽናሕ ውስጥ ያለው ያዲም («እጆች») ሥርዐታዊ የሕፅበት ደንቦችን በያዙ መመሪያዎች የተሞላ ነው:: ከእያንዳንዱ መብል በፊት (አንዳንድ የአይሁድ መምህራን እንደ ጨመሩት ከምግብ በኋላ እንኳ) ማነኛውም ሰው እጁ ላይ የተወሰነ የውሃ መጠን እንዲያፈስስ ይጠየቅ ነበር::

ይህን ወግ በተመለከተ ኤደርሼይም ሰፋ ያለ ገለጻ አቅርቧል (II:11-12)፤

> ውሃው ከማንኛውም ነገር የነጹ እንዲሆኑ ሁለቱም እጆች ላይ ይፈስሳል:: ውሃው ወደ እንጓዎች መውረድ እንዲችል እጆች ወደ ላይ ቀጥ ማለት ነበረባቸው፣ እንዲህ የሚደረገው ከእጅ የሚወርድ ውሃ መልሶ ጣቶችን እንዳያረክስ በማሰብ ነበር:: በተመሳሳይ ሁኔታ እያንዳንዱ እጅ ውሃ በያዘ ሌላው እጅ (እጁ እንደ ተጨበጠ ሆኖ) መታሸት ነበረበት፤ ያ ካልተቻለ ራስ ላይ፣ ሌላው ቀርቶ ግድግዳ ላይ እንኳ መጠረግ አለበት:: እጆቹ «ከረከሱ» ሁለት ጊዜ ውሃ የማፍሰስ ሥርዐት ይደረግ ነበር፤ የመጀመሪያው ወይም፣ «የመጀመሪያው ውሃ» (*mayim rishonim*) ርኩሰቱን ለማስወገድ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ «ከውሃ በኋላ» የእጁ ርኩሰት ያረፈበትን ውሃ የሚያስወግድ ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ በመጀመሪያው መታጠብ ጊዜ እጆች ቀጥ ማለት አለባቸው:: ውሃው ወደ እንጓዎች መውረድ አለበት፤ በሁለተኛው መታጠብ ግን ወደ እጅ ጣቶች ጫፍ እንዲዘልቅ እጆች ቁልቁል መደረግ ነበረባቸው::

ችግሩ ይን *pygme* የተሰኘ ያልተለመደ ቃል ላይ ሲሆን፣ «ጭብጦ» ወይም «እንጓ» ማለት ሊሆን ይችላል::[31] ሕፅበቱ ሁሉንም ያዳረሰ መሆኑን ለመግለጽ (እስከ እንጓ) የሚጠቀሙበት ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ ጉዳዩ ግልጽ ነው፤ እነዚህ ሰዎች የሕፅበት ሥርዐትን ለመጠበቅ በጣም ጠንቃቃ ነበሩ::

በጣም በሚያሳዝን መልኩ ሥርዐታቸው ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ይበልጥ አስፈላጊ ሆኖባቸው ነበር:: ይህ ምንም ያህል አታካች ቢመስልም ያልተለመደ አልነበረም:: ምንጊዜም ቢሆን ሃይማኖት ከእግዚአብሔር መገለጥ ይልቅ ወደ ሰው አተረጓጎም ያደላል (የጳጳስ ትእዛዝ፣ የቤተ እምነት ቀኖና፣ ኅዳግ ላይ የሰፈሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች፣ ወዘተ):: ዓላማው እግዚአብሔርን መዳፈር አይደለም:: ይልቁንም፣ የአንድን ታላቅ ምሑር አተረጓጎም ከተከተልን፣ የእግዚአብሔርን መገለጽ እየተከተልን እንደሆነ ማሰባችን ነው:: ብዙ ጊዜ ግን ሐቁ ይህ አይደለም::

ማር 7፥5-8
ማቴ 15፥2 ጋር

5ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ «ደቀ መዛሙርትህ
እንደ አባቶች ወግ በመኖር ፈንታ ባልታጠበ እጃቸው
ለምን እንጀራ ይበላሉ? ብለው ጠየቁት:: [ምግብ ሲበሉ
እጃቸውን አይታጠቡምማቴ]::

6እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «ኢሳይያስ ስለ
እናንተ፣ ስለ ግብዞች በትክክል ተንብዮአል፤ እንዲ ተብሎ
ተጽፏልና፣

«ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤
7በከንቱ ያመልከኛል፤ ትምህርታቸውም ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው፡
8የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ የሰዎችን ወግና ሥርዐት ታጠብቃላችሁ::

[31] S.M Reynolds, "PUGME" (Mk 7:3) as 'Cupped Hand,' *JBL* 85 (1966):87-88 ላይ እንደሚለው *pugme* የሚለው በዋንጫ ቅርጽ እንዲሆን የተደረገ እጅን የሚያመለክት መሆኑን መረዳት አለብን:: በዚህ ሁኔታ የውስጡም ሆነ የውጭው የእጅ አካል በጥቂት ውሃ ለማጠብ ያስችላል:: ይህ ዐይነቱ ሥርዐታዊ ሕፅበት በአሁን ዘመን ያሉ የአይሁድ ማኅበሮች ከምግብ በፊት ሲታጠቡ የሚያደርጉት ነው::

ፈሪሳውያን ሕዝቡ ላይ ጫና አሳርፈዋል:: እነዚህ ሰዎች ታላላቅ ሃይማኖተኞች እንደ ሆኑ ይታሰቡ ነበር:: ስለዚህም የተከታዮቹን ምግባር በተመለከተ ከኢየሱስ ጋር በሚያነሱት ክርክር ሕዝቡ ይደግፋቸዋል:: ትኩረታቸው እነርሱ ላይ በመሆኑ ደቀ መዛሙርቱ ይረበሻሉ:: ሃይማኖታዊ ፍልሚያው ይህን ይመስላል:: ኢየሱስ ግን ለሚሰነዘረው ተግዳሮተ ሁሉ ተዘጋጅቶል:: እንደ ተለመደው ለጥያቄያቸው ቀጥተኛ መልስ አልሰጠም፤ ሆኖም ወደ ትክክለኛው ጉዳይ መጥቷል::

ወጉን በመተላለፍ በቀረበባቸው ክስ መሠረት በደለኞች በመሆናቸው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አልተከራከረም:: ከዚያም በላይ ያንን የተማሩት ከኢየሱስ ነበር (ከሉቃ 11÷38 ጋር ያነ):: ይልቁንም ኢየሱስ ፈሪሳውያን ላይ የተቆጣው ከሁለት አቅጣጫዎች ነበር:: በመጀመሪያ፣ ግብዞች አላቸው:: ቃሉ ግሪኮች የመድረክ ላይ እንቅስቃሴን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው:: ተዋናዩ የሌላውን ገጸ ባሕርይ ድርሻ ሲጫወት እውነተኛ ማንነቱን በጭንብል ይሸፍናል:: ኢየሱስ ፈሪሳውያኑን ባለ ሁለት ገጽታዎች እያላቸው ነበር:: እግዚአብሔርን የሚያከብሩ የሚያስመስላቸውን ጭንብል ቢያጠልቁም፣ እውነተኛ ዓላማቸው ራሳቸውን መጥቀም ነበር:: ሁለተኛ፣ ኢየሱስ ኢሳይያስ 29÷13ን በመጥቀስ በቀጥታ ከእነርሱ ጋር አያይዞታል (ከሆሴ 6÷6 ጋር በማቴ 9÷13 እና 12÷7 በተጠቀሰው መሠረት ያነ):: ትክክለኛ ነገርን ይናገራሉ፤ ሆኖም የሚናገሩት ለተሳሳተ ምክንያት ነበር:: ልባቸው እግዚአብሔርን ወደ መውደድ ያዘነበለ አልነበረም:: ስለዚህም አምልኮአቸው ዋጋ ቢስ፣ ትምህርታቸውም ከንቱ ነው::

ማር 7÷9-13
ከማቴ 15÷4-6
ጋር

9ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ «የራሳችሁን ወግ
ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የምትተዉበት
ዘዴ አላችሁ:: 10ሙሴ፣ [እግዚአብሔር[ግ+]] አባትና እናትህን
አክብር፤ አባቱ ወይም እናቱን የሚሳደብ ፈጽሞ ይሙት
ብሎ ነበርና፤ 11እናንተ ግን አንድ ሰው አባቱን ወይም እናቱን፣ ከእኔ ማግኘት
የሚገባችሁን ርዳታ ሁሉ ቍርባን ይኸውም መባ አድርጌአለሁ ቢላቸው፣ [አባቱ ወይም
እናቱ አክብሮል[ግ+]] 12እናንተም ይህ ሰው ለአባቱም ሆነ ለእናቱ ከዚህ በኋላ ምንም
ነገር እንዲያደርግ አትፈቅዱለትም:: 13ስለዚህ ለትውልድ በምታስተላልፉት ወግ
የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ ይህን የመሰለም ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ!»

የሰዎችን ወግ ለመጠበቅ ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል ችላ በማለታቸው ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ወቅሶአቸው ነበር:: አሁን ደግሞ፣ ጉዳዩን በምሳሌ እያሳየ ነው:: ወላጆችን ስለ ማክበር የተሰጠው ትእዛዝ ለአይሁድ (ለእግዚአብሔርም ጭምር) ቅድሚያ የሚሰጠው ነው:: በጣም ከባድ ግዴታ በመሆኑ ይህን የሚተላለፍ ሁሉ በሞት መቀጣት ነበረበት (ዘዳ 21÷18-21)::

ቍርባን (Corban) የተሰኘው «የንጉሡ» በቃል ከሚተላለፉ ወጐች አንዱ ነበር (ለምሳሌ *m. Ned.* 1:2-4; 9:7)::[32] አንድ ነገር ቍርባን ነው ከተባለ ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ ቃል ተገብቷል ማለት ነው፤ ወዲያውኑ ባይከፈል እንኳ በሞት ጊዜ መከፈል አለበት:: ሠረገላ፣ ወይም ቤት ወይም ጥሪት ወይም ንብረት ወይም ሌላም ነገር ሊሆን ይችላል:: ቍርባን እስከ ሆነ ወላጆችን እንኳ ጨምሮ ለማንም አይሰጥም:: ሆኖም ባለቤቱ ሊጠቀምበት ይችላል:: ባለቤቱ ሲሞት ግን ለእግዚአብሔር ይሰጣል ወይም ከዚያ የሚገኘው ገቢ ለእግዚአብሔር ይሰጣል::

ቍርባን ትክክለኛ ነገረ መለኮታዊ መሠረት አለው፤ ለእግዚአብሔር የተገባ ግዴታ፣ ለወላጆች ወይም ለማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ከሚኖርብን ግዴታ ይበልጣል:: ይሁን እንጂ ለተሳሳተ ጉዳይ

[32] See J.D.M. Derrett, *"KORBAN, HO ESTIN DORON."* *NTS* 16 (1969-70): 364-368; and J.A. Fitzmyer, "The Aramaic Qorban Inscription from Jebel Hallet Et-Turi and Mk 7:11/Mt 15:5," *JBL* 78 (1959): 60-65.

የመጠቀም ዕድል ሊኖር እንደሚችል ግልጽ ነው:: ለእናንተ የሚስፈልግ አንድ ነገር ካለኝ ቍርባን የሚል ስም እሰጠዋለሁ:: ከዚያ በኋላ እናንተ ባትጠቀሙበትም እኔ ግን እጠቀምበታለሁ::

ሥርዐታዊ ሕፅበትን ስለማንፈጽም ወይም «ቍርባን» በሚለው ቃል ስለማንጠቀም፣ ወደ ፈሪሳውያን በመጠቆም ይህን ክፍል ለመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ሰዎች ብቻ ብንተወው እንደሚሻል እናስባለን:: ይሁን እንጂ ክፍሉ የሚናገረው ንጽሕናን ስለ መጠበቅና ስለ ቍርባን ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሃይማኖታዊ ተግባሮች ስለ መተካት ጭምር ነው:: ይህ ደግሞ ሰፋ ያለ አንድምታ አለው:: ከግርዘት ሥርዐት ሌላ፣ አይሁድ እንደ ወገን የሚቈጠሩትና የሚመዘኑት ሦስት መስፈርቶችን በማሟላት ነው፣ (ሀ) ሰንበትንና በዓላትን (ቀኖች) ማክበር፣ (ለ) ንጹሕና ንጹሕ ያልሆኑ ምግቦችን በደንብ መጠበቅ፣ (ሐ) ሥርዐታዊ አለባበስ:: እነዚህን ሦስት ነገሮች በጥንቃቄ ከጠበቃችሁ፣ እንደ «እውነተኛ አይሁድ» ትቈጠራላችሁ:: አንዱን ወይም ሌላውን ካፈረሳችሁ ግን እውነተኛ አይደላችሁም::

እንደ ክርስቲያኖች፣ ማድረግ ያለብንና የሌለብን ነገሮች ዝርዝር በጣም ተመሳሳይ ነው፣ «እውነተኛ ክርስቲያንን» የምንለየው:-

(ሀ) ቀን:- ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድና በአገልግሎት መሳተፍ በተለይ፣ በእሑድ ጥዋት አምልኮ፣ እሑድ ትምህርት ቤት፣ እሑድና ረቡዕ ምሽት ፕሮግራም ላይ መገኘት:: በኅብረት ማዕድ መቍረስ ቢጠበቅም፣ በግል ምርጫ ይወሰናል::

(ለ) አመጋገብ:- አልኮል አለመጠጣት፣ ሲጋራ አለማጨስና መጥፎ ፊልሞችን አለማየት:: የስፖርት መኪናዎችን አለመንዳትና ኬብል ቴሌቪዥኖችን አለመጠቀም ቢመከርም በግል ምርጫ ይወሰናል::



(ሐ) አለባበስ:- በሚገባ መልበስ፣ ጥቁር ካናቴራ አለመልበስ፣ ወንዶች የጆሮ ጌጥ ማድረግና ደማቅ ልብስ መልበስ የለባቸውም:: «ኢየሱስ ያድናል» የሚል ጽሑፍ ያለበት ካናቴራና በአምልኮ ቀን ደግሞ ሙሉ ልብስ እንዲለብስ ይጠበቃል::

ምናልባት አንዳንዶቻችን ዝርዝሩ ውስጥ ያለ አንድ ነገር እናይና፣ «ይኸኛው እኔን አያሳስበኝም» እንል ይሆናል:: ሆኖም ዝርዝሩ ከአንድ ነገር ወይም ከግለ ሰብ ግምገማ ያለፈ ነው:: እነዚህ ነገሮች የቤተ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ፣ የማኅበረ ሰቦችም ጭምር በጽሑፍ ያልሰፈሩ ደንቦች (ባሕሎች) ናቸው:: እነዚህ የክርስቲያኖችን ማንነት ለመመዘን ያለንበት ባሕል የሚጠቀምባቸው መለኪያዎች ናቸው:: ኢየሱስ፣ መለኪያዎቹ በራሳቸው መጥፎ ባይሆኑም፣ መጥፎ ሰዎችም ግን እነዚህን መልካም ዝርዝሮች በጥንቃቄ መጠበቅ ስለሚችሉ፣ ኢየሱስ የአይሁድን መለኪያ እንደ ተቃወመ ሁሉ ይህንንም ተቃውሞአል:: ውጤቱ መጥፎ ሰዎች ጥሩ መስለው መታየታቸው በሂደት ግን ይበልጥ መጥፎ መሆናቸው ነው::

ይበልጥ መጥፎ የሚሆኑት ለምንድን ነው? ምክንያቱም፣ የሰውን መስፈርት በማሟላታቸው፣ እግዚአብሔር የሚጠብቅባቸውን ችላ ለማለት መተማመኛ ስለሚሆናቸው ነው:: ትርጉም የለሽ ነገሮችን ለማድረግ የተጉ ቢሆኑም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤንና ማኅበረ ሰባዊ ኀላፊነትን ግን ችላ ይላሉ::

**ማቴ 15÷10-14**
**ማር 7÷14 ጋር**

[[14]እንደ ገና[ማቴ]] [10]ሕዝቡን ወደ እርሱ ቀረብ እንዲሉ አድርጎ እንዲህ አላቸው፤ «ስሙ አስተውሉም፤ [11]ሰውን የሚያረክሰው ከአፉ የሚወጣው እንጂ ወደ አፉ የሚገባው አይደለም::» [12]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ

ቀርበው፣ «ፈሪሳውያን ያልኸውን ሰምተው እንደ ተቈጡ አወቅህ»? አሉት፡፡ 13እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ «የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል፡፡ 14ተዉአቸው፣ እነርሱ ዕውሮችን የሚመሩ ዕውር መሪዎች ናቸው፤ ዕውር ዕውርን ቢመራ ሁለቱም ተያይዘው ወደ ገደል ይገባሉ፡፡»

ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ልማድ ከነቀፈ በኋላ ወደ መጀመሪያው ጥያቄ በመመለስ የደቀ መዛሙርቱን ባሕርይም ነቀፈ፡፡ ባልታጠበ እጅ በመብላት «ርኩስ» መሆን ችግር እንደሚያስከትል ለጌታ አልታየውም፡፡ ባልታጠበ እጅ የተበላ ምግብ ወደ ሆድ ዘልቆ፣ «ወደ ውጪ» ይወጣል (ቊ 17)፡፡ ወደ ሆድ ከሚገባው ይልቅ ሰውን የሚያረክሰው ወደ ልቡ የሚገባውና በልብ በኩል አልፎ በአፍ የሚወጣው ነው፡፡

እነዚህ ደቀ መዛሙርት ዕድሜ ልካቸውን ፈሪሳውያንን ሲያከብሩ ኖረዋል፡፡ አሁን ደግሞ ኢየሱስን በመከተላቸው የአይሁድ እምነት አዕማድ ከሆኑት ውጪ ራሳቸውን አግኝተውታል፡፡ ከዚያም በላይ በእንዲህ ያለ ነገረ መለኮታዊ እሰጥ አገባ መሓል ተገኝተዋል፡፡ ፈሪሳውያን በቊጣ ተመናጭቀው መሄዳቸው ግልጽ ነበር (ቊ 12)፡፡ «ፈሪሳውያን እንደ ተቈጡ አወቅህ?» በማለት ኢየሱስን ሲጠይቁ ድንጋጤ ውጧቸው ሳይሆን እንዳልቀረ ማሰብ ይቻላል፡፡ ኢየሱስ ግን ለእኛ ተገቢ በሚመስል መልኩ፣ «ታዲያ ምን ይሁን» ወይም፣ «ደንታ የለኝም» ወይም፣ «እኔ ላይ የተቈጡ ከመሰላችሁ እነርሱን በተመለከተ እግዚአብሔር ምን እንደሚሰማው ይታያችሁ!» የሚል መልስ ከመስጠት ይልቅ፣ ማቴዎስ 13÷28-30 ያለውን ታዋቂ ምሳሌ አቀረበ፡፡ እንደ ተክል፣ አትክልት ቦታ ስላለ ብቻ ጥሩ ተክል ነው ማለት አይደለም፡፡ እንደ መልካም አትክልተኛ ሁሉ እግዚአብሔርም ዐረሙን ያስወግዳል፡፡

«ተዉአቸው» የሚለው እስከ ፍርድ ቀን ድረስ መነቀል ስለሌለባቸው ዐረሞች ከተነገረው ምሳሌ ጋር ይስማማል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ፣ «ከዚህ በኋላ አትከተሏቸው፤ ዕውርን የሚመሩ ስለሆኑ ደዘዋቾችሁ ወደ ጥፋት ይሄዳሉ» ማለቱ እንደ ነበር ብንገነዘብ ይበልጥ ትክክል ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ የደቀ መዛሙርቱንና ከእርሱ ተለይተው የሄዱ ብዙዎቹ ደቀ መዛሙርትን ውስጣዊ ግጭት ግምት ውስጥ ብናስገባ ይህ አተረጓጐም የበለጠ ግንዛቤ ሊያስጨብጠን ይችላል፡፡

ማቴ 15÷15-18
ማር 7÷17፤19
ጋር

[17ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ከገባ በኋላ[ማር]] 15ጴጥሮስም፣ [ደቀ መዛሙርቱ[ማር]] «ምሳሌውን አስረዳን» አለው፡፡

16እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «እናንተም እስካሁን አላስተዋላችሁም ማለት ነውን? 17በአፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ ዘልቆ፣ ከዚያም ወደ ውጪ እንደሚወጣ አታውቁምን? [ይህን በማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ገለጠ[ማር]] 18ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይመነጫል፤ ሰውንም የሚያረክሰው ይህ ነው፡፡

ማር 7÷20-23
ማቴ 15÷20
ጋር

20ቀጥሎም እንዲህ አለ፤ «ከሰው የሚወጣ ያ ሰውን ያረክሰዋል፤ 21ከውስጥ፣ ከሰው ልብ የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፣ ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ 22መስገብገብ፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው፡፡ 23እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውንም ያረክሱታል፡፡ [እንጂ፣ እጅን ሳይታጠቡ መብላት ሰውን አያረክስም[ማቴ]]፡፡

ልክ በምሳሌ እንደተሰጠው ስብከት ሁሉ (ማቴ 13) ኢየሱስ ከሕዝቡ ተለይቶ ወደ ቤት ገባ፡፡ ይህም ስለ ምሳሌው ትርጒም በግል ኢየሱስን እንዲጠይቁ ለደቀ መዛሙርቱ ዕድል ሰጥቷቸዋል፡፡ እንደ ገና ደቀ መዛሙርቱን በመወከል ሲናገር የምንመለከተው ጴጥሮስን ነው፡፡ «ቤት» የሚለው ቃል ባለቤትን

በሚያመለክት መልኩ ብቻውን ስለተቀመጠ፣ እዚህ ላይ የተመለከተው በቅፍርናሆም የነበረው የጴጥሮስ ቤት ነው ማለት የሚያስችል ፍንጭ የለንም:: ኢየሱስ ወደ ገሊላ ጉዞ ላይ ስለ ነበር ይህ የሆነው በዚያ አካባቢ አንዱ ቦታ ላይ ሊሆን ይችላል::

ቁጥር 17 ቃል በቃል አለመተርጐሙ መልካም ነው:: «ከሰው የሚወጣ» የሚለው፣ «ሽንት ቤት የሚገባው» [*eis aphedrona ekballetai*] ለሚለው የገባ የአለዝቤ ትርጉም ነው:: የሰጠው ትርጉም ግልጽ ነው፤ ምንም እንኳ የተወሰነ የምግብ ቁራሽ በሥርዐቱ መሠረት የረከሰ ቢሆንም፣ ከእናንተ ጋር ስለማይቀር ሊጐዳችሁ አይችልም:: ከውስጣችሁ ወጥቶ ይጣላል:: እዚህ ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው በሥርዐቱ መሠረት ርኵስ ስለሚባሉ ጉዳዮች እንጂ፣ ጉዳት ስለሚያመጡ ነገሮች አለመሆኑን ማስታወስ አለብን::

ሰውን የሚያረክሰው ከአፉ የሚወጣው ነው:: ቃሎቻችን የልባችንን መልካምነት ወይም መጥፎነት ያሳያሉ (ማቴ 12÷34፤ ሉቃ 6÷45):: ይህ መመሪያ፣ የሚፈረድብን በቃላችን መሠረት ነው ከሚለው ጋር ይጣጣማል (ማቴ 12÷36):: ይህ ዝርዝር ለኢየሱስ የተለመደ ባይሆንም (ከሮሜ 1÷29-31፤ ገላ 5÷19-21 ጋር ያነ) ከልብ በመውጣት በአፍ ስለሚነገሩና በተግባር ስለሚገለጡ ነገሮች ምሳሌ ይሆናል:: ብዙውን ጊዜ የሰው ባሕርይ ከአእምሮ ወደ ልብ፣ ከዚያ ወደ ቃልና ምግባር በማምራት ይገለጣል::

«ይህን በማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ገለጠ» የሚለውን አስፈላጊ ቃል ማርቆስ በቅንፍ ጨምሮታል:: «የረከሰና ያልረከሰ» የሚለው በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በድጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ይሆናል (ሐሥ 10÷9-16፤ 15÷20፤ ሮሜ 14÷13፤ 1ቆሮ 8):: ጉዳዩ ስለ ምግብ ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ሕዝብም ጭምር ነው:: ይህ የሐዋርያት ሥራ 10-11 ላይ የምንመለከተው ለጴጥሮስ የተሰጠው ጠንከር ያለ ትምህርትም



ነበር:: የዐውዱ አወቃቀር የተለያዩ ነገሮችን እንድናስብ ያደርጋል:: በማቴዎስም ሆነ በማርቆስ ወንጌል ከዚህ በኋላ ኢየሱስን የምንመለከተው ከሲሮፊኒቃዊቷ ሴት ጋር ሲገናኝና በዲካፖሊስ ሲፈውስ ነው:: የኢየሱስ አገልግሎት ስለ ንጽሕና አጠባበቅ ሳይሆን ስለ ቅድስና ነው፤ ስለ ሥርዐት ሳይሆን ስለ ሰዎች ነው::[33]

**§ 78**
**ኢየሱስና ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት**
**(ማቴ 15÷21-28፤ ማር 7÷24-30)**

ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነበረች:: ማንኛውም እውነተኛ አይሁድ ማስወገድ ያለበትን ነገር ሁሉ ትወክላለች:: ሴት ናት:: በዚያ በጥላቻ በተሞላ አካባቢ ከጐና የሚሆን ወንድ አልነበረም:: ከዚህ የባሰ ደግሞ ልጇ ውስጥ ጋኔን ሰፍሮ ነበር:: ይህ ደግሞ አንድ ዐይነት ኀጢአት በሕይወቷ ሳይኖር እንደማይቀር ጥርጣሬ ያስነሣል:: ከዚያም በላይ እንደ ርኵስ ከሚቈጠሩ ከአሕዛብ ወገን ነበረች:: ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ሁኔታ በኋላ ማንኛውም ክርስቲያን ለሚመኘው የእምነት ሕይወት አርዓያ ትሆናለች:: በጣም ባልተለመደ መልኩ ኢየሱስ ውሻ በማለት ጠርቷታል:: ይህ አባባሉ ያስደነግጠናል፤ ያሳፍረናል:: አንድ ዐይነት ገለጻ እንዲገኝለት ያጓጓናል::

**ማቴ 15÷21** [21]ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና አገር ሄደ::

**ማር 7÷24** [24]ከዚያ ነተሥቶ ወደ ጢሮስ አገር ሄደ፤ ወደ አንድ ቤት ገብቶ እዚያ መኖሩን ማንም እንዳያውቅበት ፈለገ፤ ሆኖም እዚያ መኖሩን ሊሸሽግ አልቻለም::

[33] J.E. Prelan, "The Function of Mark's Miracles," *CQ* 48 (Aug 1990): 3-14 ማርቆስ ወንጌል ውስጥ ያሉ ተአምራት ይህን አመለካከት እንደሚደግፉ ያሳያል:: በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ ያልነበሩትን ኢየሱስ በተደጋጋሚ እያነጻ ነበር (1÷25-26፤ 1÷41፤ 2÷5፣11፣14፤ 2÷23-28፤ 5÷5፣28-29፣41-42፤ 7÷35፤ 8÷25):: በጥቅሉ ኢየሱስ የሌዋውያኑን ቅድስና ደንብ መተላለፉን እንመለከታለን::

የመጥምቁ ዮሐንስ በቅርብ መገደል፣ የ5000 ሰዎች መመገብ፣ ስለ ሕይወት እንጀራ የተሰበከው ስብከትና ሁኔታውን ለማጣራት በፋሲካ ሰሞን ከኢየሩሳሌም በመጡ ሰዎች ምክንያት በገሊላ ነገሮች እየተጋጋሉ ነበር:: እንዲያውም ነገሮች ተቀጣጥለዋል ማለት ይቻላል:: ኢየሱስ በአንድ ፀጥተኛ ቦታ የሚያርፍበት ጊዜ ነበር:: ስለዚህ ወደ ሰሜን ምዕራብ ወደ ፊንቄ፣ አሁን ግን ሊባኖስ ወደሚባለው አካባቢ ሄደ:: ብዙ ርቆ መሄድ አልነበረበትም:: ይህ አካባቢ በሰሜን ምዕራብ በኩል ከገሊላ ይዋሰናል:: ፊንቄ በጠላትነት የምትታይ ክልል ነበረች:: የፊንቄ ዋና ዋና ከተሞች የሆኑት ጢሮስና ሲዶና የእስራኤል ጥንታዊ ጠላቶችን ይወክላሉ (ከ58 እና ለማቴ 11÷20-30 ከተሰጠ ገለጻ ጋር ያነ)::

በዚህ ጊዜ ኢየሱስን፣ «በጠላት ወረዳ» በአንድ ድብቅ ቦታ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይሁን እንጂ ከዓመት በፊት ዝናው ወደዚህ አካባቢ ደርሶ ስለ ነበር በፈለገው ፀጥታ ውስጥ መቆየት አልቻለም (ማር 3÷8፤ ሉቃ 6÷17):: ይህች ሴት ከአሕዛብ አካባቢ «በመምጣት» [*exelthousa*] ኢየሱስን ራሱን በሰወረበት ቦታ ስታገኘው ገና ጥቂት ቀኖች እንኳ አላለፉም ነበር::

ከአሕዛብ ወገን የነበረች ይህች ሴት እንዴት ወደ አይሁዳዊ ቤት ገባች? ከአይሁዳውያኑ መካከል ሾልካ አልፋ ሊሆን እንደሚችል መገመትና ይህም ያንን ራሱን ያገለለ የቤቱን ባለቤት ሳያስደነግጥ እንዳልቀረ ከመገመት ውጪ የምንለው አይኖርም:: ኢየሱስ የነበረበትን ቦታ ባወቀች ጊዜ ብቻዋን እንደ ነበረች ማሰብ አይቻልም:: ይህ የሆነው በብዙ ሕዝብ መካከል ሳለ እንደ ነበረ መገመት እንችላለን::

**ማቴ 15÷22**
**ከማር 7÷25**
**ጋር**

[[25]ወዲያውኑ[ማር]] [22]አንዲት ከነዓናዊት ሴት [ግሪካዊት፣ በትውልዷም ሲሮፊኒቃዊት[ማር]] ከዚያ አካባቢ በመውጣት [ስለ እርሱ ሰምታ[ማር]] ወደ ኢየሱስ መጥታ፣



«ጌታ ሆይ፣ የዳዊት ልጅ፣ ራራልኝ፤ ልጄ [ትንሺቱ[ማር]] በርኩስ መንፈስ ተይዛ በጣም ትሠቃያለች» ብላ ጮኸች::

ይህች ሴት በትውልድ ፊንቃዊት ነች:: በዜግነት ሦርያዊት ነች::[34] የዘር ሐረጓ ሲመዘዝ ወደ ከነዓናውያን ይሄዳል (ማቴ 15÷22):: ማቴዎስ በዚህ አገላለጽ በመጠቀሙ ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሰን ለረጅም ዘመን የኖረውን ጥንታዊ ፉክክርና ጥላቻ እንድናስብ ያደርጋል:: በባሕልና በቋንቋ ደግሞ ግሪካዊት (ምናልባት አሕዛብ ማለት ይሁናል) ነበረች::[35]

ችግሯ ግልጽ ነው:: ልጇ በጋኔን ተይዛለች:: ይህን አይሁዳዊ ፈዋሽ ለመለመን መብት እንደሌላት ታውቃለች፤ ሆኖም ሌላ ምርጫ አልነበራትም:: ሊረዳት የሚችል ኢየሱስ ብቻ ነው:: በጣም ልዩ በሆነ መሲሐዊ መጠሪያው፣ የዳዊት ልጅ በማለት ነበር የጠራችው (ማቴ 9÷27፤ 12÷23፤ 15÷22፤ 20÷30-31፤ 21÷9፣15፤ 22÷42)::[36] ይህ ከአንዲት ሲሮፊኒቃዊት ሴት አንደበት ይወጣል ተብሎ የሚታሰብ አልነበረም:: ይህች ባዕድ ሴት በዚህ ሁኔታ ኢየሱስን የጠራችው ለምን ነበር? አንደኛ፣ በአንድ ታዋቂና ብርቱ ስም መጠቀም በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት አስማታዊ አሠራርና ጋኔን የማስወጣት ደንብ የተለመደ ነበር (ከሐሥ 19÷13 ጋር ያነ):: በዚህ ባለ ጥንድ ባሕልና ባለ ጥንድ ቋንቋ አካባቢ በአንጻራዊ መልኩም ቢሆን ነዋሪዎቹ የአይሁድን ባሕል

---

[34] ማርቆስ ሲሮፊኒቃዊት በሚለው የተጠቀመው፣ «ይህች ሴት በሰሜን አፍሪካ ካሉ ሊብዮፊንቃውያን ወገን እንዳልነበረች ለማመልከት ይሆናል» (Wessel, p. 682).

[35] የተነጋገሩት በግሪክ እንደ ነበር የማንቀበልበት ምንም ምክንያት የለም:: በገሊላ እንደ ማደጉ መጠን ኢየሱስ የግሪክ ቋንቋ ሊያውቅ እንደሚችል አያጠራጥርም:: Cf. S.E. Porter, "Did Jesus Ever Teach in Greek?" *TB* 44/2 (1993): 199-235, and J.A. Fitzmyer, "Did Jesus Speak Greek?" *BAR* 18/5 (Sept/Oct, 1992): 58-63.

[36] D.C. Duling, "The Therapeutic Son of David," *NTS* 24 (1978): 392-410 ይመ::

እንደሚያውቁ ማሰብ ምክንያታዊ ነው። ምናልባትም አየሁድ የመሲሑን መምጣት እንደሚጠብቁና አንዳንድ የተለመዱ ስያሜዎቻቸውን ጭምር ሳታውቅ አትቀርም። በዚህ ስያሜው የተጠቀመችው ኢየሱስን ለማክበርና የልጇ ፈውስ እውን ይሆን ዘንድ በዚህ ስም ውስጥ ያለውን ኃይል ለመቀስቀስ ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛ፣ የአይሁድ አምላክ ያሕዌ፣ በሕዝብ በተለይም በዳዊት መንግሥት በኩል አሕዛብን እንደሚባርክ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ተነግሮ ነበር፦

- ❖ ኢሳይያስ 9÷7፤ የመንግሥቱ ስፋትና ሰላም ፍጻሜ አይኖረውም። በዳዊት ዙፋን ላይ በመንግሥቱ ይነግሣል፤ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ለዘላለም ፍትሕና ጽድቅን ያሰፍናል። ሁሉን የሚችል አምላክ ቅንዓት ይህን ያደርጋል።
- ❖ ኢሳይያስ 11÷10፤ በዚያ ቀን የእሴይ ሥር ለሕዝቦች ምልክት ሆኖ ይቆማል። መንግሥታት ወደ እርሱ ይመጣሉ፤ ማረፊያውም የከበረ ይሆናል።
- ❖ አሞጽ 9÷11፤ በዚያ ቀን የወደቀውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ፤ የተሰበረውን እጠግናለሁ፤ የፈረሰውን ዐድሳለሁ፤ ቀድሞ እንደ ነበረም አድርጌ እሠራዋለሁ፤ ስለዚህ የኤዶምን ትሩፍ፣ በስሜ የተጠሩትንም ሕዝቦች ሁሉ ይወርሳሉ።

(በተጨማሪ ዘፍ 12÷3፤ ዘዳ 32÷43፤ መዝ 18÷49፤ 67÷2፤ 98÷2፤ 117÷1፤ ኢሳ 2÷2፤ 42÷6፤ 49÷6፣22፤ 51÷4፤ 52÷10፤ 60÷3፤ ኢዮ 2÷28፤ ሚል 1÷11 ይመ)።

እንደ ባዕድ ሰው ይህች ሴት የጠየቀችው በአይሁድ መሲሕ እንድትባረክ ነበረ። ኢየሱስ ግን እርሷም በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ መካተት እንደምትችል እንድትገነዘብ ፈልጓል። አሁን ኢየሱስ የአይሁድ መሲሕ ቢሆንም፣ ብዙም ሳይቆይ የመላው ዓለም ጌታ ይሆናል። ስለዚህ



ኢየሱስ ጥያቄዋን ችላ ያለው አሕዛብን በመናቁ (ከዮሐ 4 ጋር ያነ) ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊት ማን መሆንዋን እስክትገነዘብ ድረስ በረከቱን ለመቀበል ዝግጁ ባለመሆንዋ ነበር።[37] በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የጠየቀችውን ሰጥቷት ቢሆን ኖሮ፣ «ለሁሉም ጥሩ አድርግ» ለሚለው በዘመኑ ለነበረው አስተሳሰብ ይገዛ ነበር። ኢየሱስ፣ «ሰዎችን የሚረዳ፣ ጥሩ ሰው» ነበር ማለት እርሱን ማመስገን ሳይሆን፣ የመሳደብ ያህል ነበር። አስቀድሞ መጠየቅ የነበረባት ተአምር ሳይሆን፣ ምልክትን ነበር።

**ማቴ 15÷23-24**

> [23]እርሱ ግን አንድም ቃል አልመለሰላትም፤ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው፣ «እየተከተለችን ትጮኻለችና ብታሰናብታትስ?» ብለው ጠየቁት። [24]እርሱም፣ «የተላክሁት ከእስራኤል ቤት ሆነው ወደ ጠፉት በጎች ብቻ ነው» አለ።

ይህ በሐሳባችን ያለው ኢየሱስን አይመስልም። ለትንሹም ለትልቁም ጓደኛ ነበር። በአይሁድ ማኅበረ ሰብ ልጇ በጋኔን የተያዘችባት ከአሕዛብ ወገን የሆነች ሴትን ያህል የሚናቅ ግን ሊኖር አይችልም።

ደቀ መዛሙርቱ በሁኔታው ታውከዋል። በመንገድ እየሄዱ እያለ እየለመነች፣ እየተከተለችና እየጮኸች አስቸግራቸዋለች። ሴት ከመሆኗ በላይ፣ አሕዛብም ናት፤ ይህ ደግሞ ይበልጥ አስቆጥቷቸዋል። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን የጠየቁት ከዚህች ሴት ገላግለን ዐይነት ነበር ብሎ

---

[37] «እንደ ከነዓናዊቷ ሴት ሁሉ የመቶ አለቃውም ጥያቄ መልስ ያገኘው በእስራኤልና በሌሎች መካከል ያለውን ልዩነት ከተገነዘበ በኋላ ነበር» J.J. Scott, "Gentiles and the Ministry of Jesus: Further Observations on Mt 10:5-6; 15:21-28," *JETS* 33/2 (1990): 161-169. አሕዛብ በሙሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመሆናቸው በፊት፣ (1) አዲስ እስራኤልን ለማስገኘት ኢየሱስ መሞት ነበረበት፣ (2) አይሁድም እንዲቀበሉ የመጀመሪያውን ዕድል ማግኘት ነበረባቸው። ስለሆነም አሕዛብ የሚጨመሩበት ጊዜ ገና ቢሆንም ኢየሱስ የአይሁድ መሲሕ ከመሆኑ አንጻር ከአሕዛብ ወገን መሆንዋን በማወቋ በግል ለዚህች ሴት ጥያቄ ምላሽ ሰጠ።

ማሰብ ይህን ያህል ከባድ አይደለም (ዮሐ 4÷27፤ ሉቃ 9÷54)። ይሁን እንጂ ጥያቄው የሚታሰበውን ያህል አስከፊ ላይሆን ይችላል። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን የጠየቁት እንዲያሰናብታት እንጂ፣ ምንም እንዳያደርግላት እንደ ነበር ጽሑፉ የሚነግረን የለም። እንዲያውም ደቀ መዛሙርቱ፣ «የምታደርግላትን አድርግላትና ወዲያ አሰናብታት» አሉት በሚል መልኩ ብንረዳው ቍጥር 24 የበለጠ ትርጕም ይኖረዋል።

ቍጥር 24ን ለመረዳት በጣም ቀላል ቢሆንም በዚህ ዐውድ ግን እንደዚያ አይደለም። የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት አይሁዳውያን ላይ የሚያተኵር (ማቴ 10÷5-6፤ ዮሐ 1÷11) እንደ ነበርና የኋላ ኋላ ሕዝቦችን ሁሉ የሚያቅፍ እንደሚሆን እናውቃለን (ማቴ 10÷18፤ 28÷18-20፤ ዮሐ 10÷16)። ይህ፣ «ቅድሚያ ለአይሁድ» የሚለውን አሠራር በየሐዋርያት ሥራም ደጋግመን የምንመለከተውና (1÷8፤ 10÷34-35፤ 13÷46-47፤ 18÷6፤ 19÷8-9፤ 28÷28)፣ ጳውሎስም በሮሜ 1÷16፤ 2÷9-10 የተናገረው ነው።[38] በዚህ ምንባብ ውስጥ አስቸጋሪው ነገር ኢየሱስ፣ «የተላክሁት ለአይሁድ ሕዝብ ብቻ ነው» ካለ በኋላ ሴትየዋን መርዳቱ ነው።

ኢየሱስ እርሷን ብቻ ሳይሆን፣ ዐሥራ ሁለቱንም እያስተማረ ነበር። የእግዚአብሔር መንግሥት ለሕዝቦች ሁሉ የመሆንዋን ከባድ እውነት መረዳ ይኖርባቸዋል። እውነት ነው እርሷ ከተመረጠው ሕዝብ ወገን አልሆነችም፤[39] ይህ ግን፣ «በቤቱ» ውስጥ ስፍራ የላትም ማለት

[38] «ቅድሚያ ለአይሁድ» የሚለው አሠራር፣ እያየን ባለነው ማር 7÷27 እንኳ ተነሥቷል።

[39] «የእግዚአብሔር እስራኤል» የተሰኘውን ነገረ መለኮታዊ እሳቤ እዚህ ላይ ማንሣቱ ነገሩን ወደ ኋላ መመለስ ይሆናል። እየመጣ ቢሆንም ገና ነው። እውነተኛ እስራኤላዊ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነቱን ያስተካከለ ነው (ዘፍ 32÷28፤ መዝ 73÷1፤ 125÷5)። አዲስ ኪዳን እዚህ ነጥብ ላይ ጠንከር ያለ አቋም አለው (ማቴ 21÷41፣43፤ 8÷11-12፤ 22÷1-14)፣ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም አረጋግጠውታል (ከገላ 3÷7፣29፤ ሮሜ 4÷11፣14፤ ያዕ 2÷5፤ ራእ 21÷12-14)። (ሌላው ቀርቶ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ተነግሮአል፤ ኢሳ



አይደለም። ኢየሱስ ይህን እውነት የገለጠበት መንገድ የረቀቀ ቢሆንም፣ ውብ ነበር!

ማቴ 15÷25-26
ማር 7÷25-27
ጋር

25ሴትዮዋም እግሩ ላይ ወድቃ፣ [በእግሩ ላይ ወደቀች[ማር]] «ጌታ ሆይ፤ ርዳኝ አለች። [ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን ከልጇ እንዲያስወጣላት ለመነችው[ማር]] 26እርሱም መለሰ፣ [መጀመሪያ ልጆቹ ጠግበው ይብሉ[ማር]] «የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መወርወር አይገባም» አላት።

ማር 7÷28-30
ማቴ 15÷27-28
ጋር

28እርሷም መልሳ፣ «አዎን፣ ጌታ ሆይ፤ ውሾችም ከገበታ በታች ሆነው የልጆችን ትራፊ [ከጌታቸው ማዕድ የወዳደቀውን ፍርፋሪ[ማቴ]] ይበላሉ» አለችው። 29እርሱም [«አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ፈለግሽው ይሁንልሽ»[ማቴ]] «ስለዚህ ይህን ስላልሽ ሂጂ፤ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል» አላት [ልጇም ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰች[ማቴ]] 30እርሷም ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጇ አልጋ ላይ ተኝታ፣ ጋኔኑም ለቅቋት አገኘቻት።

ይህች ሴት ለማንነቷ የነበራትን ክብር አውልቃ ጥላለች፤ ርዳታ ያስፈልጋታል! ወንዶች ስለ ሴቶች በሚማልዱበት ማኅበረ ሰብ ከችግሯ የተነሣ ገደቡን አልፋ ሄዳለች። በኢየሱስ እግር ላይ ወድቃ፣ በማርቆስ ወንጌል ኢየሱስን ጌታ በማለት የጠራች እርሷ ብቻ ነች። ቀደም ሲል ኢየሱስ በዝምታው አሳፍሯት ነበር፤ አሁን ደግሞ በቃሉ አሳፈራት። ይህን ያደረገው ዝቅ ባለችበት ሁኔታ ሊረግጣት ሳይሆን፣ የመረዳት ደረጃዋን ከፍ ለማድረግ ነበር።

54÷1-3፣ ገላ 4÷27 ጋር ያነ፤ ሆሴ 2÷23፤ ከሮሜ 9÷24-26፤ ሕዝ 47 እና ኢሳ 44÷3፣ ዮሐ 7÷37-39 ጋር ያነ)።

ለአይሁድ ውሾች ሁሉ የረከሱ ነበሩ። በተጨማሪም፣ «ውሻ» የሚለው አይሁድ ስለ አሕዛብ ሲናገሩ ከሚጠቀሙበት ቃል አንዱ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ይህችን ሴት የረከሰች ውሻ አድርጎ ጠርቷታል ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ግሪኮች ውሾችን ይወዱ ነበር፤ እንደ ቤት እንስሳ በቤታቸው እንዲኖሩ ማድረጋቸውም የተለመደ ነበር። እዚህ ላይ ይህች ግሪካዊት ሴት የኢየሱስን ቃል የተረዳችው ኪናርያ - *kynaria* በሚለው መልክ ነበር (በተለይ መጠንን በሚያመለክት ቅጥያው)።[40] ያም ሆኖ ግን ተስፋ የሚሰጥ አልነበረም። የሴትየዋ ትሕትና በጣም የሚገርም ነው። የአነጋገር ለዛዋና ጽናቷም እንዲሁ የሚገርም ነው። በዚህም ጊዜ፣ ያላት ብቸኛ ተስፋ ኢየሱስ መሆኑንና፣ በእግዚአብሔር፣ «ቤተ ሰብ» ስፍራ ያላት መሆኑንም ተረድታለች። በኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል ተዘጋጅታለች፤ እርሱም ሊሰጣት ደስታኛ ነው።

ይህ የመጀመሪያው ረጅም ተአምር (ዮሐ 4÷46-54) ወይም ለአሕዛብ የተደረገ የመጀመሪያ ተአምር አይደለም (ማቴ 8÷5-13፤ ሉቃ 7÷1-10)። የእግዚአብሔር መንግሥት ከእስራኤል ድንበር መሻገሩን በጉልህ የሚያሳይ ገለጻ ነው (ከማቴ 13÷47-50 ጋር ያነ)። ሴትየዋ ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጇ ተፈውሳ፣ ሆኖም ዐልጋ ላይ እንዳለች አገኘቻት፤ ምናልባትም ጋኔኑ ለቆ ሲወጣ በተፈጠረው መንዘፍዘፍ ምክንያት ሊሆን ይችላል (ከማር 1÷26፤ 9÷26 ጋር ያነ)። ሆኖም ትልቁ ጥቅሟ ከቅርብ ጊዜ በኋላ በተሟላ ሁኔተ የምታገኘውን የእስራኤል ተስፋ መቀበሏ ነበር (ሐሥ 11÷19፤ 15÷3፤ 21÷3-4)፤ 27÷3)።

---

[40] Cf. F. Dufton, "The Syrophoenician Woman and Her Dogs," *ExpT* 100 (1989): 417.



### § 79ሀ
### ፈውስ በዐሥር ከተማ
### (ማቴ 15÷29-31፤ ማር 7÷31-37)

[ማር7][31]ከዚያም ኢየሱስ ከጢሮስ አገር ተነሥቶ፣ በሲዶና በኩል አድርጎ ዐሥር ከተማ በተባለው አገር በማለፍ ወደ ገሊላ ባሕር መጣ።

ኢየሱስ በጢሮስ አካባቢ የነበረው አገልግሎት አብቅቷል፤ ስለዚህ ሃያ ኪሎ ሜትር ወደ ሰሜን በመጓዝ ሙሉ በሙሉ የአሕዛብ ወደ ሆነ ቦታ ሄደ። በኋላም በሄሮድስ ፊልጶስ አራተኛ ከተማ በኩል አድርጎ ታቹን በስተ ምሥራቅ ወደ ገሊላ ባሕር ሄደ። ይህም ቢሆን ዐሥር ከተማ በመባል የሚታወቅ የአሕዛብ አገር ነበር። «ዐሥሩ ከተማ» የሚለው ዴካፓሊስ የሚለው ትርጉም ነው። ይሁን እንጂ ከዴካፓሊስ ጋር የተያያዘ የከተሞች ዝርዝር እንደ ጸሐፊውና ዝርዝሩ እንደ ተያዘበት ዘመን ይለያያል።[41] ሆኖም፣ የግሪክ ባሕልና ሃይማኖት የሞላበት አገር ስለ መሆኑ ግን እርግጠኞች ነን።

ኢየሱስ በጌርሴኖን አጋንንት ያደረበትን ሰው በፈወሰ ጊዜ ቢያንስ አንድ ጊዜ በዚህ አካባቢ ተገኝቶ ነበር። ባለፈው ጊዜ በዚያ የቆየው ከዐሥራ ሁለት ሰዓት አይበልጥም። የአገሩ ሰዎች ኢየሱስ ከአገራቸው እንዲሄድ ለምነውት ነበር። በአጋንንቱ ላይ የነበረው ሥልጣን አስፈሪ ብቻ ሳይሆን አጥፊም ነበር። 2000 ዐሣሞችን አጥፍቷል። ያ ለአካባቢው ገበሬዎች ከፍ ያለ ገቢ ያስገኝ ነበር። ያን ያህል ብዛት ያለው ሕዝብ ወደ ኢየሱስ የመጣው ተአምር በማድረግ ኀይሉ ብቻ ሳይሆን ከአጋንንት ነጻ በሆነው ሰው ምስክርነት እንደ ነበር እናስባለን (ማር 5÷20)።

---

[41] ከሶርያ ጋር ተያያዥነት የነበራቸው እነዚህ ከተሞች አንዳንድ ቅርታዎቻቸውን የሚያቀርቡት ለሮም ነበር። በሁለተኛው መቶኛ ዓመት የራሳቸውን ሳንቲም አስቀርጸው ነበር። ሆኖም የራሳቸው መንግሥት፣ ሕዝባዊ ሠራዊት ወይም የንግድ ስምምነትን በተመለከተ ከተሞቹ በኮንፌዴሬሽን የሚተዳደሩ አልነበሩም። S.T. Parker, "The Decapolis Reviewed," *JBL* 94 (1975): 437-441.

ለ79 ሀ እና ለን፣ «አንድ ዐይነት፣ ሆኖም የበለጠ» የሚል ርእስ ልንሰጠው እንችላለን:: ፈውሶቹም ሆኑ 4000ዎቹን መመገቡ የሚያቀርበው አዲስ ነገር የለም::

የተለዩ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር፣ በአሕዛብ ክልል ውስጥ ለአሕዛብ የተደረጉ መሆናቸው ነው:: እዚህ ላይ በኢየሱስ አገልግሎት በስፋት ተአምራት መደረጋቸውን ስናስተውል (§ 76ለ-82) ስለ አሕዛብ መጨመር ቀጣዩን ዐቢይ ሐሳብ እንረዳለን:: እነዚህ ራሳቸውን የቻሉ ሁኔታዎች ከዚህ ዐቢይ ሐሳብ አንጻር መታየት ይኖርባቸዋል:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ወዴት እንደሚያመራ ካልተረዳን በቀር ምን እያደረገ እንደ ነበር በትክክል መረዳት አንችልም::

[ኪዚያ ተነሥቶ ወደ ተራሩ ወጥቶ ተቀመጠ^ማቴ] ማር 7፥32-35 ማቴ 15፥29 ጋር

32በዚያም ሰዎች ደንቈሮና ድዳ የሆነ አንድ ሰው ወደ
እርሱ አመጡ፤ እጁንም እንዲጭንበት ለመኑት::
33ኢየሱስም ሰውየውን ከሕዝቡ ለይቶ ከወሰደው በኋላ፣ ጣቶቹን በጆሮው
አስገባ፤ ከዚያም እንትፍ ብሎ የሰውየውን ምላስ ዳሰሰ:: 34ወደ ሰማይም ተመልክቶ
ቃተተና፣ «ኤፍታህ!» አለው፤ ይኸውም፣ ተከፈተ ማለት ነው:: 35ወዲያውም ጆሮዎቹ
ተከፈቱ፤ ምላሱም ተፈቶ አጥርቶ መናገር ጀመረ::

ይህ ምስኪን የመናገር ችግር ነበረበት፣ ምናልባት መስማት ካለመቻሉ የተነሣ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም እርሱ ራሱ ኢየሱስ እንዲፈውሰው መጠየቅ አይችልም፤ ያንን ያደረጉለት ጓደኞቹ ነበሩ:: ስለ ኢየሱስ የመፈወስ ኀይል ሰምተው ስለነበር (ማቴ 14፥36) ጓደኛቸውን እንዲፈውሰው ጠየቁት::

ኢየሱስ ይህን ደንቈሮና ዲዳ ገለል ወዳለ ቦታ ወሰደው:: ቦታው ጸጥ ያለ ስለ ነበር እየተንተባተበ የሚናገረውን ኢየሱስ በትክክል ሊረዳ



ወይም የመስማት ችግር ያለበት ሰው ኢየሱስን በትክክል እንዲረዳ ያስችላል:: ብቻቸውን መሆናቸው ኢየሱስ የሰውየውን እምነት እንዲያነሣሣ ያስችላል:: እንቅስቃሴና ስሜትን የሚስብ ነገር ስለማይኖር ትኩረቱን ይበልጥ መሰብሰብ ይችላል:: ከዚህም በተጨማሪ በሕዝቡ መሐል ብዙ ግርግርና ኹካታ አይኖርም (ማር 7፡36):: ኢየሱስ በአገልግሎቱ እዚህ ነጥብ ላይ ሕዝቡን ከማስገረም ይልቅ ከሕዝቡ መራቅ ሲሞክር እንመለከታለን::

ጣቶቹን በሰውየው ጆሮዎች ውስጥ በማድረግና ምራቅ ከምላሱ እንትፍ በማለት ኢየሱስ ምን ሊያደርግ እንደሆነ በምልክት ለዚያ ሰው አሳየ:: እርግጥ ነው፣ ዲዳና ደንቈሮ የነበረው ሰውም ሆነ በሩቅ የነበረው ሕዝብ ኢየሱስ የሚናገረውን ከመስማት ይልቅ ማየት ይችሉ ነበር:: የአይሁድ ጸሎት ደንብ በነበረው መሠረት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ተመልክቶ ቃተተና[42]፣ «ኤፍታህ» የሚለውን ባለ አንድ ቃል ጸሎት አሰማ:: ማርቆስ ኢየሱስ በአረማይክ የተናገራቸውን ሁለት ቃላት እንደ ተረጐመ ሁሉ ይህንንም የአረማይክ ቃል ለአንባቢዎቹ ተርጕሞአል::

ይህ የግሪክኛ ተናጋሪዎች አካባቢ ከሆነ ኢየሱስ የአረማይክ ቃል የተጠቀመው ለምንድነው? በገሊላ እንደ ማደጉ መጠን በጥቂቱም ቢሆን ግሪክኛ እንደሚያውቅ ግልጽ ነበር:: በጸሎት ጊዜ ግን በትውልድ አገር ቋንቋ መጠቀም የተለመደ ስለ ነበር ነው:: ከዚያም በላይ ደንቈሮው ስለማይሰማ ኢየሱስ በትውልድ ቋንቋው ቢናገር ምንም አይጠቅመውም:: ምናልባትም የኢየሱስ አገልግሎት ወደ አሕዛብ እየደረሰ መሆኑንና፣ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ግን በተለየ ሁኔታ ለአይሁድ መሆኑን ለማመልከት የተጠቀመበት የረቀቀ ዘዴ ሊሆን ይችላል (ዮሐ

[42] ስቴናዞ [stenazo] የሚለውን ቃል ከወንጌሎቹ የምናገኘው እዚህ ብቻ ነው:: መልእክቶቹ ውስጥ ጥልቅ መቃተትን ለመግለጽ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ሮሜ 8፡23፤ 2ቆሮ 5፡2፣4፤ ዕብ 13፡17):: ኢየሱስን እንዲህ እንዲቃትት ያደረገው መን እንደ ሆነ በእርግጠኝነት አናውቅም:: ምናልባትም የሰውየውን ስሜት እንደሚጋራ ለማሳየት ሊሆን ይችላል::

4÷22):: ኢየሱስ ለአይሁድ ያደረገውን ተአምር ለአሕዛብም ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር:: ይሁን እንጂ መሲሕነቱ፣ «አይሁዳዊ» መልኩን እንዲለቅ አልፈለገም:: በተሟላ መልክ ድነት ለአሕዛብ የሚሆነው ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች፣ መሥዋዕቶችና ተስፋዎች ጋር በተያያዘ መልኩ ብቻ ነበር::

**ማር 7÷36-37**

36ኢየሱስ ይህን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው፤
ሆኖም እርሱ እንዳይናገሩ ባዘዛቸው መጠን፣ ነገሩን
አስፋተው አወሩት:: 37ሕዝቡም ከመጠን በላይ በመደነቅ፣
«ያደረገው ሁሉ ጥሩ ነው፤ ደንቆሮዎች እንዲሰሙ፣
ድዳዎች እንዲናገሩ እንኳ አድርጎአል» አሉ::

የተለመደ ዜማ፣ የአሕዛብ ግጥም፤ ኢየሱስ አገልግሎቱ በአሕዛብ ዘንድ እንዲስፋፋ ያልፈለገበት ምክንያት፣ አይሁድ አገልግሎቱን እንዲያስፋፉ ካልፈለገበት ምክንያት ጋር ተመሳሳይ ነው:: (1) ትኩረታቸው ተአምራት ላይ እንጂ ምልክቶች ላይ አልነበረም፤ (2) መሲሕነቱን በተመለከተ የነበራቸው መረዳት በእንጭጭነት ደረጃ የነበረና አግባብነት የሌለው ነበር፤ (3) ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መድረኩ በዚያ ጊዜ የተመቸ አልነበረም:: ይህ የኢየሱስ እንቅስቃሴ ከተገቢው ጊዜ በፊት ቢስፋፋ፣ ኢየሱስ ማድረግ የፈለገውን ነገር የሚያፈርስ ሕዝባዊ ዐመፅ ሊቀሰቅስ ይችላል::

አዲሱ መደበኛ ትርጒም፣ «መናገር አይችልም ነበር» በማለት በተረጐመው ማርቆስ ሞጊላሎስ - *mogilalos* የተሰኘ ቃል ተጠቅሟል:: በአዲስ ኪዳን ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው እዚህ ብቻ ነው:: የሰብዓ ሊቃና ትርጒም የተጠቀመበት አንዴ ኢሳይያስ 35÷6 ላይ ብቻ ነበር:: ይህ መሲሓዊ ክፍል መሆኑ ግልጽ ነው:: እንዲህ ይላል:-

በዚያን ጊዜም የዕውር ዐይኖች ይገለጣሉ፤ የደንቆሮም ጆሮዎች ይከፈታሉ:: አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘላል፤ የድዳውም አንደበት በደስታ ይዘምራል ... በዚያ አውራ ጐዳና ይሆናል:: «የተቀደሰ መንገድ» ተብሎ ይጠራል:: የረከሱ አይሄዱበትም ... እግዚአብሔር የዋጃቸው ይመለሳሉ:: እየዘመሩ ወደ ጽዮን ይገባሉ፤ ዘላለማዊ ደስታን እንደ አክሊል ይቀዳጃታል (ኢሳይያስ 35÷5-10)::

ማርቆስ ይህን ያልተለመደ ቃል በመጥቀስ ትኩረታችንን ስለ ኢየሱስ ወደ ተነገረ መሲሐዊ ትንቢት መሳብ የፈለገ ይመስላል:: ከዚያም በላይ ማርቆስ ከአሕዛብ ጋር በተያያዘ መልኩ ነበር የተጠቀመበት::

**ማቴ 15÷30-31**

30ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝብም አንካሶችን፣ ዐይነ
ስውሮችን፣ ሽባዎችን፣ ዲዳዎችን እንዲሁም ሌሎች
ብዙዎችን ሕመምተኞች ይዘው ወደ እርሱ በማምጣት
በእግሩ ሥር አስቀመጧቸው፤ እርሱም ፈወሳቸው::
31ሕዝቡም ዲዳው ሲናገር፣ ሽባው ደህና ሲሆን፣ አንካሳው ቀጥ ብሎ ሲሄድ፣ ዐይነ
ስውሩም ሲያይ ተመልክተው ተደነቁ፤ የእስራኤልንም አምላክ አመሰገኑ::

እዚህም ላይ ያው ነው! ለኢየሱስ የምንሰጠው ምላሽ ይኸው ነው፤ የተሰበሩ ነገሮቻችንን ወደ እርሱ እናምጣ፤ እርሱም ይጠግናቸዋል:: ይሁን እንጂ፣ እንግዳው ነገር እነዚህ አሕዛብ፣ «የእስራኤልንም አምላክ አመሰገኑ» የሚለው ነው:: እዚህ ላይ ኢየሱስ የእቅዱን አይሁዳዊነት በማሳየት ረገድ ተሳክቶለታል:: የኢየሱስ በአሕዛብ መካከል ማገልገል በተአምራት ብቻ ሳይሆን ማስተማርንም የሚጨምር ነው ማለት እንችላለን:: ማቴዎስ (15÷29) ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ «ተቀመጠ» ይላል:: አንድ አይሁዳዊ መምህር ተቀመጠ ማለት፣ «ትምህርት ሊጀመር ነው» የማለት ያህል ነበር (ከማቴ 5÷1፤ 13÷1-2 ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ እንደ አይሁድ አቻዎቻቸው ሁሉ እነዚህ አሕዛብ ኢየሱስ በሚያደርገው እንጂ ለሚናገረው ልቡ ያላቸው አልነበሩም::

**§ 79ለ**
**4,000ዎቹን መመገቡ**
**(ማቴ 15፥32-38፤ ማር 8፥1-9)**

የአራት ሺዎቹ መመገብ፣ እንደ አምስት ሺዎቹ መመገብ ሁሉ አከራካሪ ነው:: አንዳንድ ምሁራን ማቴዎስና ማርቆስ አጽንዖት ለመስጠት ያህል አንዱን ጉዳይ ድጋሚ እንዳቀረቡ ያስባሉ::[43] ይሁን እንጂ በሁለቱ መካከል በጉልህ የሚታይ ልዩነት አለ፤ ምንባቦቹን ስናነብ ስለ ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎች የሚያመለክቱ መሆናቸውን እናያለን::[44] በሁኔታዎቹ መካከል ያለው ተመሳሳይነት በዚህ የአገልግሎቱ ክፍል ኢየሱስ ለአይሁድና ለአሕዛብ የሰጠውን አገልግሎት በንጽጽር ያሳያል::

**ማር 8፥1-3**

1በዚያ ጊዜ፣ እንደ ገና ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ:: የሚበሉት ምንም ምግብ ስላልነበራቸው ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፣ እንዲህ አላቸው፤ 2ከእኔ ጋር ሦስት ቀን ስለ ቈዩና የሚበሉትም ስለሌላቸው እነዚህ ሰዎች ያሳዝኑኛል፤ 3እንዲህ እንደ ተራቡ ወደ ቤታቸው ብሰዳቸው አንዳንዶቹ ከሩቅ የመጡ ስለ ሆኑ በመንገድ ላይ ዝለው ይወድቃሉ::

---

[43] E.g., D.F. Robinson, "The Parable of the Loaves," *ATR* 39 (1957): 107-115. S. Masuda ርቆ በመሄድ ሁለቱም ታሪኮች ከአንድ የመጀመሪያ ምንጭ የተወሰዱ መሆናቸውን ያመለክታል ("The Good News of the Miracle of the Bread," *NTS* 28 [1982]: 191-219).

[44] (1) የተለያየ ዝርዝር ነበራቸው፤ (ሀ) በ5000 እና በ4000፣ (ለ) 5 እንጀራና 7 እንጀራ፣ (ሐ) 12 መሶብ ሙሉ (*kophinos*)፣ 7 ትልልቅ መሶብ ትርፍራፊዎች (*spyris*) ሐሥ 9፥25 ጋር ያነ):: (መ) 1 ቀን ከኢየሱስ ጋር እና ሦስት ቀን፣ (ሠ) አንድ ጊዜ ጸለየ፤ ሁለቴ ጸለየ፤ (ረ) ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሰደደ፤ ከሐዋርያቱ ጋር ተለይቶ ሄደ::
(2) በተለያየ ጊዜ፣ በተለያየ ሁኔታ ነበር - በመጀመሪያው ሣር ላይ ተቀመጡ፤በሁለተኛው መሬት ላይ ተቀመጡ (ሣሩ ከደረቀ በኋላ)::
(3) ለሁለት የተለያዩ ሕዝቦች ነበር:: በመጀመሪያው የመገበው አይሁዳውያንን ነበር፤ በሁለተኛው በአብዛኛው አሕዛብን ነበር::
(4) ኢየሱስ ራሱ በሁለት የተለያ ጊዜዎች መመገቡን በግልጽ ተናግሯል (ማር 8፥18-21)::



የኢየሱስ ዝና በዐሥሩ ከተሞች በፍጥነት እየተስፋፋ ነው:: ለጥቂት ጊዜ እዚያ በመቈየቱ የሕዝቡ ቍጥር እያደገ መጥቷል:: ከሦስት ቀን ፈውስና ማስተማር በኋላ ሕዝቡ የነበራቸው ምግብ አልቆ ነበር:: ብዙዎቹ ወደ ቤት ሄደው ተጨማሪ ምግብ ከማምጣት ይልቅ እዚያ ቆይተው ኢየሱስን ለመስማት ሲሉ ጾማቸውን ነበሩ:: ይህን ማድረጋቸው መልካም ነበር፤ ምክንያቱም ወደ ቤት ከሄዱ እነርሱ ከመመለሳቸው በፊት ኢየሱስ ይሄድባቸዋል::

ኢየሱስ የሚሄድበት ጊዜ መጥቷል:: ይሁን እንጂ እነዚያ ጾማቸውን የነበሩ ሰዎችን ያለ አንዳች ምግብ ቢሰዳቸው እቤታቸው ከመድረሳቸው በፊት ዝለው እንዳይወድቁ ስጋት ገብቶታል:: ጥቃቅን በሆኑ ዕለታዊ ነገሮቻችን እንኳ የኢየሱስ ርኅራኄ ይበልጥ ደምቆ ይታያል::

**ማር 8፥4-9 ከማቴ 15፥33-38 ጋር**

4ደቀ መዛሙርቱም መልሰው፣ «በዚህ ምድረ በዳ እነዚህን ለመመገብ የሚያስችል እንጀራ ከወዴት [እናገኛለን[ማቴ]] ይገኛል? አሉት:: 5እርሱም «ስንት እንጀራ አላችሁ?» ብሎ ጠየቃቸው:: እነርሱም፣ «ሰባት» አሉት:: 6እርሱም፣ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ሕዝቡን አዘዘ፤ ሰባቱንም እንጀራ ይዞ ካመሰገነ በኋላ ቈርሶ ለሰዎቹ እንዲያድሉ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዘቡ አደሉት:: 7እንዲሁም ትንንሽ ዓሣዎች ነበሯቸው፤ እርሱም ዓሣዎቹን ባርኮ እንዲያድሏቸው አዘዘ:: 8ሕዘቡም በልተው ጠገቡ፤ ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ የተረፈውን ቍርስራሽ ሰባት መሶብ ሙሉ አነሡ:: 9በዚያም [ከሴቶችና ከሕፃናት ሌላ[ማቴ]] አራት ሺህ ያህል ሰዎች ነበሩ::

እነዚህ ሰዎች የግንዛቤ ችግር ነበረባቸው ወይስ ምንድን ነው? 5000 ሰዎችን መመገቡን ከምኔው ዘነጉ (ማር 6፥52 ጋር ያነ):: እነዚህ ሰዎች ላይ ከመፍረዳችን በፊት፣ አንዳንድ ነገሮችን ግምት ውስጥ ማግባት ይኖርብናል:: አንደኛ፣ ኢየሱስ ሁሌ ተአምር አያደርግም ነበር

(ዮሐ 5÷4-6፤ ማቴ 13÷58) ወይም ይህን መጠበቅ የግድ «መንፈሳዊ» አያሰኝም (ማቴ 12÷38-45፤ 16÷1)፡፡ ሁለተኛ፣ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ለአይሁድ ያደረገውን ለእነዚህ አሕዛብም ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን እንጂ፣ ችሎታውን እየተጠራጠሩ አልነበረም፡፡ ሦስተኛ፣ ማቴዎስ፣ «እኛ» (15÷33) ለሚለው ቃል አጽንዖት መስጠቱ፣ የተጠራጠሩት የኢየሱስን ችሎታ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ያደረገውን እነርሱ ማድረግ መቻላቸውን መጠራጠራቸውን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡ እርሱ ያደረገውን እንዲያደርጉ ሥልጣን ሰጥቷቸው እንደ ነበር ግልጽ ነው (ማቴ 10÷1፣8)፡፡ ምናልባትም ጥቂት ሺ ሰዎችን በመመገብ ችሎታቸውን እንዲያሳዩ የፈለገ መስሏቸው ይሆናል፡፡ በመጨረሻም፣ የዘመናችንን ቤተ ክርስቲያን በቅን ልብ ብንመለከት ኢየሱስ መስጠትና ማድረግ መቻሉን በተመለከተ ከእነርሱ የተሻለ እምነት እንደሌለን ማሰብ እንችላለን፡፡ ኢየሱስ በየጊዜው ታማኝነቱን ቢያሳየንም፣ ሕይወታችን ግን አለማመናችንን በሚያሳፍር መልክ ያሳያል፡፡

**§80**
**በመጌዶል ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁ (ማቴ 15÷39-16÷4፤ ማር 8÷9-12)፤ [ከ62፣106 እና ዮሐ 2÷18-23፤ 6÷30 ጋር ያነ]**

[ማቴ15]39ኢየሱስ ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ [ከደቀ መዛሙርቱ ጋር[ማቴ]] በጀልባ ወደ መጌዶል [ዳልማኑታ ወደ ተባለ ስፍራ[ማር]] ሄደ፡፡

1ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ ኢየሱስ ቀርበው ሲፈትኑት በመሻት ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት፡፡

ኢየሱስ በዐሥር ከተማ 4000ዎቹን ከመገበ በኋላ ወደ አይሁድ አገር ተመለሰ፡፡[45] ፈሪሳውያን እንደ ገና ወደ ኢየሱስ ተሰበሰቡ (ከማር

[45] መጌዶልና ዳልማኑታ ሁለቱም ጠፍተዋል፤ ሆኖም ከገሊላ ባሕር ደቡብ ምዕራብ፣ ዐሥር ከተማ ዳርቻ ላይ የነበሩ ሳይሆኑ እንደማይቀር ይታሰባል፡፡



7÷1 ጋር ያነ)፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዱቃውያንም አብረው ነበሩ፡፡ አጠቃላይ በሆነ መልኩ እነዚህ ሁለቱ አይስማሙም ነበር (ከሐሥ 23÷7-8 ጋር ያነ)፡፡ ለኢየሱስ ያላቸው ጽኑ ጥላቻ ግን አቀራርቧቸዋል፡፡ የመጥምቁ ዮሐንስን ጉዳይ ለማጣራት ከተገናኙ ወዲህ፣ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ሲገናኙ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው (ማቴ 3÷7፤ ዮሐ 1÷19:24)፡፡ ብዙ ጊዜ በዋነኛነት ከኢየሱስ ጋር የሚከራከሩት ፈሪሳውያን ብቻ ነበሩ (ማቴ 9÷11፣34፤ 12÷2፣14፣24፣38፤ 15÷1፤ ሉቃ 5÷17፤ 7÷36-39)፣ ከዚህ በኋላ ግን ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር እንደሚያደርጉት ሁሉ (ማር 3÷6፤ 12÷13)፣ ከሰዱቃውያንም ጋር ያብራሉ (ማቴ 21÷45፤ 22÷34፤ 27÷62)፡፡

ጥያቄያቸው አዲስ ወይም ቅንነት ያለበት አልበረም፡፡ ከዚያ በፊት ኢየሱስ ቢያንስ ሦስቴ ይህንኑ ሰምቷል (ዮሐ 2÷18-23፤ ማቴ 12÷38-45፤ ዮሐ 6÷30 ለምንባቦቹ የተሰጠውን ገለጻ በተመለከተ § 31፣62 እና 76ለ ይመ)፡፡ በእውነት በኢየሱስ ማመን አልፈለጉም፡፡ ማቴዎስና ማርቆስ ስለ ዓላማቸው ሲያመለክቱ፣ «ሊፈትኑት» [*peirazo*] ብለዋል፡፡ ቃል በቃል ኢየሱስን የሚከሱበት ምክንያት ፍለጋ እየፈተኑት ነበር፡፡ ጳውሎስ፣ «መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናክል፣ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው» በማለት ወገኖቹን በትክክል ገልጿቸዋል (1ቆሮ 1÷22-24)፡፡

ከይሁዳ የመጡ[46] መልእክተኞች ተንኰላቸውን ሰውረው ነበር፡፡ በመጀመሪያ፣ ከተአምር ይልቅ ምልክትን [*semeian*] ጠየቁ፡፡ ሁለተኛ ያቀረቡት ጥያቄ የረቀቀ ተንኰል መሆኑን ሳይሆን፣ ኢየሱስ ያደረጋቸው

[46] «ወጥተው» (8÷11) - *exelthen* የሚለው ግሥ የሌላ ቦታ ሰዎች መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ማር 7÷1ን መሠረት በማድረግ እነዚህ መልእክተኞች ከኢየሩሳሌም ነበሩ ቢባል አግባብ ይሆናል፡፡

ተአምራት በዐይነታቸው የተለዩ ይመስል ኤልያስ ወይም ሙሴ እንዳደረጉት ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠይቀዋል::

[2]እርሱም መልሶ [በመንፈሱ እጅግ በመቃተት፤[47] እንዲህ አላቸው[ማር]] «ምሽት ላይ 'ሰማዩ ስለ ቀላ ብራ ይሆናል' ትላላችሁ፤ [3]ንጋት ላይም፣ 'ሰማዩ ቀልቶአል፤ ከብዶአልም፤ ስለዚህ ዝናብ ይዘንባል' ትላላችሁ:: የሰማዩን ገጽታ ትለያላችሁ፤ ነገር ግን የዘመኑን ምልክት መለየት አትችሉም::»

ማቴ 16÷2-3
ከማር 8÷12
ጋር

ብዙውን ጊዜ የፓለስቲና ነፋስ ከበስተ ምዕራብ ከሚዲትራኒያን ባሕር ይነሣል:: ንጋት ላይ በምዕራብ የሚታየው ዝናብ ያዘለ ደመና ከወደ ምሥራቅ ተራሮች የምትወጣው ፀሐይ ስታርፍበት በጣም ቀልቶ ይታይ ነበር:: ምሽት ላይ ግን ቀልቶ ይታይ የነበረው ደመና በምዕራብ በኩል ጥርት ያለ ሰማይ ሆኖ ይታያል::[48]

ኢየሱስ በአይሁድ መሪዎች በጉልህ ሊታይ በሚችል ሁኔታ ታውኮአል:: ከመሲሑ ይልቅ ትኩረታቸው የአየሩ ሁኔታ ላይ ሆኗል:: በኢየሱስ እንዲያምኑ ብዙ ምክንያት ነበሯቸው (ከዮሐ 5÷31-47 ጋር ያነ)፤ ይሁን እንጂ የኢየሱስን ተአምራዊ ኀይል ከቡዔልዜቡል ጋር በማያያዝ ለማመን ፈቃደኞች አልሆኑም (ማቴ 9÷34፤ 12÷22-37፤ ከሉቃ 11÷14-36 ጋር ያነ)::

[47] ኢ.መ.ት.፣ «በመንፈሱ» የሚለውን ቃል ሳይተረጉም ትቶታል::

[48] እነዚህ ቊጥሮች በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጥቂት ቅጆች ውስጥ ባይገኙም ይህ ተገቢ ቦታቸው ይመስላል:: በግብፃውያን ቅጂዎች ውስጥ ያልገቡት ምናልባት የግብፃውያን የአየር ሁኔታ የፓለስቲናውያን ዓይነት ስላልሆነ ሊሆን ይችላል::



[4]ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይፈልጋል፤ ነገር ግን ከዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም::

ማቴ 16÷4

ተአምራዊ ምልክት በመፈለጉ ክፉና አመንዝራ የሚሆነው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ያለ ማስረጃ እንድናምነው ይፈልጋልን? እምነት በጭፍን መቀበል ማለት ነውን? በፍጹም! ምልክት መፈለግ ክፉ የሚሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው:-

(1) ቀደም ሲል ኢየሱስ ያደረገውን ችላ በማለት:: በመሠረታዊ ይዘቱ፣ «ኢየሱስ ሆይ፣ አናምንህም:: ደግሞህ ደጋግመህ ማረጋገጫ ልትሰጠን ይገባሃል» የማለት ያህል ነው::

(2) እኛን በኢየሱስ ላይ ፈራጆች በማድረጉ:: ምልክት መጠየቅ፣ «ኢየሱስ ሆይ፣ አንተ አንዳች ነገር አድርግልን፤ እኛ ደግሞ ትክክል መሆን አለመሆኑን እንወስናለን» የማለት ያህል ነው::

(3) ከምስክርነት ይልቅ ተአምራትን የሚያስቀድም በመሆኑ ተአምራት የሚጠቅሙት ትኩረታችንን አሳማኝ ምስክርነት ወዳለው ሁኔታ ለመሳብ ነው:: ምስክርነቱ ከተሰጠ በኋላ ግን የተአምራቱ ዓላማ ተፈጽሟል ማለት ነው:: ከዚህም በላይ ከምክንያት ይልቅ ለስሜት ቅድሚያ ይሰጣል:: ከምስክርነቱ አንጻር ከማሰብ ይልቅ ስሜቶቻችንን እናደምጣለን::

እንደገና ትንሣኤው ለዚህ ትውልድ ምልክት መሆኑ ተነግሯል:: ይህም እንኳ ቢሆን ከማያምኑ ሰዎች የተሰወረ ነው (ከማር 8÷12፤ ሐሥ 10÷41 ጋር ያነ):: ከጠላቶቹ ተቃውሞ የተነሣ ኢየሱስ እንደ ገና አካባቢውን ትቶ መሄድ ነበረበት:: በኢየሩሳሌም፣ በናዝሬት፣ በቅፍርናሆም አሁን ደግሞ በመጌዶን ተንቋል::

[ማቴ 16፥4 = ማቴ 12፥39:: የ62ን፣ በተለይ ስለ ዮናስ ምልክት የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ::]

### § 81ሀ ከፈሪሳውያን፣ ከሰዱቃውያንና ከሄሮድስ እርሾ ስለ መጠበቅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ማቴ 16፥5-12፤ ማር 8፥13-21)

[ማር 8]13ከዚያም ትቶአቸው በጀልባ ወደ ማዶ ተሻገረ:: 14ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ መያዝ ስለ ረሱ፣ ከአንድ እንጀራ በቀር በጀልባ ውስጥ ምንም አልነበራቸውም:: 15ኢየሱስም፣ «ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና [ከሰዱቃውያን ማቴ] ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ» ብሎ አዘዛቸው:: 16እነርሱም እርስ በርሳቸው «እንዲህ የሚለን እኮ እንጀራ ስለሌለን ነው» ተባባሉ::

ከአይሁድ ሃይማኖት ባለ ሥልጣኖች ጋር ሌላ ከፍ ያለ አለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባሕሩን አቋርጦ ወደ ሰሜናዊው ዳርቻ ሄደ:: ወደ ሌላው ዳርቻ[49] በመሄድ ላይ እያሉ ኢየሱስ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንዲጠበቁ ደቀ መዛሙርቱን አስጠነቀቀ:: ኢየሱስ ስለ ትምህርት ሲያሳስብ ደቀ መዛሙርቱ ግን ስለ ምግብ እያሰቡ ነበር (ከዮሐ 4፥31-34፤ 6፥27 ጋር ያነ):: የኢየሱስ ንግግር አነጋገር ለዐሥራ ሦስት ከሚቀራመቷት አንድ እንጀራ በቀር ለምሳ የሚሆን ምንም እንዳልነበራቸው አሳሰባቸው::

የኢየሱስን ማስጠንቀቂያ እንዴት እንደ ተረጐሙት መናገር ይከብዳል:: ምናልባትም ስለ ተመረዘ ምግብ እያስጠነቀቃቸው እንደ ሆነ አስበው ይሆናል:: ቀደም ሲል በይሁዳና በገሊላ አይሁድ ኢየሱስን መግደል እንደሚፈልጉ ገልጸው ነበር (ማር 3፥6፤ ዮሐ 5፥18፤ ማቴ

49 «ሄደ» (*apelthen*) የሚለው ግሥ፣ «ማዶ»፣ (*peran*) ወይም «ባሻገር» ከሚለው ጋር ሲያያዝ መድረሳቸውን የሚያመለክት አንድምታ ሊኖር ይችላል:: ይሁን እንጂ በሰዋሰው መሠረት ገና በሂደት ላይ መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው:: በሌላ አባባል ይህን ውይይት ያደረጉት ወደ ቤተ ሳይዳ እየሄዱ ነበር:: ይህ አተረጓጐም ማር 8፥22 ላይ ያለው በሰላማዊ ሁኔታ መጠናቀቁን ያሳያል::



12፥14):: በዚያ ዘመን በመርዝ መግደል የተለመደ ነበር:: ምናልባትም ከራብ የተነሣ ኢየሱስ ምን ማለቱ እንደ ነበር በቅጡ እንዳይረዱ ሆነው ይሆናል:: እነርሱ የሚያውቁት በእጃቸው ያለው ለራት የማይበቃ መሆኑንና የኢየሱስ ማስጠንቀቂያ ምግብ አለመግዛታቸውን የተመለከተ መሆኑን ብቻ ነበር (ቍ 16)::

ፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑት ምንም ዓይነት ኅብረት አልነበራቸውም (ማቴዎስ ሰዱቃውያንን በሄሮድስ ተክቶአል፤ እነዚህ ሰዎች ከሰዱቃውያን የተላኩ ፓለቲካዊ መልእክተኞች ሊሆኑ ይችላሉ:: ምንም እንኳ የራሳቸው የሆነ የሥልጣን ደረጃ ባይኖራቸውም፣[50] እዚህ ላይ የሚወክሉት የፈሪሳውያን አቻ የሆኑት ሰዱቃዊ ሄሮድሳዊ ወገንን ነው):: እነዚህ ቡድኖች የምሥራቅ የምዕራብን ያህል የተራራቁ ቢሆኑም፣ ኢየሱስ ግን እርሾአቸው የአንዱ ከሌላው የማይበላለጥ ክፉ መሆኑን አመልክቷል:: እነዚህ ሁለት ቡድኖች የሚጋሩት ስሕተት ምንድነው? በረቀቀና ይፋ በወጣ ሁኔታ ኢየሱስን መቃወማቸው ነው:: ምልክት ቢያሳያቸው በእርሱ ለማመን ፈቃደኞች መሆናቸውን ተናግረው ነበር (ዮሐ 2፥18-23፤ ማቴ 12፥38-45፤ 16፥1-4):: ይሁን እንጂ እንደ መሪና እንደ ጌታ እርሱን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን የሚያሳይ ፍንጭ አልታየም::

ብዙ ጊዜ እርሾ የክፋት ምሳሌ ሆኖ ነው የሚቀርበው (ዘሌ 2፥11፤ ማቴ 16፥6፤ ሉቃ 12፥1፤ 1ቆሮ 5፥6-8፤ ገላ 1፥5-9 ጋር ያነ) ሆኖም ሁሌም እንደዚያ ነው ማለት አይደለም (ማቴ 13፥33፤ ሉቃ 13፥20-21 ጋር ያነ):: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች በፋሲካው

50 የፈሪሳውያን ችግራቸው ወግ አጥባቂነት፣ የሰዱቃውያን ልቅነት፣ የሄሮድሳውያን ደግሞ ወገናዊነት ነው ብንል ከሐቁ አንርቅም:: የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አመለካከትም፣ ለእንዲህ ዐይነት ስህተቶች የተጋለጠ በመሆኑ ይህን የኢየሱስን ማስጠንቀቂያ ልብ ብናደርግ ይጠቅማል:: ሦስቱም፣ ተመሳሳይ ዓይነት፣ «እርሾ» ወይም አለማመንን ይጋራሉ:: እያንዳንዱ በራሱ ደካማነት ከእውነተኛ ደቀ መዛሙርት ጉድሎአል:: እያንዳንዱ የራሱ ዝንባሌ አለው፤ ያ ዝንባሌ ግን ከኢየሱስ የሚያርቅ ነበር::

ቂጣ ውስጥ እንዳይኖር የተፈለገው እርሾ ኀጢአትን እንደሚወክል አመልክተዋል (ዘፀ 12÷8 ወዘተ ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ ምግቡ በችኰላ የተዘጋጀ መሆኑን የሚያመለክት ሊሆንም ይችላል:: እርሾው ዳቦውን፣ «ኩፍ» እስኪያደርገው ድረስ ለመጠበቅ ጊዜ አልነበራቸውም:: በሌላ አነጋገር፣ «ክፉ» የእርሾው ዓይነተኛ ባሕርይ ሳይሆን፣ «እያመረቀዘ የሚሄድ ተፅዕኖ» ነው:: ይህን ግንዛቤ ይዘን ኢየሱስ የተናገረው፣ «እያመረቀዘ ከሚሄድ የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን ያለማመን ተፅዕኖ ተጠበቁ» ለማለት እንደ ነበር እንረዳለን:: ይህ የሆነው ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ብዙዎቹ ወደ ኋላ በተመለሱበት ጊዜ ነበር (ከዮሐ 6÷60-71 ጋር ያነ):: የኢየሱስ ዝና እየደበዘዘ ሲሄድ ማኅበረ ሰቡ ሊያሳድርባቸው ከሚችል ክፉ ተፅዕኖ እንዲጠበቁ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይገባ ነበር::

**ማር 8÷17-21**
**ማቴ 16÷8 ጋር**

17ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ፣ እንዲህ
አላቸው፤ [እናንተ እምነት የጐደላችሁ^ማቴ] «እንጀራ
ስለሌለን ነው በማለት ምን ያነጋግራችኋል? አሁንም
አታስተውሉምን? ልብስ አትሉምን? ወይስ ልባችሁ ደንድኖአል? 18ዐይን እያላችሁ
አታዩምን? ጆሮ እያላችሁ አትሰሙምን? አታስተውሉምን? 19አምስቱን እንጀራ ለአምስት
ሺህ ሰው በቈረስሁ ጊዜ ስንት መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ አነሣችሁ? እነርሱም፣ «ዐሥራ
ሁለት» አሉት:: 20«ሰባቱንስ እንጀራ ለአራት ሺህ በቈረስሁ ጊዜ ስንት መሶብ ሙሉ
ትርፍራፊ አነሣችሁ?» አላቸው:: እነርሱም፣ «ሰባት» አሉት::
21እርሱም፣ «እስከ አሁን አላስተዋላችሁም ማለት ነውን?» አላቸው

**ማቴ 16÷11-12**

11ታዲያ የነገርኋችሁ ስለ እንጀራ እንዳልሆነ
እንዴት አታስተውሉም? አሁንም ከፈሪሳውያንና
ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁ::» 12በዚህ ጊዜ
ያስጠነቀቃቸው ከእንጀራ ውስጥ ስለሚጨመረው እርሾ
ሳይሆን፣ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት መሆኑ
ገባቸው::



የደቀ መዛሙርቱ እምነት መጉደል የሚያሳዝን ነው (ከማቴ 6÷30፤ 8÷26፤ 14÷31፤ 17÷20 ጋር ያነ):: እምነትን አስመልክቶ ኢየሱስ ያስተማረውን ጥልቅ ትምህርት አለመረዳት ብቻ ሳይሆን ስለ ምግብ ተራውን ነገር እንኳ መረዳት ተስኖአቸው ነበር:: ኢየሱስ ኢሳይያስ 6÷10ን መሠረት በማድረግ ምግብን ለመስጠት ስላለው ታላቅ ችሎታ አሳሰባቸው:: አምስት ትንንሽ እንጀራዎች 5000 ሰዎችን መመገብ ከቻለና ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ ቁርስራሽም ሊተርፍ ከቻለ፣ በሰባት እንጀራዎች 4000 ሰዎችን መመገብ ከቻለና ሰባት መሶብ ሙሉ ቁርስራህ ሊተርፍ ከቻለ፣ አንድ እንጀራ ብቻ ዐሥራ ሦስት ሰዎችን መመገብ መቻሉ ግልጽ ነው::

ኢየሱስ እንጀራን በተመለከተ የተፈጠረውን ይህን አነስተኛ አለመግባባት ካስተካከለ በኋላ ወደ ተነሣው ጉዳይ ተመለሰ፤ ጉዳዩ የፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ትምህርት እርሾ ነበር::[51] እንዲህ ሲባል ትምህርታቸው ሁሉ መጥፎ ነበር ማለት አይደለም (ከማቴ 23÷3 ጋር ያነ):: ኢየሱስ የፈሪሳውያንን አጉል ወግ ባለመቀበላቸው ከሰዱቃውያን ጋር ይስማማል:: ትንሣኤንና ሌሎችንም እውነቶች በማመናቸው ደግሞ ከፈሪሳውያን ጋር ይስማማል:: ይሁን እንጂ ኢየሱሰ ሥር የሰደደ አለማመናቸውን በተመለከተ አስጠንቅቆናል:: በሃይማኖት ካባ የተሸፈነ በመሆኑ አለማመናቸው ስውር ነው:: ቀጥተኛውን ተግባርና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አጥብቀው ቢይዙም፣ ያለማመን ራስ ወዳድነታቸው ጠንቅ ከእግዚአብሔር እቅድ እንዲርቁ አድርጓቸዋል:: ይህ ደግሞ በአለባበስ፣ በአነጋገርና በአደባባይ የሚታይን ሃይማኖተኝነት በሚመዝን

---

[51] ብሉምበርግ፣ «ቍጥር 12 ላይ ያሉት፣ «ትምህርት» (*amira*) እና «እርሾ» (*hamira*) በተሰኙ ቃላት መካከል ተመሳሳይነት በመኖሩ በአረማይክ ቋንቋ ሰምና ወርቅ ዓይነት የቃላት ጨዋታ ሊኖር ይችላል» የሚል ማሳሰቢያ አቅርቧል (ገጽ 249)::

ሕዝብ ዘንድ ግራ የሚያጋባ ነበር። ብዙውን ጊዜ አስፈላጊው ነገር ከመጠን በላይ አስፈላጊ ሆኖ እንዲታይ ያደርጋል (?)።

### §81ለ
### የዐይነ ስውሩ ባለ ሁለት ደረጃ ፈውስ
### (ማር 8፥22-26)

22ከዚያም ወደ ቤተ ሳይዳ መጡ፤ ጥቂት ሰዎችም አንድ ዐይነ ስውር ወደ ኢየሱስ አምጥተው እንዲዳስሰው ለመኑት። 23እርሱም የዐይነ ስውሩን እጅ ይዞ ከሰፈር ውጭ አወጣው፤ በዐይኖቹም ላይ እንትፍ ብሎበት፣ እጁንም በላዩ ጭኖ፣ «ምን የሚታይህ ነገር አለ?» ሲል ጠየቀው።

24እርሱም ቀና[52] ብሎ አይቶ፣ «ሰዎች እንደ ዛፍ ሲንቀሳቀሱ አያለሁ» አለ።

25ኢየሱስም እንደ ገና እጆቹን በሰውየው ዐይኖች ላይ ጫነ፤ በዚህ ጊዜ ዐይኖቹ በሩ፤ ብርሃኑም ተመለሰለት፤ ሁሉንም ነገር አጥርቶ ማየት ቻለ። 26ከዚያም፣ «ወደ መንደሩ አትግባ! በመንደሩም ለማንም አትናገር» ብሎ ወደ ቤቱ ሰደደው።

ይህ፣ «የዓሣ አጥማጆች ሰፈር» (ቤተ ሳይዳ) የጴጥሮስና የጓደኞቹ ትውልድ ቦታ ሳይሆን አይቀርም። ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ በሄዱ ጊዜ ጀልባዎቻቸውን ትተው የሄዱት እዚህ ቦታ ነበር። ወደ አገራቸው ሲመለሱ ዐይነ ስወሩን ይዘው ከመጡ ሰዎች ጋር ተገናኙ። ስለ ሰውየው እምነት መጠን መናገር አንችልም፤ የጓደኞቹ እምነት ግን ግልጽ ነበር (ከማር 2፥3-12፤ 7፥31-37 ጋር ያነ)። እምነት የጐደለው ቢሆን እንካ እምነቱን ለማነሣሣት ኢየሱስ ያልተለመደ እርምጃ የወሰደው ለምን እንደ ነበር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

[52] «ቀና ብሎ»[*anablepo*] የሚለው፣ «ማየት ቻለ» በሚል በተሻለ ሁኔታ ተተርጉሟል፤ E.S. Johnson, "Mark 8:22-26; Blind Man From Bethsaida" *NTS* 25 (1979): 230-383.



እንዲህ ያለው ሁኔታ በጣም የተለመደ እየሆነ ሄዷል። ኢየሱስ ምን ጊዜም ዐይነ ስውርነትን ይፈውስ ነበር (ማቴ 9፥27-30፤ 11፥5፤ 12፥22፤ 15፥31፤ ሉቃ 7፥21-22፤ ዮሐ 5፥3)። ዐይነ ስውርነት በሦስተኛው ዓለም አገሮች በስፋት የሚገኝ በሽታ ነው። ሆኖም እዚህ ላይ የምንመለከተው ሁኔታ የተለየ ነበር። ደንቆሮና ዲዳ ከነበረው ሰው ፈውስ ጋር ተመሳሳይ የሚያደርጉት አንዳንድ ነገሮች አሉ (ማር 7፥31-37)[53]:-

(1) ሁለቱን በማርቆስ ብቻ የተጻፉ ናቸው።

(2) ሁለቱም የተፈጸሙት እረፍት ላይ እያሉ ነበር።

(3) ሁለቱም ወደ ገለልተኛ ቦታ ተወስደዋል።

(4) ኢየሱስ በምራቁና በሁለት እጆቹ በመዳሰስ ተጠቅሟል፡

(5) በሁለቱም ጊዜ ለማንም እንዳያወሩ ተናግሯል።

ይህን ፈውስ የተለየ የሚያደርገው ኢየሱስ ካደረጋቸው ፈውሶች ሁሉ፣ «ባለ ሁለት ደረጃ» የሆነው ይኸኛው ብቻ መሆኑ ነው። ኢየሱስ ይህን ሲያደርግ ዓላማው ምን እንደ ነበር ከግምት ያለፈ ምክንያት የለንም። ይሁን እንጂ ዌሴል፣ «ኢየሱስ የተንቀሳቀሰው የሰውየው እምነት እስከ ፈቀደ ድረስ ነበር» የሚል ጥሩ ሐሳብ አቅርቧል (በማርቆስ ወንጌል ውስጥ እምነት ፈውስን ለመቀበል ቅድመ ሁኔታ እንደ ነበር አጽንዖት ተሰጥቶአል)። ካልቪን ደግሞ ኢየሱስ ሉዓላዊ ነጻነቱን እያሳየ ነበር የሚል ሐሳብ አቅርቧል። የዐይን ሐኪሞች ተጨማሪ ገለጻ መስጠት ይችላሉ። አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ዐይነ ስውር ሆኖ ከኖረ ከቀዶ ሕክምና በኋላ ዓይኖቹ ቢበሩ እንኳ የሚያያቸው ነገሮችን ሁሉ በሚገባ መረዳት ከመቻሉ በፊት የዐይኖቹ ክፈፍ ብርሃን

[53] R.A. Guelich (p. 436) እንደሚለው ማረቆስ የደንቆሮና ዲዳ (7፥31-37) እና የዐይነ ስውሩን (8፥22-26 ታሪክ ያቀረበው ጀልባው ውስጥ (8፥13-21) ያሳዩትን የደቀ መዛሙርቱን መንፈሳዊ ደንቈሮነትና ዕውርነት ለማመልከት ነበር። በሌላ አነጋገር ማርቆስ በአካላዊ ደንቆሮነትና ዐይነ ስውርነት መካከል በማቅረብ የደቀ መዛሙርቱን እምነት ደካማነት ነገሩን ማሳየት ፈልጓል።

እንደ ገና መላመድ ይኖርባቸዋል:: ይህ ምናልባት አንድ ወር ይወስድ ይሆናል! እስከዚያ ድረስ የሚያያቸው ነገሮች ሁሉ ዝርግ፣ ተጓዳኝና የተጠላለፉ መስመሮች መስለው ይታዩታል:: ኢየሱስ የፈወሰው ዐይነ ስውር ሰዎች እንደ ዛፍ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ይታዩኛል ሲል እንዲሁ የተጠቀመበት ቃል ሳይሆን በሕክምና የተለመደ አገላለጽ ነበር፤ ዐይኖቹ ቢፈወሱም፣ ኢየሱስ የሰውየውን ክፈፈ ብርሃን በቅጽበት በማስተካከል ሁለተኛ ተአምር አደረገ::[54] በአንደ ነገር በጣም እርግጠኞች ነን:: የጥንት ቤተ ክርስቲያን ይህን ታሪክ አልፈጠረችም! ፈጠራ ቢሆን ኖሮ ባለ ሁለት ደረጃ አይሆንም ነበር:: ከዚህም በተረፈ ይህ የሕክምና ገለጻ ለምን እንደ ነበር በቂ ምክንያት ያቀርባል::[55] በምራቅ መጠቀሙ ምራቅ ስላለው ፈዋሽነት በአይሁድ ዘንድ በሰፊው ከተለመደው አስተሳሰብ ጋር ይስማማል:: «ሰዎች እንደ ዛፍ ሲንቀሳቀሱ» ማየቱ ሰውየው ከሩቅ ማየት አለመቻሉን ወይም ደግሞ እንዲህ ያለ ንጽጽር ማቅረብ በመቻሉ

[54] Russell Grigg, "Walking Trees," *Creation* 21/4 (Sept/Nov 1999): 54-55.

[55] L.W. Countryman, "How Many Baskets Full? Mark 8:14-21 and the Value of Miracles in Mark," *CBQ* 47 (1985): 643-655 እንደሚለው ከፊል ገለጻው የመጣው ከማርቆስ ወንጌል አቀራረብ የተነሣ ሊሆን ይችላል:: እዚህ ላይ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ሁለት ተነጻጻሪ ዑደቶች ያሉ ይመስላል::

| ዑደት 1 | ዑደት 2 |
| --- | --- |
| ነፋሱን ጸጥ ማሰኘቱ (4÷35-41) | በባሕር ላይ መራመዱ (6÷45-52) |
| በጌርሴኖን አጋንንት ማውጣቱ (5÷1-20) | ከሲሮፊኒቃዊቷ ሴት ልጅ ጋኔን ማውጣቱ (7÷24-30) |
| የኢያኢሮስን ልጅና ደም ይፈሳት የነበረች ሴት መፈወስ (5÷21-43) | ደንቆሮና ዲዳ (7÷31-37) |
| 5000ዎቹን መመገቡ (6÷32-44) | 4000ዎቹን መመገቡ (8÷1-9) |

በመጀመሪያው ዑደት ኢየሱስ በነጻነትና በታላቅ ኀይል ተአምራት ያደርግ ነበር:: በሁለተኛው ዑደት የኢየሱስ አገልግሎት አሕዛብ ወደሚበዙበት አካባቢ ሲዛወር ተአምራቱ አልፎ አልፎ ነበር የሚፈጸሙት:: በባሕር ላይ በተራመደ ጊዜ፣ አልፎ ሲሄድ» ነበር:: ከሲሮፊኒቃዊቷ ሴት ጋር ተከራከረ፤ ደንቆሮና ዲዳውን በሁለት ደረጃ ፈወሰ:: በሁለተኛው ጊዜ ኢየሱስ በዛ ባለ እንጀራ አነስ ያሉ ሰዎችን መገበ:: እነዚህ ሁሉ ዝርዝር ሁኔታዎች በእርግጥ እርሱ የአይሁድ መሲሕ ስለ መሆኑ ሳያሳውቅ በግልጽ ተአምራት ለማድረግ ፈቃደኛ ስላለመሆኑ ሊያመለክት ይችላል::



ዕውር ሆኖ አለመወለዱን ሊያመለክት ይችላል:: ኢየሱስ እጆቹን ሰውየው ላይ ሲጭን የሰውየው ዐይኖች በሩ:: ማርቆስ ከሩቅ አጥርቶ ማየትን የሚያመለክት፣ [*telaugos*] የሚልና አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ተጠቅሟል:: ማየት ብቻ ሳይሆን፣ አጥርቶ ማየትም ችሏል::

ይህ ባለ ሁለት ደረጃ ተአምር ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጴጥሮስ የሚያቀርበውን ምስክርነት የሚያመለክት ነበር በማለት ዌሴል መናገሩ ምናልባት ትክክል ነበር:: በማርቆስ ወንጌል ያለውን ይህንን ንጽጽር የሚያሳየው ሰንጠረዥ ማስተዋል የሚታይበት ነው::

| | | |
| --- | --- | --- |
| 8÷22 | ሁኔታዎቹ | 8÷27 |
| 8÷23-24 | ከፊል የማየት ችሎታ - ከፊል የመረዳት ችሎታ | 8÷28 |
| 8÷25 | ማየት መቻሉ - መረዳት መቻል | 8÷29 |
| 8÷26 | ለማንም እንዳይናገር መታዘዙ | 8÷30 |

**§82**
**የጴጥሮስ አስደናቂ ምስክርነት**
**(ማቴ 16÷13-20፤ ማር 8÷27-30፤ ሉቃ 9÷18-21)**

በዚህ ጊዜ ወደ ሦስተኛው የኢየሱስ አገልግሎት ዓመት መጥተናል:: አሁንም ቢሆን ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ማንነት በሚገባ አልተረዱም:: እንዲህ ያለው ምስክርነት ከጊዜው የቀደመ ይሆናል::

ባለፉት ጥቂት ወራት ኢየሱስ በአይሁድ አገር ዳርቻዎች ወዲያ ወዲህ ሲመላለስ ነበር:: በወቅቱ ይህ በኢየሱስ አገልግሎት የተቃውሞ ጊዜ የነበረ ይመስላል:: ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ የሰጠው ምስክርነት የሦስቱም ወንጌሎች ዐቢይ ጉዳይና ለኢየሱስ አገልግሎት እንደ መከለያ ሆኗል::

[13]ኢየሱስ ፊልጶስ ቂሣርያ [መንደሮች[ማር]] ወደ ተባለው አገር በደረሰ ጊዜ [በመንገድ ላይ ሳለም[ማር]] [ብቻውን ይጸልይ በነበረ ጊዜ[ሉቃ]] ደቀ መዛሙርቱን፣ «ሰመሆኑ ሰዎች፣ የሰውን ልጅ ማን ነው ይላሉ?» ብሎ ጠየቃቸው።

ማቴ 16፥13-14
ከማር 8፥27፤
ሉቃ 9፥19 ጋር

[14]እነርሱም፣ «አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው [ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ከሙታን ተነሥቶአል[ሉቃ]] ይላሉ» አሉት።

ፊልጶስ ቂሣርያ አየሩ ጥርት ባለ ቀን አናቱ ላይ ያለው በረዶ ከናዝሬት ድረስ ማየት በሚቻለው ባአርሞንኤም ተራራ ግርጌ ነበር የሚገኘው። ውብና ለም የሆነ አካባቢ ነበር።[56] ከባሕር ወለል 1150 ጫማ ከፍታ ላይ ሆኖ የላይኛውን ዮርዳኖስ ውብ አካባቢ ማየት ይቻል ነበር። ሌላው ቀርቶ ትዕይንቱ ራሱ እንካ፣ «አንድ አስደናቂ ነገር ሊደረግ ነው» የሚል ይመስል ነበር። ይሁን እንጂ ምን እንደ ሆነ፣ ወይም መልካም ወይም ክፉ መሆኑን ሐዋርያቱ ገና አላወቁም ነበር።

ለኢየሱስ ይህ በጣም አስፈላጊ ጊዜ ነበር። በሌሎች ወሳኝ ሁኔታዎች እንዳደረገው ሁሉ (ሉቃ 3፥21፤ 6፥12፤ 9፥28፤ 22፥4) በጸሎት ነበር የቆየው (ሉቃ 9፥18)። ስለ ኢየሱስ የተሰጡ ሌሎች ምስክርነቶችም ነበሩ (ለምሳሌ ዮሐ 1፥29-34፣41፣45፣49፤ 3፥2፣36፤ 4፥42፤ 6፥68-69፤ 11፥27)፣ ሆኖም አንዳቸውም ይህን አያህሉም። እንደሚሞት ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጽ እስኪናገር ድረስ አንዳቸውም

---

[56] ስለ ፊልጶስ ቂሣርያ ኤደርሼይም ሰፋ ያለ ገለጻ አቅርቧል (II: 72-74)። በጣም ማራኪ ከሆኑ ጥቅሶቹ አንዱን የወሰደው Tristram, *Land of Israel*, p. 586 ሲሆን፣ እንዲህም ይላል፣ «በየቦታው እጅብ ብሎ የበቀለ ቁጥቋጦ፣ የእንጆሪ ዛፎች፣ የበለስ ዛፎች፣ ከገደል የሚወረወር ጅረት፣ የተጐነጐኑ የወይን ግንዶች፣ ጥርት ያለ ውሃ የፈለቀባቸው ምንጮች፣ ቀርቀሃዎች፣ ፍርስራሾችና የወፎችና የውኖች ዝማሬ በአንድነት የሚሰሙበት ስፍራ ነበር።»



እንካን በዚህ ሁኔታ ከኢየሱስ የጋለ ምላሽ አላገኙም (ዮሐ 2፥19፤ 3፥14፤ 6፥53፤ ማቴ 9፥15፤ 10፥38-39፤ 12፥39-40 ጋር ያነ)።

ኢየሱስ ከጸሎት በኋላ መንገድ ላይ እያሉ ወደ ዐሥራ ሁለቱ ዞወር በማለት በጥንቃቄ የታሰበበት የሚመስል ጥያቄ አቀረበላቸው። ዝንባሌን እንጂ መልስ በመጠበቅ የቀረቡ ጥያቄዎች አልነበሩም። በመጀመሪያ፣ «ለመሆኑ፣ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ነው ይላሉ?» የሚል ነበር። ይህ ለኢየሱስ ያልተለመደ ጥያቄ ነበር። እርሱ ይህን አያውቅም ኖሯል? የሰዎችን ሐሳብ የማንበብ ችሎታው ሳይጨመርበት እንካ (ከማቴ 12፥25፤ ሉቃ 5፥22፤ 6፥8፤ 7፥39-40፤ ዮሐ 2፥24-25ጋር ያነ)፣ ኢየሱስ ደንቆሮ አልነበረም። እንደ ዐሥራ ሁለቱ ሁሉ ሰዎች ስለ እርሱ የሚሉትን መስማተ ይችል ነበር። ለመሆኑ ኢየሱስ ሰዎች ስለ እርሱ ስለሚያስቡት ነገር ይህን ያህል ግምት መስጠት የጀመረው ከመቼ አንሥቶ ነው? ይህን የጠየቀው መልስ በመጠበቅ ሳይሆን፣ በእርግጥ እርሱ ማን መሆኑን ደቀ መዛሙርቱ የእርሱን ሐሳብ እንዲጋሩ ለማድረግ ነበር።

የተወሰኑ አስተያየቶ ቀርበዋል። አንዳንዶች ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ብለው አስበዋል (ከማቴ 14፥1-2 ጋር ያነ)። አንዳንዶች ኤልያስ ነው ብለው አስበዋል (ሚል 3፥1፤ 4፥5-6)። አንዳንዶቹም ምናልባት የአዋልድ መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ኢየሱስ ኤርምያስ ሊሆን እንደሚችል አስበዋል (ዕዝራ ካልዕ 2፥16-18፤ መቃ ካልዕ 2፥1-12፤ 15፥12-16)። አይሁድ ሰው ከሞተ በኋላ እንደ ገና ይወለዳል ብለው አያምኑም ነበር። ይሁን እንጂ የተለዩ ነፍሶች የጀመሩትን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ በሕይወት ባሉ ሰዎች በኩል ሊጠቀሙ እንደሚችል ያምኑ ነበር (ከ71 ሀ ጋር ያነ)። ስለሆነም ኢየሱስ ከእነዚህ ታላላቅ ሰዎች የአንዱ መለኮታዊ ምስል ሊሆን እንደሚችል አስበዋል።

ለመሆኑ ኢየሱስ እነዚህ ሰዎችን የመሰለው እንዴት ነበር? እነዚህ ሰዎች ከመሞታቸው ባሻገር፣ ሁሉም ከኢየሱስ ጋር የሚጋሩዋቸው ሦስት የወል ባሕርያት አሏቸው፤ (1) ጥላቻና ስደት በያለበት ሁኔታ እንኳ ያለ ምንም ማለባበስ እውነትን ተናግረዋል፤ (2) በዘመናቸው የነበሩትን የሃይማኖትና የፖለቲካ ባለ ሥልጣኖች ፊት ለፊት ተጋፍጠዋል፤ (3) በአቋማቸው ምክንያት የተለያየ መከራ ተቀብለዋል:: ሕዝቡ የሃይማኖት መሪዎቹ ኢየሱስ ላይ የነበራቸው ጥላቻ በየጊዜው እየከፋ መምጣቱን አይተዋል:: ከእነዚህ አመለካከቶች አንዳቸውንም እንኳ እንደ መደምደሚያ መውሰድ አይችሉም:: ኢየሱስን ከታላቅ መምህራን ወይም ታዋቂ ነቢያት ደረጃ ማስቀመጥ ተገቢውን ስፍራ አለመስጠት ማለት ነው::

15 እርሱም፣ «እናንተስ እኔን ማን ትሉኛ
ላችሁ?» አላቸው::
16 ስምዖን ጴጥሮስም፣ «አንተ ክርስቶስ
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» በማለት መለሰ::

ማቴ 16÷15-16

አሁን ወደ ዋናው ጥያቄ መጥተናል ... መሠረታዊው ጉዳይ ያለውም እዚህ ላይ ነው «እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?» ምንም እንኳ ኢየሱስ ጥያቄውን ያቀረበው ለሁሉም ቢሆንም እንደ ተለመደው ሁሉንም በመወከል የመለሰው ጴጥሮስ ነበር:: አልፎ አልፎ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን ተናግሮ ነበር (ማቴ 16÷22-23፤ 26÷31-35፤ ዮሐ 13÷6-11):: አንዳንዴ ደግሞ በከፍተኛ ማስተዋል ተናግሮ ነበር (ማቴ 14÷28-31፤ 16÷16-18፤ ዮሐ 6÷68-69፤ ሐሥ 2÷14):: ይሁን እንጂ ከዚህ የበለጠ ጴጥሮስ አንዴም እንኳ በከፍተኛ ማስተዋል የተናገረበት ጊዜ ሊኖር አይችልም:: ቀደም ሲል ጴጥሮስ ቀዳሚ ምስክርነት ሰጥቶ ነበር (ዮሐ 6÷69) ሆኖም መሲሕነቱን በሚገባ ለመረዳት ሌሎች



መገንዘብ የነበረበት ሁኔታዎች ነበሩ (ቊ 22-23):: ይሁን እንጂ፣ በተለይ ኢየሱስ ከሰጠው ምላሽ አንጻር ይህ ቀላል የሚመስል ምስክርነት ምን ያህል ጥልቅና ምጡቅ ለመሆኑ ማን ሊክድ ይችላል::

«ክርስቶስ» - «መሲሕ» የሚለው ዕብራይስጥ ቃል የግሪኩ አቻ ትርጉም ነው:: ሁለቱም፣ «የተቀባ» የሚል ትርጉም አላቸው:: በዕብራይስጡ አመለካከት ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ እግዚአብሔር በሚያስታጥቀው ኀይል ለመፈጸም «መለየትን» ያመለክታል:: በዋነኛነት ደረጃ አንድ ሰው ራስ ላይ ዘይት ማፍሰስ የሚያመለክተው ለነቢይነት፣ ለክህነትና ለንጉሥነት መለየቱን ነበር (ዘፀ 29÷7፣21፤ 1ሳሙ 10÷1፣6፤ 16÷13፤ 2ሳሙ 1÷14፣16):: ሦስቱም ሥልጣኖች ኢየሱስ ለክርስቲያኖች የሚሰጠውን አገልግሎት ያመለክታሉ:: የኢየሱስን ነቢይነትና ክህነት ብዙዎች በደስታ ይቀበላሉ፤ በጣም የሚያሳዝነው ግን ብዙ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች በሕይወታቸው እንዲነግሥ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው:: ከሦስቱ ሁለቱን የመምረጥ ዕድል አልተሰጠንም:: ስለሆነም፣ «ክርስቶስ» የአይሁድ መሲሕ ታዋቂ መለያ ሆኗል:: ይህ ብቸኛ ሰው እስራኤልን ከባርነት ነጻ ሊያወጣና ግዛቷን በምድር ሁሉ ላይ ሊያሰፋ ነው (ከዳን 9÷25-27 ጋር ያነ)::[57]

«የሕያው እግዚአብሔር ልጅ» - «ክርስቶስ» የተሰኘውን ያህል የተለየ መጠሪያ ነው:: ይህ መጠሪያ የተገኘው ሙት ከሆኑ የአሕዛብ አማልክት ጋር በሚቃረን መልኩ እግዚአብሔር «ሕያው» ነው ከሚል የአይሁድ አስተሳሰብ ነው:: ስለዚህ ጴጥሮስ እየተናገረ ያለው ዐሥራ ሁለቱን ብቻ ሳይሆን መላው የአይሁድ ሕዝብን በመወከል ነበር::

---

[57] ነጻ የሚያወጣ መሲሕ እንደሚመጣ አይሁድ የነበራቸው ተስፋ በዋነኛነት የሚገኘው በተራው ሕዝብ እንጂ በእስራኤል መሪዎች ዘንድ አልነበረም:: ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን የተለያዩ መሲሐዊ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፤ አንዳንዶቹም፣ «የአይሁድ ንጉሥ» በመባል ተጠርተዋል:: (R.A. Horsley, "Like one of the Prophets of Old": Two Types of Popular Prophets at the Time of Jesus," *CBQ* 47 (1985): 435-463 ይመ):: ይሁን እንጂ «የኢየሱስ እንቅስቃሴ» የተለየ ነበር:: እርሱ ሰላማዊና የሚመጣው ዓለም መሪ ነው::

ማቴ 16፥17-18

17ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «የዮና ልጅ ስምዖን
ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ
እንጂ ሥጋና ደም አይደለም። 18አንተ ጴጥሮስ ነህ፤
በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም
ደጆችም አያሸንፏትም።

የኢየሱስ ምላሽ የጴጥሮስ ምላሽ ተጓዳኝ ነው። ጴጥሮስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ተናገረ፤ ኢየሱስ ደግሞ ጴጥሮስ የዮና ልጅ መሆኑን ተናገረ (ዮሐ 21፥15፤ «የዮሐንስ» ይላል)። ጴጥሮስ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ተናገረ፤ ኢየሱስ ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት መሆኑን ተናገረ። ይህን ያህል ግልጽ ነው። ቍጥር 18 ግን በመጠኑም ቢሆን ነገሮችን ያወሳስባል። ለመሆኑ፣ ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን፣ «ዐለት» መሆን ምን ድረስ ነው? እንዲህ ሲባል ጴጥሮስ ሐዋያዊ የሥልጣን ተዋረድ ያለወ የመጀመሪያው ጳጳስ ነው ማለት ይሆን? ይህ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አቋም ነው። ፕሮቴስታንቶች ግን ይህን ተቃውመዋል። የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነወ ጴጥሮስ ሳይሆን የእርሱ ምስክርነት ነው በማለት ይከራከራሉ። ለዚህ አባባላቸው መሠረት የሚደርጉት ኢየሱስ ስለዚህ በሚናገርበት ጊዜ ጴጥሮስ - (*Petros*) ከሚለው ተባዕታይ መጠሪያ፣ ፔትራ [ዐለት] (*Petra*) ወደሚለው አንስታይ መጠሪያ ዘወር ማለዩን ነው። በተጨማሪም 'ፔትሮስ' ትንሽ ጠጠር እንደ ማለት ሲሆን 'ፔትራ' ግን ግዙፍ ዐለት መሆኑን ይናገራሉ። ስለሆነም የኢየሱስን ንግግር የሚረዱት፣ «ጴጥሮስ አንተ ትንሽ ዐለት ነህ (ከዮሐ 1፥42 ጋር ያነ፤ በተጨማሪ 1ቆሮ 15፥5፤ ገላ 1፥18 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ምስክርነትህ እጅግ ታላቅ በመሆኑ በዚያ ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ» በሚል መልኩ ነው (1ጴጥ 2፥5-8 ጋር ያነ)።



ይሁን እንጂ በፔርሶስና በፔትራ መካከል ያለውን ረቂቅ ልዩነት በሚገባ ማየት የሚቻለው በግሪኮች ቅኔ ውስጥ ነው። እዚህም ላይ ቢሆን አንድምታው አጠያያቂ ነው። ከዚህም በተረፈ ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው በአረማይክ ቋንቋ ነበር። ሌላው ቢቀር እንኳ ጴጥሮስን፣ «ባርጆና» በማለት የጠራው ጊዜ የተጠቀመው በአረማይክ ቋንቋ ነበር። አረማይኩ፣ «ዐለት» ለማለት ግሪኩ የሚጠቀምባቸው ቃላት መካከል ያሉ ልዩነቶች ዓይነት የረቀቀ ልዩነት አያደርግም። ኬፋ (*kepha*) በሚለው አንድ ቃል ብቻ ነው የሚጠቀመው። ከዚህም በላይ ጴጥሮስ «ዐለት» ባይሆን እንኳ አሁንም ቢሆን፣ «የመንግሥተ ሰማይ መክፈቻዎች» በእርሱ እጅ ናቸው (ቍ 19)። ያም ቢሆን መብራራት ይኖርበታል።

በሌላ በኩልም የመጀመሪያው ጳጳስ በመሆነ ጴጥሮስ ዋነኛ ነው የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት የሌለው ነው። የሐዋርያት ሥራ ጴጥሮስ የጵጵስና ሥልጣን እንደ ነበረው አያመለክትም (11፥2፤ 15፥13-21፤ 21፥18፤ በተጨማሪ ገላ 2፥14 ይመ)። ሐዋርያዊ ሥልጣን ተዋረድ፣ ጴጥሮስ በሕይወት የነበረውን ዮሐንስ ችላ ብሎ ትእዛዙን ለሌላ ደቀ መዝሙር እንዲያስተላልፍ ሊያደርገው ይችላል። ይህን ጨምሮ ሌሎች ይህን የመሳሰሉ አስተምህሮዎችን አጥጋቢ በሆነ መልኩ የሚደግፍ ከአዲስ ኪዳን አንድም ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም።?

ስለዚህ የምንደመድመው ጴጥሮስ ዐለት ቢሆንም እንካን፣ የመጀማመሪያው ጳጳስ እንዳልነበር በማመልከት ነው። የጴጥሮስ ሥራ ድርሻ ምን እንደ ነበር ከታች ገለጻ ተሰጥቶበታል። እዚህ ላይ ግን ቤተ ክርስቲያን የዐሥራ ሁለቱ ተወካይ በነበረው ጴጥሮስ ላይ ተመሥርታለች ማለቱ ይበቃል (ከኤፌ 2፥20 ጋር ያነ)።

«ቤተ ክርስቲያን» [*ekklesia*] ጥምር ቃል ሲሆን፣ ሥርወ ቃሉ፣ «ተጠርተው የወጡ» እንደ ማለት ይሆናል። በወንጌሎቹ ውስጥ ጥቅም

ላይ የዋለው ሦስቴ ብቻ ነው (ማቴ 16÷18፤ 18÷17 [ሁለቴ]):: አንዳንዶች ለዚህ ሥርወ ቃል አጽንዖት በመስጠት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ «ከጨለማ ተጠርታለች» ስለዚህ፣ «ከዓለም መለየት» ይኖርባታል ይላሉ:: ይሁን እንጂ ቃሉ ጉባዔ እንጂ ሌላ ምንም ማለት ባለ መሆኑ ጉባዔው አንዳንዴ የአረማውያን (ሐሥ 19÷32)፣ አንዳንዴ ደግሞ የክርስቲያኖች ሊሆን ይችላል:: ከግሪኩ ሥርወ ቃል ይልቅ በጣም ጠቃሚው ቃሔል (*qahal*) የተሰኘው የዕብራይስጡ ቃል ሲሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባዔን ያመለክታል:: «ጉባዔ» ወይም «ቤተ ክርስቲያን» - የእግዚአብሔርን ዓላማ፣ የሥራ ዝርዝርና ሥልጣን የሚጋሩ የእግዚአብሔር መንግሥት ተወካዮች ናቸው::



ክፉው ዜና ይህ፣ «የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባዔ» በቅርቡ፣ «ከገሃነም ደጆች» ጋር የሚጋፈጥ መሆኑ ነው:: መልካሙ ዜና ቤተ ክርስቲያን በፍልሚያው አሸንፋ መውጣቷ ነው:: ጥያቄው ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ምንድነው? የሚለው ነው:: የተለያዩ አመለካከቶች ሊኖሩ ይችላሉ::[58] ለግንዛቤ ያህል ግን ቢያንስ ይህን ማወቅ አለብን፤ (1) በመሠረቱ፣ «ደጆች» የሚውሉት ጥበቃ እየተደረገለት ላለ ምሽግ ነው:: እዚህ ላይ ግን፣ «ኀይልን» ለማመልከት ነው ጥቅም ላይ የዋለው:: ስለሆነም የገሃነም ደጆች አጥቂ ወይም ተከላካይ ሊሆኑ ይችላሉ:: (2)

58 አንዳንድ የተለመዱ ሐሳቦች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤ (1) የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የቤተ ክርስቲያን ውድቀት አይደለም (ደጆቹ አጥቂ ቢሆኑም):: የኢየሱስ ትንሣኤ የሰይጣንን ኀይል - ሞትን ይሽራል፤ ራእ 1÷18 (በተከላካይነት ቢሰለፉም):: (2) የመጨረሻው ቀን ትንሣኤ እንደ ገና ለመንግሥቱ ሕያዋን ስለሚያደርጋቸው የቅዱሳን ሞት የቤተ ክርስቲያን መጥፋት አይደለም (ጥቃት ቢኖርም):: (3) ሰማዕትነት ቤተ ክርስቲያንን አያጠፋም:: አምብሮስ እንደሚለው፣ «የቅዱሳን ደም፣ የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው» (ጥቃት ቢኖርም):: (4) ሰይጣን የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት መግታት አይችልም:: ማደጓንና በዚህ ምድር የእግዚአብሔርን መንግሥት መመሥረቷን ትቀጥላለች (የሚቋቋም ኀይል ቢኖርም):: ክርስቲያኖች፣ በተለይ፣ «ኀይል የታጠቁት» ሰይጣንና አጋንንታዊ አሠራርን ያሸንፋሉ (መከላከሉ ቢኖርም)::



«ሀዴስ» የግድ የገሃነም አቻ ትርጉም እንደሆነ መወደስ የለበትም:: በመደበኛነት የሙታን መኖሪያን ሲያመለክት፣ ሰፋ ባለ መልኩ ደግሞ ሞት ራሱን ያመለክታል (ኢዮ 17÷16፤ 38÷17፤ መዝ 9÷13፤ 107÷18፤ ኢሳ 38÷10):: (3) ከገሃነም ደጆች ጋር የሚፋለሙት ኢየሱስ ወይም ጴጥሮስ ሳይሆኑ መላው ቤተ ክርስቲያን ናቸው:: ስለሆነም ይህን በሚመስል መደምደሚያ እንቋጫለን - የገሃነም ደጆች ቤተ ክርስቲያንን አያሸንፏትም:: መስቀል ወይም ሰማዕትነት የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ያስፋፋሉ::

**ማቴ 16÷19-20**

19የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤
በምድር ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤[59]
በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል::
20ቀጥሎም እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ለማንም እንዳይናገሩ
ደቀ መዛሙርቱን [ለጥብቆ[ሰቃ]] አስጠነቀቃቸው::

«መክፈቻዎች» አንድ ዐይነት ሥልጣን እንደሚወክሉ ግልጽ ነው፤ ግን ምን ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን? ሐየርስ[60] የሚከተሉትን ጨምሮ አንዳንድ አስተያየቶችን አቅርቧል::

(1) የሃይማኖት መምህራን ከስዕለት ዕዳ የመፍታት ሥልጣን (ሆኖም ከማቴ 5÷33-37 ጋር ያነ)::
(2) የሃይማኖት መምህራን ነገሮች የተፈቀዱ ወይም ያልተፈቀዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሥልጣን (ሆኖም ከማቴ 23÷8 ጋር ያነ)::

59 J.R. Mantey, "Evidence that the Perfect Tense in John 20:23 and Mt 16:19 is Mistranslated," *JETS* 16 (1973).
60 R.H. Hiers, "Binding and Loosing: The Matthean Authorization," *JBL* 104 (1985): 233-250.

(3) የሥነ ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን (ማቴ 18÷18፤ 1ቆሮ 5)::

(4) በአሁኑ ጊዜ ኀጢአትን ይቅር ማለት (ዮሐ 20÷23፤ ይሁን እንጂ ከማቴ 5÷23-26፤ 6÷12-15፤ 18÷21-35 ጋር ያነ)፣ ወይም በፍርድ ጊዜ (ማቴ 10÷23፤ 11÷20-24፤ 19÷28)::

(5) በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በነበረው ዘመን፣ «ማሰር» እና፣ «መፍታት» የተሰኙ ቃላት ጥቅም ላይ በዋሉበት መሠረት አጋንንትን ማስወጣት (ጦቢት 3÷17፤ 8÷3፤ Josephus *Ant.* 8.2.5)::

በሐዋርያት ሥራ ካሉ ብዙ ማስረጃዎች ጋር የሚጣጣም ሐየርስ ያላነሣው አንድ አማራጭ የጴጥሮስ ወንጌልን መስበክ ነው (ሉቃ 11÷52):: ለአይሁድ ቤተ ክርስቲያን (ሐሥ 2) እና ለአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን (ሐሥ 10፤ 15÷7 ጋር ያነ) «በር የከፈተ» ጴጥሮስ ነበር:: ይህ መፍታትና ማሰር ስላለው አንድምታ በቂ ምክንያት ላይሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ረጅም ርቀት ያስኬደናል:: ከላይ የተመለከትነው ሁለተኛው አማራጭ፣ በተለይም በቀኖናውያን መጻሕፍት አንጻር ከተመለከትነው ብዙ የቀሩ ነጥቦችን ሊሸፍን ይችላል:: አማራጭ 3ትም ቢሆን፣ ሐሥ 4÷11-12፤ 5÷3-10፤ 8÷20-21፤ 13÷51-52፤ 28÷28 በመሳሰሉ ምንባቦች የሐዋያት፣ «ማሰር» ሥልጣንን በተመለከተ የራሱ ድርሻ አለው::

በተጨማሪም መክፈቻዎች ያሉት ጴጥሮስ ብቻ ነው በማለት ማሰብ የለብንም:: እዚህ ላይ የሐዋርያቱ አፈ ጉባዔ ሆኖ እናያለን (ከማቴ 15÷15-16፤ 19÷25-29፤ 26÷40፤ ማር 11÷20-22፤ ሉቃ 12÷41፤ ዮሐ 6÷67-70 ጋር ያነ):: በሐዋርያት ሥራ 2 እና 10 ሁነኛ ስፍራ ይዞ የምናየውም እርሱ ነው:: ዮሐንስ አፈወርቅ ጴጥሮስን፣ «የሐዋርያቱ አንደበት» በማለት ጠርቶታል:: ይሁን እንጂ ይህ ዋነኛነቱ



የቅደም ተከተል እንጂ የሥልጣን መበላለጥ ጉዳይ አይደለም::[61] ሌሎቹ ሐዋርያትም ወንጌል በማስፋፋት ሥራ፣ (ሐሥ 2÷4፣14)፣ (ሐሥ 5÷18) መተዳደሪያዎችን በማውጣት (ሐሥ 6÷2) በአስተምህሮ (ሐሥ 2÷42፤ 8÷14፤ 15÷10፣22-28) እና ሌሎችም ሁሉ እኩል ይሳተፋሉ (ኤፌ 2÷20)::

እዚህም ላይ ኢየሱስ ዝም እንዲሉ ተናግሮአል፤ ይህን ያደረገው ግን መሲሐዊ መገለልን ለማድበስበስ አልነበረም:: የክርስቶስ ምስክርነት ይህን ያህል ከባድ ሳይሆን፣ አብዛኛው ሕዝብ እንዳይቀበለው ጊዜውን የጠበቀ አለመሆኑ ነው::

**§83**
**ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሞቱ በግልጽ መናገሩ**
**ማቴ 16÷21-23፤ ማር 8÷31-33፤ ሉቃ 9÷22)**

በተዘዋዋሪ መልኩም ቢሆን ኢየሱስ ስለ ሞቱ ደጋግሞ ተናግሮአል (ዮሐ 1÷29፤ 2÷19፤ 3÷14፤ ማቴ 9÷15፤ 10÷38-39፤ 12÷39-40):: ደቀ መዛሙርት ግን አልተረዱም:: አሁን ግን የኢየሱስን ማንነት በመረዳታቸው መሲሑ ለእነርሱ የሚያደርገውን እንዲያውቁ በግልጽ ሊነግራቸው ይገባል::

[ማቴ]21ኢየሱስ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ፣ በዚያም [የሰው ልጅ[ማር]] በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በኦሪት ሕግ መምህራን እጅ መከራን ይቀበልና [እንደሚናቅ[ማር]] ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን [ከሦስት ቀንም በኋላ[ማር]] ከሞት ይነሣ ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጽላቸው ጀመር [በግልጽ ነገራቸው[ማ]]::

---

[61] በማቴዎስ መሠረት በመጀመሪያ የተጠራው ጴጥሮስ ነበር (4÷18-20)፣ ምንጊዜም በሐዋርያቱ ዝርዝር ውስጥ የመጀመሪያውም እርሱ ነው (10÷2-4):: ገላትያ 2÷11 ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር የቤተ ክርስቲያን፣ «አዕማድ» ከሚባሉት ዝርዝር ውስጥ አስፍሮታል::

ይህ ሁኔታ ዐሥራ ሁለቱን በማስተማር ረገድ አዲስ ጅማሬ ነው::[62] «ከዚያን ጊዜ ጀምሮ» ኢየሱስ በቅርቡ ስለሚፈጸመው ሞቱ በግልጽ ይናገር ጀመር:: ጴጥሮስ ከተናገረው ማየት እንደሚቻለው ሐዋርያቱ ኢየሱስ መሲሑ መሆኑን ከመረዳታቸው የተነሣ አሁን ደግሞ ጌታ ስለ መሲሑ ሥራ አስተሳሰባቸውን ማዘጋጀት ጀምሯል:: ሰብዓዊ ሠራዊት ያለው ምድራዊ መንግሥት ጠብቀው ነበር:: ሰማያዊ ሠራዊት ያለው መንፈሳዊ መንግሥት ሊያገኙ ነው:: ድል በሚነሣ ንጉሥ አማካይነት ከሮም ነጻ መሆንን ጠብቀው ነበር:: ከሞት በሚነሣው ጌታ አማካይነት ከኀጢአት ነጻ መሆንን ሊያገኙ ነው:: እነርሱ ተስፋ ካደረጉት ይልቅ በጣም የተሻለ ቢሆንም፣ ይህን ሁሉ ለመገንዘብ ግን ጊዜ ይጠይቃል:: እዚህ ላይ መጀመር አለበት::

«የሰው ልጅ» የሚለው በወንጌሎቹ 81 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፤ የተጠቀመበት ኢየሱስ ብቻ ስለ ራሱ ሲናገር ነው:: «የሰው ልጅ» የሚለው በብሉይ ኪዳን[63] ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ቢውልም በገንቢ ጐኑ አልነበረም:: የሰውን፣ «ሰብዓዊነት» ማለት በአካል፣ በጊዜና በአእምሮ ውሱን መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት ነበር ጥቅም ላይ የዋለው (ዘኍ 23÷19፤ ኢዮ 25÷6፤ መዝ 8÷4፤ 144÷3):: ዳንኤል 7÷13-14 ያልተለመደ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው:-

> ሌሊት ባየሁት ራእይ፣ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመና ጋር ሲመጣ አየሁ፤ ወደ ጥንታዊ ጥንቱ መጣ፤ ወደ ፊትም አቀረቡት:: [14]ሥልጣን፣

---

[62] በማቴዎስ ወንጌል፣ ይህ "*apo tote*" የተሰኘ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ሁለቴ ብቻ ነው:: 4÷17 ላይ የኢየሱስ ስብከት አገልግሎት መጀመሩን ለማመልከት፣ ከጥምቀቱና ከፈተናው በኋላ ጥቅም ላይ ውሏል:: በ26÷16 ደግሞ ሠላሳ ብሩን ከተቀበለ በኋላ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ያደረገውን ሙከራ ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል::

[63] «የሰው ልጅ» የሚለው አንድ መቶ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ዘጠና ሦስቱን የምናገኘው ትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ ነው:: አምላክነቱን ከሕዝቅኤል ሰብዓዊ ፍጡርነት ጋር ለማነጻጸር ለሕዝቅኤል የተሰጠ መጠሪያ ነበር::



> ክብርና ታላቅ ኀይል ተሰጠው፤ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች፣ መንግሥታትና ሕዝቦች ሰገዱለት፤ ግዛቱም ለዘላለም የማያልፍ ነው፤ መንግሥቱም ፈጽሞ የማይጠፋ ነው::

እዚህ ላይ ይህ፣ «ሰው - መሰል» ፍጡር፣ እግዚአብሔር ብቻ የሚያደርገውን ነገር ሲያደርግ እንመለከታለን (ለምሳሌ በሰማይ ደመና ላይ መሆን):: ይህ ሰብዓዊ/መለኮታዊ ሰው በምሳሌያዊ መልኩ ትስጉትን ያመለክታል:: ኢየሱስ ይህን መጠሪያ ለራሱ የተጠቀመበት በዚህ ምክንያት ነው:: ዳንኤል 7÷13 የሚናገርለት፣ «የሰው ልጅ» እርሱ ነው:: ይህ መጠሪያ የኢየሱስን መለኮታዊ ባሕርይ ከማመልከት ያለፈ ነው:: የኢየሱስን፣ «ፍጹም ሰው» መሆንንም ያመለክታል:: ሕማምን፣ ብቸኝነትን፣ በሰዎች መካድን፣ መፈተንን፣ ውሱንነትን የመሳሰሉ እኛን የሚሰሙን ነገሮች እርሱንም ስለሚሰሙት በእርግጥ ይረዳናል:: በድካማችን ስለሚራራ (ዕብ 4÷14-16)፣ ፍጹም ወደ ኋላ የማይል ጠበቃችን ነው (ሮሜ 8÷31-35)::

ማቴዎስና ማርቆስ ኢየሱስ የተናገረውን በግልጽ አቅርበዋል:: ማቴዎስ፣ «ይገልጽላቸው ነበር» [*deiknymi*] በሚል ቃል ተጠቅሟል፤ ይህም፣ «ማመልከት፣ በማስረጃ አስደግፎ ማሳየት» ማለት ነው:: ማርቆስ፣ ኢየሱስ «በግልጽ» ወይም «በድፍረት» [*parresia*] (8÷32) ነገራቸው ይላል:: ኢየሱስ ስፍራውን (ነቢያትን በመግደል የምትታወቀው ኢየሩሳሌም ማቴ 23÷2)፣ መከራውን (መናቁን፣ መገደሉንና ከሞት መነሣቱን) እና ስለሚገድሉት ሰዎች (በአይሁድ ሸንጐ አባሎች) አመልክቷል:: ከላይ የተጠቀሱ ሦስቱ ቡድኖች በአንድነት የአየሁድ ሸንጐ አባሎች ይሆናሉ:: ሽማግሌዎች የተባሉት ማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያሉ መሪዎች ናቸው:: ሊቀ ካህናት፣ የቤተ መቅደሱ፣ «አስተዳዳሪዎች» ሲሆኑ፣ ይህም ከሰዱቃውያን ጋር የሚመጣጠን ደረጃ

ነው። ጸሐፍት በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያሉ ጠበቆችና መምህራን ሲሆን፣ ይህ ከፈሪሳውያን ጋር የሚመጣጠን ደረጃ ነው።

የእግዚአብሔርን እቅድ ለመፈጸም ብቻ ሳይሆን፣ የእኛን ኀጢአት ለመክፈል ጭምር የኢየሱስ መሞት አስፈላጊ [*dei*] ነበር።[64] ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረውን አስመልክቶ በእርሱ ላይ በየጊዜው እየበረታ ከመጣው ጥላቻና ተቃውሞ አንጻር የእርሱ መገደል የሚጠበቅ ነበር። ማንም እንደሚገምተው እንዲህ ያለው ወሳኝ ጉዳይ በሁለቱም ኪዳኖች ትንቢት ተነግሮለት ነበር።[65] ኢሳይያስ 53÷7-12፤ መዝሙር 22 እና ዘካርያስ 13÷6-7 የመሳሰሉ ምንባቦች ቢያመለክቱም እንኳ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ በኀጢአተኞች ምትክ እንደሚሞት በፍጹም አልጠረጠሩም ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳ ኢየሱስ ስለ ራሱ ሞት በግልጽ ትንቢት ቢናገርም፣ ሐዋርያቱ በሚገባ አልተረዱትም ነበር (ማቴ 12÷40፤ 16÷4፣21፤ 17÷11-13፣22፤ 20÷17፤ 21÷33-39፤ 26÷2)።

ኢየሱስ ከሞተ በኋላ ዐሥራ ሁለቱ እነዚህን ቃላት አስታውሰው ትንሣኤውን ይጠብቃሉ በማለት እናስብ ይሆናል። ሆኖም ግን የምናየው ያንን አይደለም የምናየው። አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ትንቢቶች ሁኔታው ከተፈጸመ ዐሥርት ዓመታት በኋላ በኦርትዖት የተጨመሩ ናቸው ይላሉ። እርግጥ ነው ይህ ሐዋርያቱ ትንሣኤውን ተስፋ ያላደረጉበትን ምክንያት ይገልጽልናል። ሆኖም የሚከተሉትንም ይክዳል፤ (1) የኢየሱስን የወደፊቱን የመተንበይ ችሎታ፤ (2) መንፈስ ቅዱስ

[64] ስለ ክርስቶስ የምትክነት ሞት ማብራሪያ ለማግኘት ከ76ሀ ለዮሐ 6÷48-51 የተሰጠውን ገለጸ ይመ።

[65] ዘፍ 3÷15፤ መዝ 22÷1፤ ኢሳ 53÷7-12፤ 63÷1-6፤ ዘካ 13÷6-7፤ ማቴ 9÷15፤ 10÷38-39፤ 12÷39-40 [እና ሉቃ 11÷30]፤ 16÷21 [እና 9÷22]፤ 20÷18-19 [እና ማር 10÷33-34፤ ሉቃ 18÷31-33]፤ 26÷2፤ ማር 8÷31፤ 9÷9፣31፤ 10÷38-39፤ ሉቃ 2÷34፤ 5÷35፤ 12÷50፤ 17÷25፤ 22÷15፣37፤ ዮሐ 2÷19፤ 3÷14፤ 6÷53፤ 10÷11፤ 12÷7፣32-33፤ 14÷19፤ 15÷13፤ 16÷20።



ለወንጌላውያኑ ስለ እነዚህ ነገሮች እንዲያስቡ ለማድረግ ያለውን ችሎታ፤ (3) የአራቱን ወንጌል ጸሐፊዎች ታማኝነትና ቅንነት። እንዲህ ያለው የግምት አነጋገር አስፈላጊ አይደለም፤ ከፍ ያለ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

ኢየሱስ እነዚህን ቃላት ተናግሮአል ብንል እንኳ ደቀ መዛሙርቱ ከሞት ይነሣል ብለው አለመጠበቃቸውን ምን ምክንያት ልንሰጠው እንችላለን? በመጀመሪያ፣ እርሱ ቃል በቃል ሲናገር በምሳሌያዊ ሁኔታ፣ በምሳሌ ሲናገር ደግሞ ቃል በቃል የሚረዱ ደቀ መዛሙርቱን ጨምሮ ብዙ አድማጮች ነበሩት (ለምሳሌ፣ ዮሐ 2÷19-20፤ 3÷3-4፤ 6÷51-52፤ 7÷34-35፤ 8÷51-52፤ 11÷11-12፣23-24፤ 14÷4-5)። እነዚህን ቃላት ሲናገር በምሳሌያዊ ሁኔታ እየተናገረ ያለ መስሏቸው ይሆናል። ሁለተኛ፣ ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሲናገር ሰምተዋል ማለት፣ የግድ ተረድተውታል ማለት አይደለም። ኢየሱስ ስለ ሞቱ ከተናገረ በኋላ ቀጥሎ የሚናገረው ይህን ያህል ግምት ውስጥ አልገባም። ዐሥራ ሁለቱ ኢየሱስ ስለ ሞቱ የተናገረውን ብቻ ሲያሰላስሉ፣ ነገሩ እስከ ተፈጸመ ድረስ ስለ ትንሣኤው የተናገረውን ችላ ብለው ይሆናል። በመጨረሻም፣ በተነገረው ትንቢት መሠረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ከሞት ከመነሣታቸው በፊት አንድ ሰው ስለ ራሱ ትንሣኤ መናገሩ በፍጹም ያልተለመደ ነበር።

ማቴ 16÷22-23
ከማር 8÷33 ጋር

[22]ጴጥሮስም ኢየሱስን ወደ ጐን ሳብ አድርጐ፣
«ጌታ ሆይ፣ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ አይድረስብህ» እያለ
ይገሥጸው ጀመር።
[23]ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ዞወር ብሎ [ደቀ መዛሙርቱን
እያየ[ማር]] «አንተ ሰይጣን፣ ሂድ ከዚህ! የሰው እንጂ የእግዚአብሔር ነገር በሐሳብህ ስለ
ሌለ መሰናከል ሆነህብኛል» አለው።

ኢየሱስ በተናገረለት መልካም ነገር ተኩራርቶ የነበረው ጴጥሮስ ጠንከር ባለ አነጋገር ይቃወመው ጀመር። «ጌታ ሆይ፣ እንዲህ ያለ ነገር

ፈጽሞ አይድረስብህ» [*hileos soi, kyrie*] ያለ ሲሆን፣ ቃል በቃል፣ «እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ» ማለት ነው። ይሁን እንጂ የኋላ ኋላ፣ «እግዚአብሔር አይበለው!» ማለት ሆኗል። ችኩሉ ጴጥሮስ ነገሮች ከቁጥጥሩ ውጪ ከመሆናቸው በፊት ሊይዛቸው ይፈልጋል። ኢየሱስ ማን መሆኑን በሚገባ ተረድቷል ... ወይም እንደዚያ ያስባል! የጴጥሮስ ዓላማ ንጹሕ እንደ ነበር መዘንጋት የለብንም። አላዋቂነቱ በከፍቅር የመነጨ ነበር ... ብዙ ጊዜ ከፍ ያለ ስሕተቶችም እንዲሁ የሚመጡ ናቸው።

ጴጥሮስ በሁሉም ፊት እንደ ተደነቀ ሁሉ፣ በሁሉም ፊት ተገሠፀ። ኢየሱስ ዘወር አለና ዐሥራ ሁለቱ እያዩ ጴጥሮስን፣ «ሂድ ከዚህ!»[66] አለው። «ሰይጣን» የሚለው ቃል፣ «ከሳሽ» ማለት ነው። ኢየሱስ ጴጥሮስን ከምር ዲያብሎስ ብሎ መጥራቱ አልነበረም፤ ሆኖም ንጽጽሩ ግልጽ ነው። በምድረ በዳ በተፈተነበት ጊዜ ሰይጣን ለኢየሱስ ቀላሉን መንገድ፣ ያም ወደ ዝነኛነትና ብልጥግና የሚደርስበትን ፈጣን መንገድ አቅርቦለት ነበር። ጴጥሮስም ያንኑ ዐይነት ነገር ለኢየሱስ እየነገረ ነበር፤ «መሞት የለብህም። እንዲህ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም!» እያለው ነበር። ከአንድ ጌታ በላይ ሊኖር አይችልም። ፊት ለፊት እግዚአብሔርን የሚገጥም ሰው ራሱን መሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ ያገኘዋል። ጌታችን ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቃል። አነጋገሩ ያልተለመደ ወይም አስደንጋጭ ቢመስልም፣ ያ የሆነው ከእርሱ አለማወቅ ሳይሆን ከእኛ አለመረዳትና የአመለካከት ውሱንነት የተነሣ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሠረት፣ ዐለቱ ጴጥሮስ ብዙም ሳይቆይ የመሰናከያ ድንጋይ ሆነ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ታላቅ መገለጽ

[66] በማቴ 4÷10 ኢየሱስ፣ «አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ» ሲል የተጠቀመው በዚሁ ግሥ ነበር። እዚህ ላይ አንድምታው ጴጥሮስ ዘወር እንዲል እንጂ ጨርሶ እንዲርቅ አይደለም።



ተቀብሎ የነበረው ጴጥሮስ አስተሳሰቡ፣ «ከሰው» አስተሳሰብ ጋር ተቀላቀለበት። በከፊልም ቢሆን የጴጥሮስ ችግር በከፊልም ቢሆን እንደ አብዛኞቻችን ነው። ይህ የዐሥራ ሁለቱ አፈ ጉባዔ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው።

**§ 84**
**አንዳንድ የደቀ መዝሙርነት እንድምታዎች**
**(ማር 8÷34-9÷1፤ ማቴ 16÷24-28፤ ሉቃ 9÷23-27)**

[ማር8][34]ከዚህ በኋላ፣ ሕዝቡን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ «ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም [በየዕለቱ[ሉቃ]] ተሸክሞ ይከተለኝ፤ [35]ነፍሱን ለማዳን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋት ሁሉ ግን ያድናታል። [36]ሰው ዓለሙ ሁሉ የእርሱ ቢሆንና ነፍሱን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? [37]ስለሆኑ፣ ሰው ስለነፍሱ ምን መተኪያ አለው?

ኢየሱስ በሄደበት ሁሉ ትኩረትን ይስብ ነበር። ምናልባት ይህን ጉዞ የመረጠው በግል ለዐሥራ ሁለቱ ሥልጠና ለመስጠት ሊሆን ይችላል። ሆኖም እንደ ጢሮስና ሲዶና (ማር 7÷24)፣ እንደ ዐሥሩ ከተማ ጉዞው ሁሉ (ማር 8÷1)፣ ሕዝቡ እንደ ገና ኢየሱስን አግኝተዋል (ማር 8÷34፤ 9÷14)።

ማርቆስ 8÷34-35 (እና ማቴ 16÷24-25)፣ ማቴዎስ 10÷38-39ን ያስተጋባል (የ§70ለ ማብ ይመ)። መስቀሉን፣ «በየዕለቱ» መሸከም እንደሚገባ ሉቃስ ያቀረበው ተጨማሪ ቃል ዐረፍተ ነገሩን የማያያዝ ፋይዳ አለው። ከቍጥር 36-37 ያለውን በምንም መልኩ ብንረዳውም ለዚህ ዓለም ጊዜያዊ ደስታ ነፍስን መሸጥ አትራፊ ሊሆን አይችልም።

**ማር 8÷38-9÷1**
**ከማቴ 16÷27-28**
**ጋር**

[38]በዚህ ዘማዊና ኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅም በአባቱ ግርማ፣ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሲመጣ ያፍርበታል

[ለእያንዳንዱም ሰው እንደ ሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል[ማቴ]] [9:1]ቀጥሎም፣ «እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔር መንግሥት በኀይል ስትመጣ [የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ[ማቴ]] እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ» አላቸው::

ማርቆስ 8÷38 እንዲሁ ወደ ማቴዎስ 10 (ቍ. 32-33) በተለይም «የእጅን ወደ ማግኘት ሕግ» ይመልሰናል:: በዚህ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ከቆማችሁ፣ በፍርድም ቀን ከእርሱ ጋር ትቆማላችሁ:: ዋጋ ቢያስከፍልም ደቀ መዝሙርነት ጥሩ ያተርፋል:: ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ ቍጥር 38ም ዳንኤል 7÷13-14ን ያነሣል፤ እዚህ ላይ አጽንዖት የሰጠው ግን ለኢየሱስ አምላክነት ነው (ለምሳሌ ከመላእክቱ ጋር ስለ መምጣቱ፤ ከማር 13÷26፤ 14÷62 ጋር ያነ):: ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው እንደሚሰጠው ማቴዎስ የጨመረው፣ በሥራችን መሠረት እምነታችን የሚመዘን መሆኑን እንጂ፣ ድነት በሥራ የሚገኝ መሆኑን አያመለክትም:: አዲስ ኪዳን ደጋግሞ ፍርድ ከሥራ የተነሣ እንደሚፈጸም ይናገራል (ማቴ 25÷31-36፤ ዮሐ 5÷28-29፤ ሮሜ 2÷6-8፤ 2ቆሮ 5÷10፤ 1ጴጥ 1÷17፤ ራእ 20÷12-13)::

ከዚህ ክፍል ጋር ተያይዞ የሚነሣው ጥያቄ፣ «መንግሥቱ የምትመጣው መቼ ነው?» የሚለው ነው:: ኢየሱስን ሲያደምጡ ከነበሩ አንዳንዶች በሕይወት ስለሚኖሩ ያያሉ:: የተወሰኑ ሐሳቦች ቀርበዋል፤

(1) መለወጡ - ቀጥሎ የተጠቀሰው ሁኔታ (ከ2ጴጥ 1÷16-18 ጋር ያነ):: ሆኖም፣ ይህ የሆነው ከስድስት ቀን በኋላ ነበር:: በስድስት ቀን ውስጥ ብቻ ስለማይሞቱ ሰዎች መናገር ያልተለመደ ነው:: ስለዚህም ይህን አባባል፣ «በሕይወት ዘመናችሁ አንድ ቀን አንዳንዶቻችሁ የእግዚአብሔር መንግሥት ስትገለጽ ታያላችሁ» በሚል መልኩ ልንረዳው እንችላለን:: ይሁን እንጂ መለወጡ የቱንም ያህል የከበረ ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ነፀብራቅ ሊሆን አይችልም፣ ወይም ደግሞ፣ «እያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ዋጋውን» አላገኘም::

(2) በተጠቀሰው መሠረት የኢየሱስን ሞት፣ መቀበርና ትንሣኤ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ምናልባትም፣ ዕርገቱንና በዐለ ሃምሳንም ሊጨምር ይችላል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሁኔታዎችም ቢሆኑ፣ «ሞትን የማይቀምሱ ...» ለሚለው በጣም የቀረበ ቢሆንም፣ ለእያንዳንዱ፣ «እንደ ሥራው» ሲከፈለው በግልጽ አልታየም::

(3) በ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም መደምሰስ:: ይህ ከማቴዎስ 10÷23 እና እንደ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ከማቴዎስ 24÷27፣30 ጋር ይስማማል:: ምንም እንካ፣ «ሞትን የማይቀምሱ ...» ከሚለው ሐረግ ጋር ቢጣጣምም፣ በአሉታዊ መልኩ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መክፈሉን ቢያሳይም፣ ስለ መገለጡ (Parovsia) ከሚናገረው ከዐውዱ ሐሳብ ጋር አይጣጣምም (ከ2ተሰ 1÷7 ጋር ያነ):: በዚህ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ በእርግጥ በ70 ዓ.ም. ተመልሶ መጥቷል፣ እኛ ግን አምልጠናል ወይም ከተመለሰ በኋላ አነዳንድ የወደፊት እቅዶችን እየፈጸመ ነው በማለት አምነዋል:: ይህ ግን በጣም አጠያያቂ ነው::

(4) አንዳንዶች ይህ የሚያመለክተው ስለ ዳግም ምፅአት ነው፤ «እዚህ ከቆሙት ሰዎች መካከል» የሚለው ግን የሚያመለክተው በዚያ ጊዜ የነበሩ አድማጮቹን ሳይሆን የደቀ መዛሙርቱ ወራሾች ስለሚሆኑ የመጨረሻው ትውልድ ነው የሚል ሐሳብ አቅርበዋለ:: በጣም ርቆ

የሄደው አማራጭ ሐሳብ ደግሞ ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው ገና ወደ ፊት ስለሚኖሩ ደቀ መዛሙርቱ ሳይሆን፣ በስሕተት ቶሎ የሚመለስ ስለ መሰለው ነው ብለዋል::

(5) ከላይ ያሉት ሁለቱን ወይም ሦስቱን በአንድነት ማጣመር፤ ይህ «ወላዋይነት» ቢመስልም ወደ ፊት የሚገለጠው የመንግሥቱን ባሕርይ ግምት ውስጥ ስናስገባ ግን ምናልባት ኢየሱስ ይህን እያሰበ ሳይሆን አልቀረም::

**§ 85**
**መለወጡ**
**(ማቴ 17፥1-8፤ ማር 9፥2-8፤ ሉቃ 9፥28-36ሀ)**

መለወጡ የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት መደምደሚያ ነበር::[67] ሳይፌልድ እንደሚለው፣ «በልደቱና በመከራው መካከል ያለ ሁነኛ ሁናቴ ነበር» (ገጽ 925):: ከትንሣኤው በፊት ኢየሱስ በመለኮታዊነቱ አልታየም ነበር:: ከዚያ በላይ መለወጡ በአጭሩ የቀረበ ወንጌል ነው:: ናይርድ እንደሚለው፣ «መለወጡን በተመለከተ የሚቀርብ አጥጋቢ ገለጻ፣ ከጥምቀት፣ ከፊልጶስ ቂሣርያ፣ ከጌቴሴማኒ፣ ከስቅላት፣ ከትንሣኤ፣ ከዕርገትና ከዳግም መገለጡ ጋር ያለውን ተያያዥነት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል»::[68]

ቀደም ሲል ያየናቸውን ሦስት ዐቢይ ሐሳቦች እዚህ ላይ ከኋላ ወደ ፊት በሆነ ሁኔታ እናያቸዋለን:: (ሀ) የኢየሱስ መሲሐዊ ማንነት፣ (ለ) ስለ ኢየሱስ መከራ የተነገረ ትንቢት፣ (ሐ) መጪው ክብሩ:: እነዚህ ሁኔታዎች በፍጹም ሊፋቅ በማይችል መልኩ በጴጥሮስ አእምሮ ተቀርጸዋል፤ በኋላም ለኢየሱስ መለኮታዊነት እንደ ማስረጃ አቅርቧቸዋል (2ጴጥ 1፡16-18)::

**ሉቃ 9፥28**
**ማቴ 17፥1፤**
**ማር 9፥2 ጋር**

28 ኢየሱስ ይህን ከተናገረ ከስምንት ቀን ያህል በኋላ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ ሊጸልይ ወደ አንድ [ከፍ ያለ[ማቴ+ማር]] ተራራ ወጣ [ብቻቸውንም ነበረ[ማር]]::

ጴጥሮስ ታላቅ ምስክርነቱን ከሰጠ ሳምንት ያህል[69] በኋላ፣ በጣም ያቀርባቸው የነበሩትን ሦስቱን ደቀ መዛሙርት (ከማር 5፥37፤ 9፡2፤ 13፥3፤ 14፡33 ጋር ያነ) ለቅጽበታዊው መገለጽ ይዞአቸው ሄደ:: ሉቃስ ከሳምንት በፊት ኢየሱስ ስለ ራሱ የሰጠውን መገለጽ (9፡22-27) ከመለወጡ ሁኔታ ጋር አያይዞታል:: ሁለቱ መነጣጠል የለባቸውም:: እንደ ብዙዎቹ የዘመናችን ክርስቲያኖች ሁሉ ደቀ መዛሙርቱ አሸናፊ መሆንን በመናፈቅ ያደጉ ነበሩ፤ መሲሕ መጥቶ ድል እንደሚያደርግ ነበር የሚጠብቁት:: እውነቱ ግን መከራ ድል አድራጊ ለመሆን ብዙውን ጊዜ እንደ ቅድመ ሁኔታ መሆኑና፣ እንዲያውም ወደዚያ የሚያደርስ መንገድ መሆኑ ነው:: ኢየሱስ በሞቱ በኩል ድል ያደርጋል እንጂ ከሞት ለማምለጥ አይሞክርም:: ስለሆነም መለወጡ በቅርቡ ኢየሱስ ላይ

---

[67] የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችና ታሪኮች ከየት መጣ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ምሑራን ስለሚለወጡ የቀረበው በመሠረታዊ ሁኔታ የተለወጠ የትንሣኤ ታሪክ ነው ይላሉ:: ስቴይን እንደሚለው ይህ ንድፈ ሐሳብ አሳማኝ አይደለም:: (R.H. Stein, "Is the Transfiguration (Mk 9:2-8) A Misplaced Resurrection-Account?" *JBL* 95(1976): 76-96 ጋር ያነ)::

[68] G.B. Caird, "The Transfiguration, "*ExpT* 67 (1955-56): 292.

[69] በማቴዎስና በማርቆስ፣ «ስድስት ቀኖች» እና በሉቃስ፣ «ስምንት ቀኖች» መካከል ያለው ልዩነት ይህን ያህል አሳሳቢ አይደለም:: ሁለቱም አንድ ሳምንት የሚያህል ጊዜን ለማመልከት የተጠቀሙበት ነው:: ምናልባትም ሕጉ እስኪሰጥ ድረስ ሙሴ በሲና ተራራ ያሳለፈውን ጊዜ በተዘዋዋሪ የሚመለከት ሊሆን ይችላል (ዘፀ 24፥15-16):: ከዚህም በላይ ብዙውን ጊዜ በሴማውያን ጽሑፎች ውስጥ «ስድስት ቀኖች» ወደ ሰባተኛው ቀን መዳረሻ የሚወስድ ሁኔታን ለመግለጽ ይጠቀሙበታል (F.R. McCurley, "And After Six Days' (Mk 9:2): A Semitic Literary Device," *JBL* 93 (1974): 67-81 ጋር ያነ):: ስለሆነም ማቴዎስና ማርቆስ አንባቢዎቻቸው የበለጠ ትልቅ ነገር እንዲጠብቁ እያመለከቱ ነው::

በሚደርሰው መከራ ተስፋ ለቆረጡ ደቀ መዛሙርት፣ ስለ ኢየሱስ የወደፊት ሕይወት የሚያሳስባቸው ነበር::

በተለምዶ እንደሚታሰበው የተለወጠው ታቦር ተራራ ላይ ሲሆን (1,929) ትልቅ የሚባልም ተራራ አይደለም:: ከጥቂት ዓመት በኋላ ሮማውያን በዚያ ቦታ ምሽግ ሠርተው (Josephus, *War* 11,20.6) ነበር፤ ምናልባትም በዚህ ጊዜ እንኳ ሳይኖር አይቀርም:: በቅርቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ያ ቦታ የቀርሜሎስ ተራራ (9,232) ሲሆን እንደሚችል በማሰብ ትኩረታቸውን ወደዚያ አድርገዋል:: ይሁን እንጂ ኢየሱስና አብረውት የነበሩ ሦስቱ በጣም አድካሚው የአርሞንኤም ተራራ ጫፍ ላይ ለመውጣት ወይም በዚያ ቅዝቃዜ ሌሊቱን እዚያ ለማሳለፍ ያን ያህል ጉልበታቸውን ጨርሰው እንደ ሆነ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል (ከሉቃ 9÷37 ጋር ያነ):: ከዚህም በተጨማሪ ላይፌልድ ከአርሞንኤም ተራራ የተመለሱት፣ «በገሊላ በኩል» (ማር 9÷30) ሊሆን እንደማይችል ይናገራል:: ይሁን እንጂ እስከ ተራራው ጫፍ ድረስ መሄዳቸውን የሚያመለክት ከምንባቡ ምንም የምናገኘው ጠቋሚ የለም:: ከዚህ የበለጠ ጠንካራ መከራከሪያ ግን ኢየሱስና አብረውት የነበሩት ከተራራው ሲወርዱ የሕግ መምህራንን ጭምር ከብዙ ሕዝብ ጋር መገናኘታቸው ነው (ማር 9÷14):: ይህ ደግሞ በጣም ርቆ ያለው የአሕዛብ አካባቢ ሊሆን እንደማይችል ያመለክታል:: ስለሆነም የሚኖን ተራራ (3,926) ነው ቢባል ይበልጥ ምክንያታዊ ይሆናል:: በፓለስቲና ያለ ከፍ ያለ ተራራ እርሱ ሲሆን የሚገኘው ከቅፍርናሆም ሰሜን ምዕራብ ነበር:: ጸሐፍት ከበታቹ ሲሆኑ፣ ጫፍ ላይ ፀጥተኛ ጊዜ ማግኘት ይቻላል:: ወደ ቅፍርናሆም ሲመለሱ፣ በእርግጥም፣ «በገሊላ በኩል» ማለፍ ይችላሉ::

እንደ ጌቴሴማኒ አትክልት ስፍራ ሁሉ ከሦስቱ ጋር ለመጸለይ ፀጥ ያለ ቦታ ነው:: ይህ የሆነው በስንት ሰዓት እንደ ነበር ባይነገረንም፣ በጣም ምሽት ላይ ነበር ቢባል አንዳንድ ነገሮችን በተመለከተ ገለጻ



ሊሰጠን ይችላል፤ (1) ወደ ተራራው ለመውጣት ስለ ወሰደባቸው ጊዜ፣ (2) ለምን ብቻቸውን እንደ ሆኑ፣ (3) ለምን ደቀ መዛሙርቱ እንደ ደከሙ፣ (4) ብርሃኑ ከመጠን በላይ ደምቆ መውጣቱ እና (5) ሌሊቱን ተራራው ላይ ማሳለፋቸው:: እንዲህ ከነበረ አራቱም ሲጸልዩ እንደ ነበርና በኋላ ግን ኢየሱስ ብቻውን እስኪቀር ድረስ አንድ በአንድ ተለይተውት እንደ ሄዱ ማሰብ ይቻላል::

**ሉቃ 9÷29-32**
**ከማቴ 17÷2፤**
**ማር 9÷2-3 ጋር**

29በመጸለይ ላይ እንዳለም [በፊታቸው
ተለወጠ[ማቴ፣ማር]] የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ [ፊቱ እንደ ሐፀይ
አበራ[ማቴ]] ልብሱም እንደ መብረቅ የሚያንጸባርቅ ነጭ ሆነ
[እንደ ብርሃን አንጸባረቀ[ማቴ]] [ማንም አጣቢ አጥቦ ሲያነጣው በማይችልበት ሁናቴ
እጅግ ነጭ ሆነ[ማር]]:: 30እነሆ፤ ሁለት ሰዎች፣ እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር
ይነጋገሩ ነበር፤ 31በክብርም ተገልጠው፣ በኢየሩሳሌም ይፈጸም ዘንድ ስላለው ከዚህ
ዓለም ስለ መለየቱ ይናገሩ ነበር:: 32ጴጥሮስና አብረውት የነበሩት ግን እንቅልፍ
ተጭኖአቸው ነበር፤ ሲነቁ ግን ክብሩንና ከእርሱ ጋር የቆሙትን ሁለት ሰዎች አዩ::

የቅርብ የተባሉት ወዳጆቹ ሲተኙ ኢየሱስ አብዛኛውን የሌሊት ጊዜ ይጸልይ እንደ ነበር ማሰብ ይቻላል (ማር 1÷35፤ ሉቃ 5÷16፤ 6÷12፤ 22÷44-46):: መልኩ ተለወጠ ማለት፣ ምድራዊ ባልሆነ ሁናቴ ተለወጠ [*metamorphao*, ሮሜ 12÷2፤ 2ቆሮ 3÷18]:: ሦስቱም ወንጌሎች የተለያየ አገላለጽ ተጠቅመዋል፤ ሆኖም ሦስቱም ፊቱና ልብሱ እንደ ብርሃን መንጣቱን አመልክተዋል:: ሙሴ ከሲና ተራራ ሲወርድ ተመሳሳይ ነገር ተለማምዶ ነበር (ዘፀ 34÷29፤ 2ቆሮ 3÷7)::

ሙሴና ኤልያስ ተገልጠው፣ ከኢየሱስ ጋር ተነጋገሩ:: ሁለቱም ከተአምራትና የመሲሑ መምጣት ከመጠበቅ ጋር በጣም የተያያዙ ናቸው:: ታዋቂው ነቢይ ሙሴ (ዘዳ 18÷16-18) ሕግን ሁሉ ይወክላል:: የመሲሑን መንገድ የሚያዘጋጀው ኤልያስ (ሚል 4÷5-6)፣ ነቢያትን

ሁሉ ይወክላል:: ኢየሱስ ደግሞ ሁለቱን ሰዎች፣ ያለፈውንና የወደ ፊቱን የእስራኤል ተስፋ ፍጻሜ ይወክላል:: በተጨማሪም የሁለቱ ሰዎች ፍጻሜ ያልተለመደ ነበር:: ሙሴን የቀበረው እግዚአብሔር ነበር[70] (ዘዳ 34÷1፣6)፣ ኤልያስ ደግሞ በዐውሎ ነፋስ ተወሰደ (2ነገ 2÷11):: ከዚህም በላይ ሙሴና ኤልያስ በራሳቸው ወገኖች ቢናቁም፣ እግዚአብሔር ግን ፈርዶላቸዋል:: በሁለት መከራዎች መካከል የተፈጸመው መለወጥ ኢየሱስም ተመሳሳይ ሁኔታን እንደሚለማመድ ያሳያል::[71]

የንግግራቸው ርእሰ ጉዳይ፣ ስለ መለየቱ [*exodus*] መውጣቱ ነበር:: ይህም ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነጻ ካወጣው ሙሴ፣ በተለይም ደግሞ ከፋሲካው በግ ጋር ያያይዘዋል:: የኢየሱስ የመጨረሻ ፋሲካ ምናልባት ከሰባት ወይም ስምንት ወር በኋላ ሊፈጸም ነው:: ፋሲካን ከመፈጸም በተጨማሪ፣ ኢየሱስ ሕጉንም ሊፈጽም ነው (ማቴ 5÷17፤ ሮሜ 10÷4፤ ቈላ 2÷14):: እንደ ሙሴ ሁሉ ኢየሱስም አዲስ ሕግና አዲስ ሕዝብ ይመሠረታል (ሮሜ 13÷10፤ ገላ 6÷2፤ ያዕ 2÷8፤ 1ዮሐ 3÷23-24)::

ያንቀላፉትን ሐዋርያት ከእንቅልፍ የቀሰቀሳቸው ውይይታቸው ወይም ብርሃኑ ሊሆን ይችላል::[72] ምናልባት በሕልማቸው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ዓይኖቻቸውን ሳያሹ አልቀረም:: ሙሴና ኤልያስ መሆናቸውን ጴጥሮስ እንዴት እንዳወቀ ምንም ፍንጭ የለንም:: መገመት የሚቻለው አንዳቸው ሌላውን ይጠሩ እንደ ነበር ወይም

[70] በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በነበረው ወቅት የተጻፈውን *The Assumption of Moses* መሠረት በማድረግ ብዙ አይሁድ ሙሴ በእርግጥ አልሞተም በማለት አምነዋል::

[71] M. Pamment, "Moses and Elijah in the Story of the Transfiguration," *ExpT* 92 (1980-81): 338-339.

[72] በግሪኩ መሠረት ሙሉ በሙሉ አንቀላፍተው ወይም፣ «አሸልበው» እንደ ነበር ግልጽ አይደለም:: ሆኖም ራእዩ አንቅቷቸዋል:: በተጨማሪም ይህ ታሪክ የፈጠራ ወይም አፈ ታሪክ ቢሆን ኖሮ ሐዋርያቱ አንቀላፍተው እንደ ነበር ማቅረቡ አስፈላጊ አይሆንም ነበር::



አገልግሎታቸው ከኢየሱስ ጋር ስለሚያያዝበት አንድ ሁኔታ አንስተው ሲነጋገሩ ሰምተው እንደ ነበር ነው::

**ማቴ 17÷4-8**
**ሉቃ 9÷33-35፤**
**ማር 9÷5-8 ጋር**

[33ሰዎቹም ከኢየሱስ ተለይተው ሲሄዱ[ሉቃ]] 4ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ በዚህ ብንሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ፈቃድህ ከሆነ፣ አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ ሦስት ዳሶች ልሥራ» አለው:: [እጅግ ፈሩ የሚናገረውን አያውቅም ነበር[ማር]]::

5እርሱ እየተናገረ ሳለ፣ ብሩህ ደመና ሸፈናቸው፤ ከደመናውም ውስጥ፣ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው [የመረጥሁት[ሉቃ]] ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት» የሚል ድምፅ ተሰማ::

6ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲሰሙ ደንግጠው በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ:: 7ኢየሱስም ቀርቦ ነካቸውና፣ «ተነሡ፤ አትፍሩ» አላቸው:: 8ቀና ብለው [ወዲያውም[ማር]] ሲመለከቱም ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ ማንንም አላዩም::

ሰዎቹ እንደ ሄዱ ጴጥሮስ፣ ያንን ወርቃማ ጊዜ የሚያስታውሰውን ነገር ማድረግ ፈለገ:: ሦስት፣ «ዳሶች» እንዲሠሩ ለኢየሱስ[73] ተናገረ:: የዐርባ ዓመቱን የምድረ በዳ ጉዞ የሚያስታውስ ሁናቴ ይሆናል:: ፍርሃትን የተንተራሰ ተገቢ ያልሆነ ነገር ነበር (ማር 9÷6):: የኢየሱስን ታላቅነት ግምት ውስጥ ያላስገባ ብቻ ሳይሆን፣ ሁኔታውን የሚያራዝም፣ የኢየሱስን አገልግሎት ዕድገትም የሚያሰናክል ነበር:: ጴጥሮስ ከአንድ ሳምንት በፊት በፊልጶስ ቂሣርያ አጠገብ ያደረገውን ዓይነት ስሕተት እያደረገ ነበር:: በዚያ ጊዜ ኢየሱስ ገሥፀው:: እዚህ ቦታ የሚገሥፀው ግን እግዚአብሔር አብ ነው::

[73] የሦስቱ ወንጌል ጸሐፊዎች ኢየሱስን መጥራት ምንም የትርጉም ልዩነት ወይም ጥቂት ልዩነት ባላቸው የተለያዩ መጠሪያዎች ተጠቅመዋል:: ማርቆስ ወንጌል ውስጥ የምናገኘው፣ «ረቢ» የሚለው ቃል ከራሱ በጴጥሮስ የተነገረ በመሆኑ ምናልባት የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም::

ጴጥሮስ በደመናና በድምፅ ተቋረጠ:: የደመናው ጊዜያዊ ዓላማ ሙሴና ኤልያስን መሰወር ነበር:: ምናልባትም የሚከሰቱት ነገሮችን የሚያመለክት ነበር፣ (ሀ) እስራኤላውያንን ቀን ይመራቸው የነበረ ደመና፣ (ዘፀ 13÷21-22)፣ (ለ) እግዚአብሔር ክብሩን ተላብሶ መገለጡ[74] (ዘፀ 19÷16)፣ (ሐ) የሰው ልጅ ወደ ፊት እንደሚመጣ (ዳን 7÷13፤ ማር 14÷62፤ 1ተሰ 4÷17):: ከዚያ በኋላ፣ «እርሱን ስሙት» የሚለውንና ወጪ ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ የተናገረውን ቃል በቃል የደገመው የእግዚአብሔር ድምፅ መጣ (ማቴ 3÷17፤ በተጨማሪ ዮሐ 12÷28 ይመ):: ሁለቱም መዝሙር 2÷7 እና ኢሳይያስ 42÷1ን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ለጴጥሮስ ብቻ የተነገረ ነው እንዳይባል፣ «ስሙት» የሚለው ትእዛዝ አንቀጽ በብዙ ቍጥር የተነገረ ነው:: መልእክቱ ግልጽ ነው፤ ኢየሱስ ከሙሴና ከኤልያስ ይበልጣል::

ጴጥሮስና ዮሐንስ ማንኛውም ሰው «ለክርስቶስ መገለጥ» የሚሰጠው ዐይነት ምላሽ ነበር የሰጡት:: በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ (ከሕዝ 1÷28፤ ዳን 8÷17፤ ራእ 1÷17 ጋር ያነ):: ኢየሱስ ሥጋዊነቱና መለኮታዊነቱ በተቀላቀለበት ያልተለመደ ሁኔታ ምላሽ ሰጠ:: ሥጋዊነቱ ወደ እነርሱ ቀርቦ ነካቸው:: መለኮታዊነቱ በተለምዶ መላእክት በሚጠቀሙበት ቃል፣ «አትፍሩ» አሏቸው::

ከመሬት ቀና ሲሉ ሁሉም ነገር ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ ሙሴ፣ ኤልያስና ደመናው ተለይተዋቸዋል:: ኢየሱስ ብቻውን ቆሟል፤ ከብሩህ ፊገግታውና ከአንጸባራቂ ዐይኖቹ በቀር የነበረው ደማቅ ብርሃን በቦታው አልነበረም::

74 *episkiazo* («ማጥላት») በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ዘፀአት 40÷35፣ «ክብር» (Shekinah) የሚለውን ቃል ለመተርጐም ጥቅም ላይ ውሏል (Liefeld, p. 928):: ስለሆነም የተባለው ተያያዥነት ጠንካራ ነው::



**§ 86**
**ስለሚመጣው ኤልያስ መነጋገራቸው**
**(ማቴ 17÷9-13፤ ማር 9÷9-13፤ ሉቃ 9÷36)**

9ከተራራው በመውረድ ሳይ ሳሉ ኢየሱስ፣ «የሰው
ልጅ ከሞት እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን ለማንም
እንዳትናገሩ» ብሎ አዘዛቸው:: [10እነርሱም የተናገሩቸውን
ቃል በልባቸው አሳደሩት[ማር]] [ስላዩት ነገር በዚያን ወቅት
ለማንም አልተናገሩም[ሉቃ]] [«ከሙታን መነሣት» ምን
ማለት እንደ ሆነ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር[ማር]]::
10ደቀ መዛሙርቱም፣ «ታዲያ የኦሪት ሕግ መምህራን፣ ኤልያስ አስቀድሞ
መምጣት አለበት የሚሉት ለምንድን ነው?» ብለው ጠየቁት::
11እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ኤልያስ በእርግጥ መጥቶ ሁሉንም ነገር
ያስተካክላል፤ 12ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ኤልያስ መጥቶአል፤ ሆኖም የፈለጉትን ነገር
አደረጉበት እንጂ አላወቁትም:: [ታዲያ፣ የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀበልና መናቅ
እንዳለበት የተጻፈው ለምን ይመስላችኋል?[ማር]] እንዲሁም የሰው ልጅ በእጃቸው መከራን
ይቀበላል::» 13በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የነገራቸው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ
መሆኑን ተረዱ::

ለማንም እንዳይናገሩ ሲያመለክት ይህ የመጨረሻው ነው::[75] ሆኖም እዚህ ላይ ኢየሱስ፣ «የሰው ልጅ ከሞት እስኪነሣ ድረስ» የሚል ጊዜ ገደብ አስቀምጧል:: ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ የሚናገሩበት ቀን ይመጣል:: ይሁን እንጂ ይህ የሚሆነው፣ ሁሉም ነገር ከተፈጸመና ሕዝቡ ያንን ለመስማት ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ነው:: ሆኖም እንዲህ እንዲህ ያለውን የተለየ ምስጢር መያዝ አዳጋች ይሆናል:: ይህ ሌሎቹ ዘጠኝ ደቀ መዛሙርት ሊያውቁት የሚገባ ዋነኛ ጉዳይ ነው:: ከዚህም በተረፈ ማን እንደሚበልጥ በቅርቡ በመካከላቸው ክርክር ሊነሣ ነው (§ 90)::

75 ማቴዎስ 8÷4፤ 9÷30፤ 12÷16፤ 16÷20፤ 17÷9፤ ማርቆስ 1÷44፤ 3÷12፤ 5÷43፤ 7÷36፤ 8÷26፣30፤ 9÷9፤ ሉቃስ 8÷56፤ 9÷21 ይመልከቱ:: ይህ ስምንት የተለያዩ ሁኔታዎችን ይጨምራል (§ 45፣ 52፣ 67፣ 68፣ 79ሀ፣ 81ለ፣ 82፣ 86) ማርቆስ ያልጠቀሰው § 68 ብቻ ነው:: ዝም እንዲሉ ስለ ተሰጠው ትእዛዝ ማብራሪያ ለማግኘት ለ§ 52 የተሰጠውን ማስታወሻ ይመ::

በጣም ቅርብ የነበሩት ሦስቱ ይህን ፈተና ማለፍ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል:: ሆኖም እንደምንመለከተው ዝም ብለዋል:: ለእኛ እንደተገለጠውም ዝም እንዲሉ ኢየሱስ የሰጠውን ትእዛዝ ያከበሩ እነርሱ ብቻ ናቸው::

ደቀ መዛሙርት አሁንም ቢሆን ኢየሱስ፣ «ከሙታን መነሣት» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ገና አላወቁም ነበር:: እንዳይጠይቁ ደግሞ በጣም ፈርተዋል:: ምናልባትም የፈሩት ምን ሊላቸው እንደሚችል ስላሰቡ ይሆናል:: ምናልባትም የፈሩት አላዋቂ ሆነው እንዳይታዩ ይሆናል:: ይህን ያህል እርግጠኛ ቢሆኑም ኢየሱስ በእርግጥ ይሞታል ብለው አልገመቱም:: ለእነርሱ መከራ የሚቀበል መሲሕ ጨረሶ የማይታሰብ ነበር:: ምናልባትም፣ «ከሙታን መነሣት» ሲል፣ (ሀ) ኢየሱስ የበፊት ዝነኛነቱን እንደገና እንደሚያገኝ፣ (ለ) ኢየሱስ እርሱን ለመግደል አይሁድ እያደረጉ የነበረውን ሤራ በድል እንደሚወጣ፣ (ሐ) ከሲና ተራራ በታች የነበሩ ሰዎች ሙሴ ሞቷል ብለው እንዳሰቡ ሁሉ ከተራራው በታች የነበሩ ሰዎች ኢየሱስ ሞቷል ብለው ገምተው እንደሆነ ሳያስቡ አይቀርም:: ስለዚህም ሲገለጥ ለሕዝቡ መንግሥቱን ያስታውቃል::

«ከሙታን መነሣት» ከሚለው የበለጠ አስገራሚው ደግሞ፣ «ኤልያስ ይመጣል» የሚለው ነው:: ሚልክያስ 4÷5-6ን መሠረት በማድረግ የመሲሑን መንገድ ለማዘጋጀት አስቀድሞ ኤልያስ እንደሚመጣ ጸሐፍት ሲያስተምሩ ነበር::[76] ያ ትክክል ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ ትንቢት ኤልያስ በአካል ከመምጣቱ ይልቅ በመጥምቁ ዮሐንስ መምጣት ተፈጽሟል በማለት ኢየሱስ እየተናገረ ነው:: ምንም

[76] ኤልያስ ባለመሞቱ አይሁድ ወደ ምድር እንደሚመለስ ይጠብቁ ነበር:: ዛሬም ቢሆን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ከክርስቶስ መመለስ ቀደም ሲል ከሁለቱ ምስክሮች አንዱ ሆኖ ኤልያስ ይመለሳል ብለው ያምናሉ (ራእ 11÷3-6) Cf. C. Blomberg, “Elijah, Election and the Use of Malachi in the New Testament,” *CTR* 2 (1987):100-108.



እንኳ ኢየሱስ በግልጽ ቢነግራቸውም፣ ሦስቱም ይህን ገና አላስተዋሉም ነበር (ከማቴ 11÷14፤ ሉቃ 1÷17 ጋር ያነ):: አንዳንዴ አንድን ከበድ ያለ ጽንሰ ሐሳብ ለመረዳት ሁለት ሦስት ጊዜ መስማት ይኖርብናል::

ዮሐንስ በሚልክያስ 4÷5-6 የተነገረለት ኤልያስ ከሆነ፣ «የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች» የሚመልሰው እንዴት ነው? በአይሁድ አስተሳሰብ ይህ የዝምድናን ያህል ቤተ ሰብን የሚመለከተ አይደለም:: መጥምቁ ዮሐንስን የሰሙ ብዙ አይሁድ ንስሐ ገብተዋል፤ የአባቶቻቸውን መንገድ በማስታወስ መሲሑን ለመቀበል ተዘጋጅተዋል:: ይሁን እንጂ፣ አብዛኞቹ አይሁድ ኢየሱስን እንደ መሲሕ ለመቀበል ገና አለመዘጋጀታቸውን ማን ሊክድ ይችላል:: (በዚያ ጊዜ ኢየሱስ በገለልተኛ ስፍራ የነበረውና ዝም እንዲሉ ዐሥራ ሁለቱን እየነገረ የነበረው በዚህ ምክንያት ነበር::) ስለሆነም፣ ምንም እንኳን የዮሐንስ ጥፋት ባይሆንም መንገድ በማዘጋጀት ረገድ አገልግሎቱ በአብዛኛው የተሳካ እንዳልነበር የግዳችንን መቀበል ይኖርብናል ማለት ነው:: ወደ ሚልክያስ 4÷5-6 ስንመለስ፣ «መጥቼ ምድርን በርግማን እንዳላጠፋ፣ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ...» የሚል ትንቢት እንመለከታለን:: ዮሐንስ የራሱን ድርሻ ተወጥቷል፤ ሕዝቡ ግን የራሳቸውን ድርሻ አልተወጡም:: በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ርግማን ወደ ምድራቸው ሊመጣ ነው (ከማቴ 24 ጋር ያነ)::

ከዚህም በላይ፣ ዮሐንስ ኤልያስ መሆኑ፣ ኢየሱስም መሲሕ መሆኑ፣ ከሚመጣባቸው ጥፋት ነጻ አያደርጋቸውም:: እንዲህ ያለው መከራ በትንቢት የተነገረ መሆኑን ኢየሱስ አመልክቷል (ማር 9÷12):: እየተነገረ ያለው ኢሳይያስ 53 ላይ ስላለው ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም ስለመጥምቁ ዮሐንስ ላነሡት ጥያቄ ኢየሱስ መልስ ሰጥቷቸዋል:: እርሱ ኤልያስ ነበር (ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ)፣ ተልዕኮውን በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው አገልግሎቱ፣ «የተሳካ»፣ አለመሆኑን ይናገራሉ:: በተጨማሪም ኢየሱስ በአንደበት ላልገለጹት ጥያቄ ጭምር

መልስ ሰጥቷል:: መከራ ስለሚደርስበት መሲሕ ማሰብ አልቻሉም:: ኢየሱስ እንዳመለከተው፣ የመሲሑን መንገድ የሚያዘጋጀው መከራ ተቀብሏል:: ታዲያ፣ ከመሲሑ ከዚህ የተለየ የሚጠብቁት ለምድንነው? ለእርሱ መንገድ ያዘጋጅ የነበረው በሰዎች ከተናቀና ከተገደለ፣ መሲሑማ እንዴት ከዚያ የበለጠ አይደርስበት?

§ 87
አጋንንት የነበሩበት ልጅ መንፈስ
(ማቴ 17÷14-20፤ ማር 9÷14-29፤ ሉቃ 9÷37-43)

ይህ ክፍል፣ «ከመለኮታዊው፣ ወደ ዕለታዊው» የሚል ርእስ ሊሰጠው ይችላል:: ኢየሱስና ሦስቱ ደቀ መዛሙርት በሕይወታቸው በጣም ከፍ ያለ የሚባል መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ነበሩ:: ከተራራው ሲወርዱ፣ ኢየሱስ ፀበኛና እምነተ ቢስ ከሆኑ ሰዎችና ደካማነት ከተሰማቸው ሐዋርያቱ ጋር ተገናኘ:: አለማመን፣ አለመብሰልና ፀበኝነት በሞላበት እውን ዐለም ውስጥ እንደምንኖር ጠንካራ ማሳሰቢያ ነው:: ያም ሆኖ ግን የእርሱ አቻ የሆነ መለኮታዊ ልምምድ የሚያሻው ዓለም ነው:: ሃይማኖቱም የሚካተተው እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ ውስጥ እንጂ ተራራ ላይ አይደለም::

ማር 9÷14-16ን ከሉቃ 9÷37 ጋር

14 [በማግስቱ ከተራራው ከወረዱ በኋላ[ሉቃ]] ወደ
ቀሩት ደቀ መዛሙርት ተመልሰው ሲመጡ፣ ብዙ ሕዝብ
ከበዋቸው ጸሐፍት ከእነርሱ ጋር ሲከራከሩ አዩ:: 15 ሕዝቡ
ሁሉ ሲያዩት ወዲያው ተደንቀው እጅ ሲነሡት ወደ እርሱ
ሮጡ:: 16 እርሱም፣ «ከእነርሱ ጋር የምትከራከሩት ስለምን
ጉዳይ ነበር» ሲል ጠየቃቸው::



ኢየሱስ ከተራራው ሲወርድ እየተጨቃጨቁ ያሉ ሰዎችን ድምፅ ሰማ:: ኢየሱስ አንዳች ክፉ ነገር ሲያደርግ ለመያዝ አድብተው ይጠብቁ የነበሩ ጸሐፍት ጭቅጭቁን አባብሰውት ነበር:: ኢየሱስ በቦታው ባልነበረ ጊዜ ጋኔን ማስወጣት ያቃታቸውን የተቀሩትን ዘጠኝ ደቀ መዛሙርት ለማዋረድ ሁኔታውን ተጠቀሙበት:: ጭቅጭቁ ምንን አስመልክቶ እንደ ነበር ባይነገረንም አጋንንት ለማስወጣት ያላቸውን ሥልጣንና ኢየሱስ ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር ያለው ግንኙነት ላይ ያተኰረ ሊሆን እንደሚችል እርግጠኞች ነን (ከማቴ 9÷34፤ 12÷22-37፤ ማር 3:20-30 ጋር ያነ)::

ኢየሱስ፣ «በትክክለኛው ጊዜ» በመምጣቱ ሕዝቡ ተደንቀዋል:: አንዳንዶች በኢየሱስ ገጽ ፀዳል መደነቃቸውን አመልክተዋል (ከዘፀ 34÷29-35 የሙሴ ሁኔታ ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ፣ ይህ ቀደም ሲል ኢየሱስ ዝም እንዲሉ ከሰጠው ትእዛዝ ጋር አይስማማም:: ይልቁንም ሲሰርቅ እንደ ተያዘ ሰው ሁሉ የኢየሱስ እዚያ መገኘት ብቻውን አስደንግጦአቸዋል ቢባል ይበልጥ አሳማኝ ይሆናል:: ጸሐፍት የያዙት ማንጓጠጥ መቀጠል እንደማይችል ዐውቀዋል:: ዘጠኙ ደቀ መዛሙርትም ያንን ልጅ መፈወስ ባለ መቻላቸው ሲያጠፉ እጅ ከፍንጅ እንደ ተያዘ ልጅ ሆነዋል:: ደቀ መዛሙርቱ ማድረግ ያቃታቸውን ኢየሱስ ማድረግ እንደሚችልና ይህ አስደናቂ ነገር የሚታይበት ጊዜ እንደሚሆን ሕዝቡ ተረድተዋል::

«የምትከራከሩት ስለምን ጉዳይ ነበር?» በማለት ኢየሱስ ላቀረበው ጥያቄ እዚያ የነበሩ የሰጡት መልስ ዝምታ ነበር:: ከእንግዲህ ዝም ማለት ያልቻለ ምስኪኑ አባት ዝምታውን ሰበረ:: ለአምልኮ ባይሆንም ለአክብሮት ያህል ኢየሱስ እግር ሥር ተንበረከከ:: ጥያቄው ቀላል ሆኖም ልባዊ ነበር:: ይህ ብቸኛ ልጁ ነበር (እንደ ኢያኢሮስና በናይን እንደ ነበረችው መበለት)::